አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ
የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል
የድህረ- ምረቃ መርሀ ግብር

በትግራይ ክልል ሰሜናዊ ምዕራብ ዞን በተመረጡ ሦስት ትምህርት ቤቶች የሚዘጋጁ የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ግምገማ

በ
አብርሃም መስፍን

መጋቢት 2003 ዓ.ም
አዲስ አበባ

በትግራይ ክልል ሰሜናዊ ምዕራብ ዞን በተመረጡ ሦስት ትምህርት ቤቶች የሚዘጋጁ የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ግምገማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

የድህረ- ምረቃ መርሀ ግብር

ለተግባራዊ ስነ- ልሳን አማርኛን ለማስተማር

ኤም. ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

አብርሃም መስፍን

ILS LIBRARY ADDIS ABABA

መጋቢት 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

የድህረ- ምረቃ መርሀ ግብር

በትግራይ ክልል ሰሜናዊ ምዕራብ ዞን በተመረጡ ሦስት ትምህርት ቤቶች የሚዘጋጁ የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ግምገማ

በ

አብርሃም መስፍን

መጋቢት 2003 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

_____	_____
አማካሪ	ሬርማ
_____	_____
አማካሪ	ሬርማ
_____	_____
ፈታኝ	ሬርማ

ADDIS ABABA UNIVERSITY LIBRARY

ምስጋና

ከሁሉም አስቃድሜ የፀጋ ሁሉ ባለቤት የሆነውን እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ ለዚህ ስላደረሰኝ ክብር እና ምስጋና ይድረሰው እላለሁ።

በመቀጠል ይህ ጥናት ተጀምሮ እዚህ ደረጃ እስኪደርስ ድረስ ወርቃማ ጊዜያቸውን ሳይሰሱ መሰዋዕት በማድረግ ሙያዊ ምክራቸውን ለሰጡኝ አማካሪዎቼ ለዶክተር ጌታሁን አማረ እና ለአቶ ታደሰ ሲባሞ ከልብ ከልብ አመሰግናቸዋለሁ።

የትምህርት ወጪዬን በመሸፈን ይህን ትምህርት እንድማር እድሉን ላመቻቸልኝ የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮም አመሰግናለሁ። በትምህርቱ ቆይታ በቂ እውቀት እንዳገኝ ሁኔታዎችን በማመቻቸት እዚህ ደረጃ እንድደረስ ላደረገኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲም ሳላመሰግን አላልፍም። ይህን ጥናት በማካሂድበት ወቅት አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ የሶስቱ ትምህርት ቤቶች ርዕሰ መምህራን፣ምክትል ርዕሰ መምህራንና መምህራን ምስጋናዬ ይድረሳቸው እላለሁ።

በገንዘብም ሆነ በሀሳብ ከጎኔ በመቆም ላበረታቱኝና እዚህ ደረጃ እንድደረስ ለረዱኝ ቤተሰቦቼና ጓደኞቼ በተለይም ደግሞ ጓደኛዬ አዜብ ክፍለን ከልቤ አመሰግናለሁ።

በመጨረሻም ይህን ጥናታዊ ጽሑፌን በትእግስት አርማና አስተካክላ የጻፈችልኝን ወይንሸት አሸናፊን አመሰግናታለሁ።

ማውጫ

ገጽ

ምስጋና ---------- I

ማውጫ ---------- II

የሰንጠረዥ ማውጫ ---------- III

የአባሪዎች ማውጫ ---------- IV

አጠቃሎ ---------- V

ምዕራፍ አንድ:-መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ ---------- 1

1.2 የጥናቱ አላማ ---------- 5

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ---------- 5

1.4 የጥናቱ ወሰን ---------- 6

1.5 ቁልፍ ቃላት ---------- 7

1.6 መዳየ ቃላት ---------- 7

1.7 አህፅሮተ ቃል ---------- 8

ምዕራፍ ሁለት:-የተዛማጅ ፅሑፎች ቅኝት

2.1 የፈተና ምንነትና አስፈላጊነት ---------- 9

2.2 የጥሩ ፈተና መገለጫ ባህርያት ---------- 11

2.2.1 አስተማማኝነት (Reliability) ---------- 12

2.2.2 ተተግባሪነት (Practicability) ---------- 13

2.2.3 ተገቢነት (Validity) ---------- 13

2.2.3.1 የተገቢነት ምንነት ---------- 13

2.2.3.2 የተገቢነት አይነቶች ---------- 15

2.4 የቋንቋ ፈተና ምንነት፣ አላማና አስፈላጊነት ---------- 18

2.4.1 የቋንቋ ፈተና ምንነት ---------- 18

2.4.2 የቋንቋ ፈተና አላማ ---------- 20

2.4.3 የቋንቋ ፈተና አስፈላጊነት ---------- 21
2.5 የቋንቋ ፈተና አይነቶች ---------- 22
2.5.1 የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና (Aptitude Test)---------- 25
2.5.2 የደረጃ መለኪያ ፈተና (Proficiency Test) ---------- 25
2.5.3 የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና (Diagnostic Test) ---------- 24
2.5.4 የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement Test) ---------- 25
2.5.4.1 የችሎታ መለኪያ ፈተና ምንነት---------- 25
2.5.4.2 የችሎታ መለኪያ ፈተና ይዘት አመራረጥ ---------- 27
2.5 የቋንቋ ፈተና እና የቋንቋ ትምህርት---------- 29
2.6 የቋንቋ ፈተና እና የቋንቋ መማርያ መፅሐፍ ---------- 30
2.7 የቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት፣ ምንነትና አስፈላጊነት ---------- 32
2.7.1 የቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት ምንነት ---------- 32
2.7.2 የቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት አስፈላጊነት ---------- 35
2.8 የቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት ደረጃን መጠበቂያ መንገዶች ---------- 35
2.9 የቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት መገምገምያ ስልቶች---------- 37
2.10 የቀደምት ስራዎች ቅኝት ---------- 38
ምዕራፍ ሶስት:-የጥናቱ ዘዴ
3.1 የናሙና አመራረጥ ---------- 42
3.1.1 የጥናቱ ክልልና ዞን ናሙና አመራረጥ ---------- 42
3.1.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ ---------- 42
3.1.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ---------- 42
3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ---------- 42
3.3 የመረጃ ትንተና ዘዴ ---------- 43
ምዕራፍ አራት:-የመረጃ ትንተና እና ውጤት
4.1 ከሰነዶች የተገኙ መረጃዎች ---------- 45
4.1.1 የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ---------- 45
4.1.1.1 የመፅሐፉ አጠቃላይ ገፅታ ---------- 45
4.1.1.2 በመማሪያ መፅሐፉ የሚገኙ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች---------- 46
4.1.2 የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ይዘት ---------- 49

4.1.2.1 የ2002 ዓ/ም የሴሚስተር አጋማሽ ፈተናዎች ይዘት ---------- 49
4.1.2.2 የ2002 ዓ/ም አንደኛ መንፈቅ አመት ማጠቃለያ ፈተናዎች ይዘት -- 50
4.1.2.3 የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ሞዴል ፈተና ይዘት ---------- 52
4.1.2.4 የ 2003ዓ.ም የሰሚስቴር አጋማሽ ፈተናዎች ይዘት ---------- 54
4.1.2.5 የመማሪያ መፅሐፍ እና የፈተናዎቹ ይዘት አጠቃላይ ተዛምዶ ----- 56
4.2 ከቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተናና ውጤት ---------- 61
4.2.1 የመረጃ ሰጪዎች አጠቃላይ መረጃ ---------- 61
4.2.2 የቃለ- መጠይቅ ምላሽና ማብራሪያ ---------- 62
ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያና አስተያየት
5.1 ማጠቃለያ ---------- 67
5.2 አስተያየት ---------- 69
ዋቢ መጻሕፍት ---------- 71

የሠንጠረዥ ማውጫ

ገጽ

ሠንጠረዥ 1.1 የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በመፅሐፍ ያላቸው የይዘት ሽፋን --------- 48

ሰንጠረዥ 1.2 በ 2002ዓ.ም የተዘጋጀ የሰሚስቴር አጋማሽ ፈተናዎች ይዘት ---------- 49

ሰንጠረዥ 1.3 በ 2002 ዓ.ም የተዘጋጁት የአንደኛ መንፈቅ አመት ማጠቃለያ

ፈተናዎች ይዘት ---------- 51

ሠንጠረዥ 1.4 የ 2002ዓ.ም የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ሞዴል ፈተና ይዘት ---- 53

ሠንጠረዥ 1.5 የ 2003ዓ.ም የሰሚስቴር አጋማሽ ፈተናዎች ይዘት---------- 55

ሠንጠረዥ 1.6 የመማሪያ መፅሐፍና የፈተናዎቹ ይዘት ተዛምዶ ---------- 57

ሠንጠረዥ 1.7 የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በመማሪ መፅሐፉና በፈተናዎቹ

ከተሰጣቸው ሽፋን አንጻር ያላቸው ደረጃ ---------- 59

ሠንጠረዥ 1.8 የመረጃ ሰጪዎች አጠቃላይ መረጃ ---------- 61

የአባሪዎች ማውጫ

አባሪ አንድ ፡- የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ናሙና ፈተናዎች ---------- 74

አባሪ ሁለት፡- በአስረኛ ክፍል አማርኛ መመሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች -- 88

አባሪ ሦስት፡- የቃለ መጠይቅ ዝርዝር ጥያቄዎች ---------- 90

አባሪ አራት፡- የቃለ መጠይቅ መልስ ---------- 91

አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በትግራይ ክልል ሰሜናዊ ምዕራብ ዞን በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች የሚዘጋጁ የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ደረጃን መገምገም ሲሆን ጥናቱ በትምህርት ቤቶቹ መምህራን በሚዘጋጁ የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተናዎቹ ብቻ የተወሰነ ነው። በዚህ ጥናት ውስጥ በ 2003ዓ.ም የተዘጋጀው የሰሚስተር አጋማሽ ፈተናን ጨምሮ በ 2002ዓ.ም የተዘጋጁት የሰሚስተር አጋማሽ፣ የማጠቃለያ እና ሞዴል ፈተናዎች፣ የአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ እንዲሁም ከትምህርት ቤቶቹ የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ የመረጃ ምንጭ በመሆን አገልግለዋል። የሰነድ ምርመራ እና ቃለ መጠይቅ መረጃዎቹን ለመሰብሰብ በጥቅም ላይ የዋሉ መሳሪያዎች ሲሆኑ ከነዚህ የተገኙ መረጃዎች ለመተንተን ደግሞ በቁጥርና በመቶኛ መግለፅ፣ የደረጃ ልዩነት ዝምድና አመልካች ስሌት እንዲሁም የገለጻ ስልት በጥቅም ላይ ውለዋል። በመሆኑም ጥናቱ በዋናነት በሰነድ ምርመራ ላይ ትኩረት በማድረግ አይነታዊና መጠናዊ (Qualitative and Quantitative) የምርምር ዘዴዎችን በጥምረት የተጠቀመ ነው። ጥናቱ ከሰበሰበውን መረጃ ያገኘውን ውጤት እንደሚያመለክተው በተጠቀሰው አካባቢ ለአስረኛ ክፍል የሚዘጋጁ ትምህርት ቤት አቀፍ ፈተናዎች ያላቸውን የይዘት ተገቢነት ደረጃ መካከለኛ (Moderate) የሚባለው ነው። የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መፅሐፉ እና በፈተናዎቹ ውስጥ በአይነትም ሆነ በመጠን ከተሰጣቸው ሽፋን አንጻር ሲታይ ተመጣጣኝ ሆነ ውክልና አይታይባቸውም።

ምዕራፍ አንድ:-መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ

በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የመማር ማስተማር ሂደት ዋና አላማ በተማሪዎች ላይ ይታያሉ ተብለው የሚጠበቁትን የመማር ውጤቶችና ትምህርቱ በመጨረሻ ላይ ለማሳካት ያቀዳቸውን አላማዎች ስኬታማ እንዲሆኑ እገዛ ማድረግ ነው (Gronulonad 1981:7)። እነዚህ የመማር ውጤቶችና የትምህርት አላማዎች ደግሞ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተቀመጡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች አማካኝነት በተግባር የሚገለፁ ናቸው።

Desalegn and Girma (2009) እንደሚገልፁት ደግሞ በትምህርት መርሃ ግብር የተቀመጡት አላማዎች ለማሳካት የሚያስችሉ የመማር ማስተማር ክንውኖች እንዴት እየሄዱ እንደሆነ፣ ምን አይነት ማሻሻያ ወይም ለውጥ ሊደረግባቸው እንደሚገባ፣ እንዲሁም የመማር ማስተማር ሂደቱን የሚያጠናክሩ ተጓዳኝ ጉዳዮች ምን መምሰል እንዳለባቸው ወዘተ በሚሉት ጉዳዮች ላይ ትምህርታዊም ሆነ አስተዳደራዊ ውሳኔ ለመስጠት ከፈተና የሚገኝ መረጃ ትልቅ ፋይዳ አለው።

የቋንቋ ትምህርትም እንደሌሎች የትምህርት አይነቶች በተማሪዎች ላይ ለሚታዩት ድምር አካዳሚያዊ እና ማህበራዊ ለውጦች የማይናቅ አስተዋፅኦ ያላቸው የትምህርት አላማዎችን ነድፎ የመማር ማስተማር ተግባር እንደሚያከናውን ይታወቃል። እነዚህ የትምህርት አላማዎችን መሰረት በማድረግ በክፍል ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት ተግባራዊ የሚደረገው የቋንቋ ትምህርት ደግሞ ሂደቱንና ውጤቱን በተመለከተ መረጃ ከሚሰበስብባቸው መሳሪያዎች አንዱ የቋንቋ ፈተና ነው።

የቋንቋ ፈተና በቋንቋ ላይ ከሚደረጉ ሌሎች ተግባራት ይልቅ ከቋንቋ ትምህርት ጋር የጠበቀ ትስስር እንዳለው ብዙ ምሁራን ይገልፃሉ። Ur (1996:31) እና Hughes (1989:8) እንደሚገልፁት የቋንቋ ፈተና በቋንቋ ትምህርት ታሪክ ውስጥ ከረጅም ዘመናት ጀምሮ የመማር ማስተማሩ ሂደት አካል ሆኖ ሲሰራበት የነበረና አሁንም እየተሰራበት ያለ፣ አንድ ተማሪ የቋንቋ ዕውቀትና ችሎታ፣ ድክመትና ጥንካሬ ፍላጎትና

የዕለት ተዕለት መሻሻል ወዘተ በሚመለከት ውሳኔዎችን ለማሳለፍ እንዲሁም ቀጣይ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችሉ መረጃዎችን የሚሰበሰብበት መሳሪያ ነው።

ምሁራኑ እንደሚስማሙበት የቋንቋ ፈተና በቋንቋ ትምህርቱ፣ ሂደትና ውጤት ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ትምህርታዊ የመረጃ ምንጭ መሆኑን ነው። Allen (1977:42) ስለ ቋንቋ ፈተና ሲገልፁ «በቋንቋ ፈተና አማካኝነት መምህራን ተማሪዎቻቸው ምን እውቀት እንደጨበጡና እንዳልጨበጡ ወይም እነሱ ያስተማሩትን ትምህርት ምን ያህል ከግብ እንደ ደረሰ ለማወቅ ይረዳቸዋል። ከዚህ የተነሳም መደረግ የሚገባቸው ለውጦችንና መሻሻሎችም ምን ምን እንደሆኑ ለይተው እንዲያውቁ ያግዛቸዋል»ብለዋል።

Harrison (1983:1) Alderson et al (1995:1) Brown (1996:123) የተባሉት ምሁራን ደግሞ የቋንቋ ፈተና ተማሪዎች በተማሩት ትምህርት ዙሪያ የተገነዘቡትን ዕውቀት ለመረዳትና ከአንድ ክፍል ደረጃ ወደ ሌላው የሚሸጋገሩበትን ሁኔታ ለመወሰን የሚያስችል መረጃ የሚገኝበት መሳሪያ መሆኑን ጠቁመዋል። Ur (1996:34)ም «የቋንቋ ፈተና መምህሩ የሚያስተምርበትን ስነ-ዘዴ በብቃት ለመመርመርና የትምህርት ይዘቱን ከተማሪዎች ደረጃ አንፃር ምን ያህል የተጣጣመ መሆኑን ለመመዘን አይነተኛ መሳሪያ ነው። በተጨማሪም ተማሪዎች የተማሩትን ከማወቅ አኳያ በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ በመረዳት ቀጥሎ ምን መማር እንዳለባቸው ለመወሰን ያስችላል» በማለት ይገልፃሉ። ከዚህ ገለፃ ፈተና በአንድ ደረጃ ላሉ ተማሪዎች የሚቀርበው የትምህርት ይዘትና አቀራረብ ምን መምሰል እንዳለበት ለመወሰንም ትልቅ ሚና የሚጫወት መሆኑን መረዳት ይቻላል።

በአጠቃላይ ከላይ በምሁራኑ የተሰጡ ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው በክፍል ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት በተማሪዎች ላይ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አለማምጣቱን መረጃ ለማግኘት ከተፈለገ ፈተና አይነተኛ መሳሪያ ነው። የቋንቋ ፈተናም በቋንቋ ትምህርቱ ያለውን የመማር ማስተማር ሂደት ለመገምገምና ተማሪዎች ያስቡትን አጠቃላይ ሁኔታ ለማወቅ እንዲሁም ቀጣይ ተግባራትን ለመወሰን ቁልፉ ሚና የሚጫወት መረጃ አመንጪ መሳሪያ ነው።

ይህ እንዲህ ሆኖ ሳለ የቋንቋ ፈተና ትክክለኛውንና ተፈላጊውን መረጃ ማቀበል ያስችለው ዘንድ በጥራት ሊዘጋጅ እንደሚገባ የተለያዩ የመስኩ ምሁራን ይስማሙበታል። ከፈተናው የሚገኘው መረጃ ለተፈለገው አላማ እንዲውልና የተፈለገውን እርምጃ ተወስዶ የመማር ማስተማር ሒደቱን ስኬታማ ለማድረግ በፈተና ይዘትና አዘገጃጀት ላይ ትልቅ ትኩረት መደረግ ይኖርበታል።

Gronulonad (1981:65) እንደሚገልፀት አንድ ፈተና በጥራት የተዘጋጀና ትክክለኛውን መረጃ እንዲሰጥ ከሚያስችሉት ጉዳዮች አንዱ ተገቢነት (validity) የሚባለውን ነው። ተገቢነት በተለያዩ መልኮች የሚገለፅ ቢሆንም በተለይ ደግሞ የይዘት ተገቢት ከምንም በላይ አስፈላጊና አይቀሬ ጉዳይ ነው። አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት ይኑረው ሲባል በጥያቄነት ያካተታቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በአይነትም ሆነ በመጠን በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከተሰጣቸው ሽፋን አንፃር ሲታይ ተመጣጣኝ የሆነ ውክልና ሊኖራቸው ይገባል ማለት ነው(Cronbach፡1970:145)።

Gronulonad (1981:67) በአንድ ትምህርታዊ ፕሮግራም ላይ ተማሪው ምን ያህሉን እንዳወቀ ለመለካት የሚዘጋጅ ፈተና አንድ በዋነኛነት ሊያሟላው የሚገባ ጉዳይ ቢኖር የይዘት ተገቢነት መሆኑን ይገልፃሉ። «የይዘት ተገቢነት የምንለው ለፈተና የቀረበውን ይዘት ምን ያህሉን የተሰጠውን ትምህርት ይወክላል? ወይም የፈተናው ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ የተሰጠውን ትምህርት ናሙና (sample) መሆን አለመሆናቸውን የሚመለከት ሲሆን የፈተናው አቀራረብ ደግሞ የተማሪዎች ችሎታና ስነ-ልቦናዊ ደረጃ ያገናዘበ መሆኑን የሚፈተሽበት ነው» በማለት Brown (1996:253) ይገልፃሉ።

በቋንቋ ፈተና የሚቀርብ ጥያቄ ተማሪዎች የተማሩትን ይዘት ከጫፍ እስከ ጫፍ የሚዳስስ ካልሆነና በተወሰኑ የትምህርቱ ይዘቶች ብቻ ላይ የሚያተኩር ከሆነ የተማሪዎች ትክክለኛ ብቃት የመለካት ችሎታ ሊኖረው አይችልም። Gronulonad (1981: 67) እንደሚገልፀት ፈተና የአንድ ትምህርት አይነት ርዕሰ ጉዳዮችን ስፋትና ጥልቀትን ግምት ውስጥ በማስገባት ወሳይ በሆነ መልኩ ያዘጋጃል። የተማሪዎች የፈተና ውጤቱም የተማሩትን የትምህርት ዓይነት ምን ያህሉን ማወቅ እንደቻሉ የሚያመለክት ይሆናል። በርግጥ አንድ ፈተና ፍፁም ተገቢነት ያለው ነው የሚባል አይደለም። ነገር ግን ደረጃ በደረጃ ተገቢነቱ የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል ይላሉ።

Cronbach (1970:145) የተባሉት ምሁር በበኩላቸው የይዘት ተገቢነት የምንለው በትምህርትነት የቀረበውን ይዘት በአግባቡና በትክክል በፈተናው ላይ ተወክሎ መገኘት መቻሉን የሚያመለክት ነው፤ ካሉ በኋላ ይህም አጠቃላይ የትምህርት ይዘቱ በስርዓት በመከፋፈል ናሙና እየወሰዱ በማካተት ፈተና ማዘጋጀት የተሻለ መንገድ መሆኑን ያስረዳሉ።

ከዚህ በተጨማሪም Gronulonad (1981:69) የአንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት ለመጠበቅ የንሞና (sampling) ሂደትን መከተል አስፈላጊ መሆኑ ያብራራሉ። ይህን የንሞና ሂደት ለማከናወንና የይዘት ተገቢነቱን የጠበቀ ፈተና ለማዘጋጀት የፈተና ይዘት መወሰኛ ሠንጠረዥ (Table of Specification) የተሰኘ ባለ ሁለት ረድፍ ቻርት ማዘጋጀት ያስፈልጋል በማለት ይገልፃሉ። ይህ ባለ ሁለት ረድፍ ቻርት የትምህርት ይዘትና ዝርዝር የትምህርት አላማዎችን የያዘ ነው። ይህንን ሠንጠረዥ በመጠቀም ቀድሞ የተነደፉትን የትምህርት አላማዎችንና ተማሪዎች የተማሯቸው የትምህርት ይዘቶችን መሠረት ያደረገ ፈተና አዘጋጆቶ የፈተናውን የይዘት ተገቢነት ደረጃውን ከፍ የሚልበት አጋጣሚ መፍጠር ይቻላል።

በአጠቃላይ ከላይ በምሁራኑ እንደተጠቀሰው አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት ደረጃውን እንዲጠብቅ አድርጎ ማዘጋጀት እጅግ አስፈላጊ ብቻም ሳይሆን የማይቀር ጉዳይ መሆኑ ነው። የፈተና የይዘት ተገቢነት ደግሞ በደረጃ የሚቀመጥ እንጂ ፍፁም ተገቢ ወይም ኢ-ተገቢ በማለት የሚገለጽ እንዳልሆነ መረዳት ይቻላል። በመሆኑም ምሁራኑ እንደገለፁት የትምህርት አላማዎችና ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ካላቸው የስርጭት መጠን አንፃር በፈተና ላይ ሊኖራቸው የሚገባውን ውክልና የያዘ የፈተና ይዘት መወሰኛ ሠንጠረዥ በማዘጋጀትና ናሙና በመውሰድ በይዘት ተገቢነት ረገድ ሊመጣ የሚችለው የፈተና ችግር መቅረፍ ይቻላል። አጥኚው በስራ በተሰማራበት አካባቢ በአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ዝግጅት ላይ የፈተናዎቹ የይዘት ተገቢነት ደረጃን ዝቅ የሚያደርጉ ጉዳዮች እንዳሉ አስተውሏል።

ከዚህ በመነሳት በትግራይ ክልል ሰሜናዊ ምዕራብ ዞን በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች የሚዘጋጁት የአስረኛ ክፍል ትምህርት ቤት አቀፍ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ከዚህ መሰረተ-ሀሳብ አንፃር የይዘት ተገቢነት ደረጃቸው ምን እንደሚመስል ለመመልከት ተነሳስቷል።

1.2 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በትግራይ ክልል ሰሜናዊ ምዕራብ ዞን በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች የሚዘጋጁት የአስረኛ ክፍል ትምህርተ ቤት አቀፍ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነትን መፈተሽ ነው።

ከዚህ ዋና አላማ ስርም የሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል። እነሱም፡-

ሀ.በአስረኛ ክፍል ትምህርት ቤት አቀፍ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በመጠንም ሆነ በአይነት ለደረጃው በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ከተሰጣቸው ሽፋን አንጻር ሲታይ ተመጣጣኝ የሆነ ውክልና ያላቸው ናቸው?

ለ.በተጠቀሰው አከባቢ የሚዘጋጁት የተተኳሪ ቋንቋ የአስረኛ ክፍል ትምህርት ቤት አቀፍ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነታቸው በየትኛው ደረጃ ይገኛል?

ሐ.በተመረጡት ሶስት ትምህርት ቤቶች ያሉት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ፈተናዎቹን ለማዘጋጀት የሚከተሉት ስልት ምንድን ነው? መምህራኖቹ የፈተና ይዘት መወሰኛ ሠንጠረዥ የመጠቀም ልምዳቸው ምን ይመስላል? የሚሉት ናቸው።

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

በትምህርት ነክ ጉዳዮች ላይ የሚደረግ ጥናት ለመማር ማስተማሩ ሂደት የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ እንዳለው ግልፅ ነው። በመሆኑም ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል።

ሀ.የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲያስተምሩት በተዘጋጀላቸው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን በአይነትና በመጠን ተመጣጣኝ የሆነ ፈተና እንዲያዘጋጁ ጥቆማ ይሰጣል።

ለ.መምህራን የሚያቀርቧቸው ፈተናዎች በጥንቃቄ ለማዘጋጀት ፈተናዎች ለጤናማና ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደት የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ከፍ እንዲል እገዛ ይሰጣል።

ሐ.የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚያዘጋጁት ፈተና የተማሪዎቻቸውን ብቃት በትክክል መለካት አለመለካቱን እንዲረዱና የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ያነሳሳል።

መ. በመስኩ ወደፊት ለሚካሄዱ ተመሳሳይ ጥናቶች መነሻ በመሆን መጠነኛ አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይችላል።

1.4 የጥናቱ ወሰን

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ይህ ጥናት በትግራይ ክልል ሰሜናዊ ምዕራብ ዞን በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች የሚዘጋጁ የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ላይ ያተኮረ ነው። በመሆኑም ጥናቱ ከቦታ አንፃር በተጠቀሰው አካባቢ ብቻ ተወስኖ የሚካሄድ ጥናት ነው።

በጥናቱ ትኩረት የሚደረግባቸው ፈተናዎች በ 2003ዓ.ም የተዘጋጀው የሰሚስተር አጋማሽ ፈተናን ጨምሮ በ 2002ዓ.ም የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ የአስረኛ ክፍል የሰሚስቴር አጋማሽ ፈተና፣ የሰሚስተር ማጠቃለያ እና ሞዴል የተባሉት ፈተናዎች ናቸው።በተጠቀሱት ጊዜያት የተዘጋጁ ፈተናዎችን የተመረጡበት ምክንያት አጥኚው በተሰያዩ ደረጃዎች እየተደረጉ ካሉት የመምህራን ስልጠናና የመማሪያ መጻሕፍት መሻሻሎች ጋር ተያይዞ በአሁን ወቅት ያለውን የፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ደረጃ ምን እንደሚመስል ለማወቅ ፍላጎት ስላለው ነው። ለዚህ እንዲያግዝና መረጃውን ወቅታዊ እንዲሆን ለማድረግ የዚሁ አመት (2003ዓ.ም) ፈተናዎችን እንዲካተቱ ተደርጓል።

ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ በተጠቀሰው የትምህርት ዘመን ውስጥ በተዘጋጁት ትምህርት ቤት አቀፍ የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ላይ ብቻ ያተኮረ ሲሆን በሀገር

አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁት ፈተናዎችን አያካትትም። ጥናቱ ትኩረት ያደረገው በትምህርት ቤቶች መርሀ- ግብር መሰረት መደበኛ በሆነ ጊዜ የሚቀርቡ ወይም የችሎታ መለኪያ ፈተና የሚባሉ የፈተና አይነቶችን ነው። ይህም የሰሚስተር አጋማሽ፣የሰሚስተር ማጠቃለያ ፈተና እና በሁለተኛው መንፈቅ አመት የሚዘጋጀው ሞዴል ፈተናን የሚያካትት ነው።

ጥናቱ በአሁኑ ወቅት በአገልግት ላይ የሚገኘውን የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ እና ለዚህ ክፍል ደረጃ የተሰጡ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ያላቸውን የይዘትተገቢነት መፈተሽ ዋና ተግባር ላይ የተወሰነ ነው።

1.5 ቁልፍ ቃላት

በዚህ ንኡስ ክፍል ውስጥ በዚህ ጥናት ውስጥ አንዳንድ ቁልፍ የሆኑ ቃላት አገልግሎት ላይ የዋሉበትን ትርጉም ቀርቧል።

1. ይዘት - በመማሪያ መፅሐፍ እና በፈተና ውስጥ የሚገኙ የቋንቋ ትምህርት አካላትን ማለትም የንግግር፣ የማዳመጥ፣ የንባብና የመጻፍ ክሂልን እንዲሁም የስነ- ፅሁፍ፣ የስነ- ልሳንና የቃላት ትምህርትን የተመለከቱ ርእሰ ጉዳዮችን የሚመለከት ነው።
2. ተገቢነት- አንድ ፈተና ቀድሞ የታቀደለትን አላማ ከግብ ማድረስ በሚያስችለው ሁኔታ መቅረቡን የሚመለከት ነው።
3. የይዘት ተገቢነት- አንድ ፈተና መፈተን ያለበትን ይዘት በትክክል አሟልቶ በመገኘት መፈተን መቻሉን የሚያመለክት ነው።
4. ትምህርት ቤት አቀፍ ፈተና- በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ በሚገኙ መምህራን የተዘጋጀና በትምህርት ቤቱ መደበኛ የሆነ የፈተና መርሀ- ግብር ተዘጋጅቶለት የሚሰጥ የችሎታ መለክያ ፈተና ሲሆን የሰሚስቴር አጋማሽ፣ የሰሚስተር ማጠቃለያና ሞዴል ፈተናን ያጠቃልላል።
5. የስነድ ምርመራ- አንድን የትምህርት መሳሪያ (የመማሪያ መጽሐፍ፣ ፈተና) አስፈላጊ መረጃ ለማውጣት ወይም ከተቀመጠ አንድ መስፈርት አንጻር ለመገምገም ፍተሻ ማካሄድ.

6. ተመጣጣኝ ውክልና- አንድ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ ይዘት በፈተና ላይ የሚሰጠው ሽፋን ቀድሞ በመማሪያ መፅሐፉ ከተሰጠው ሽፋን አንጻራዊ በሆነ መልኩ ተቀራራቢነት እንዲኖረው ማድረግን የሚመለከት ነው።

1.6 ሙዳየ ቃላት

በፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ (Table of Specification)፡- በፈተና ውስጥ መካተት የሚገባቸው ይዘቶች መጠንና አይነት ከትምህርቱ አጠቃላይ ይዘትና አላማ አንጻር በመወሰን የፈተና ይዘቶች በመጠንና በአይነት ተቀምጠው ለምናመለክትበት ሰንጠረዥ የተሰጠ ስያሜ ነው።

ተተኳሪ ችሎታን የማሳየት ተገቢነት (Construct Validity)፡- አንድ ፈተና አስቀድሞ የተቀመጠውን አላማ ወይም ለመለካት የተፈለገውን ችሎታ በትክክል የማሳየት ብቃቱን ለመገምገም የምንጠቀምበት መስፈርት ለመግለጽ የተሰጠ ስያሜ ነው።

መስፈርት አመላካች ተገቢነት (Criterion reference validity)፡- አንድ ፈተና ቀድሞ ከነበረው ወይም አንድ ደረጃውን ከጠበቀ ፈተና አንፃር ያለውን የትክክለኛነት ደረጃ ለምንለካበት መስፈርት የተሰጠ ስያሜ ነው።

1.7 አህፅሮተ ቃል

- ሽሬ ሁ/ደ/ት/ቤት - ሽሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- እ/ጉና ሁ/ደ/ት/ቤት - እንዳባጉና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ዓ/ዳ/ሁ/ደ/ት/ቤት - ዓዲ ዳዕሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ዓ/ም - ዓመተ ምህረት

ምዕራፍ ሁለት:-የተዛማጅ ፅሑፎች ቅኝት

2.1 የፈተና ምንነትና አስፈላጊነት

የግምገማና ምዘና ሂደት በትምህርት ቤቶች ከሚካሄዱ ተግባራት መካከል የሚጠቀስ አንድ ዋና ተግባር ነው። ትምህርታዊ የግምገማና የምዘና ሂደት ስለ ተማሪዎች የመማር ሂደትና ውጤት መረጃ ከመስጠት ባሻገር የትምህርት ቤቱ አጠቃላይ የስራ ክንውን በተመለከተ ጠቃሚ መረጃ የሚሰጥ በመሆኑ ሆን ተብሎ የሚከናወን አይቀሬ ተግባር ነው። ትምህርታዊ ግምገማና ምዘና ለማከናወን ከሚያስችሉ መሳሪያዎች መካከል አንዱ ደግሞ ፈተና ነው (Desalegn and Girma 2009:22)።

Cronbach (1970:102) ፈተና አብዛኛው ጊዜ በአንድ ውሱን መርሀ ግብር ለተሰበሰቡት ግለሰቦች የሚቀርብ ፣ የመርሀ ግብሩ አላማዎችን መሰረት አድርገው የተቀረፁ ጥያቄዎች ስብስብ ነው በማለት ገልጸዋል። ይህም ከትምህርታዊ መርሀ ግብር አንጻር ሲታይ ፈተና በመማር ማስተማር መርሀ ግብር ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ተማሪዎች የትምህርት መርሀ ግብሩ በትምህርቱ መጨረሻ በተማሪዎቹ ላይ ሊታይ የተፈለገው ባህሪ መታየት አለመታየቱን ለመፈተሽ የሚያስችሉ ጥያቄዎች ስብስብ ነው ማለት እንችላለን።

Gronulonad (1981:2) በበኩላቸው ‹‹ፈተና ተማሪዎች ቀደም ሲል የተቀመጡ ዝርዝር የትምህርት አላማዎች ምን ያህል ከግብ መድረስ መቻላቸውን ለመለካት የምንጠቀምበት ስርአታዊ መሳሪያ ነው›› በማለት ይበይኑታል። Harrison (1983:1) እና Alderson et al (1995:1) ፈተና ማለት ተማሪዎች በተማሩት ትምህርት ዙሪያ የተገነዘቡትን ዕውቀት ለመለካት፣ ከአንድ የክፍል ደረጃ ወደሚቀጥለው ደረጃ የሚሸጋገሩበትን ሁኔታ ለመወሰን፣ ለአንድ ሥራ ብቁ የሆነ ሰው ለይቶ ለመምረጥ እንዲሁም አንድ ሰው በአንድ ጉዳይ ላይ ያለውን የዕውቀት ደረጃ ለመመዘን የሚያገለግል መሳርያ ነው በማለት ይገልፁታል።

Ur (1996:33) ም እንዲሁ ‹‹ፈተና ተቀዳሚ ዓላማው ተፈታኙ አንድን ነገር ምን ያህል እንደሚያውቀው ወይም ተግባራዊ እንደሚያደርገው ለመረዳት የሚያገለግል ክንውን ነው›› በማለት በይነውታል። ይህም ፈተና አንድ ሰው ምን እንደሚያውቅ ወይም አንድን ነገር እንዴት እንደሚፈጽም፣ ምን እንደሚፈልግ ወዘተ. በተመለከተ መረጃ የምንሰበሰብበት መሣሪያ መሆኑን የሚያስረዳ ነው። በሌላ በኩል ፈተና ዘርፈ ብዙ በሆኑ ጉዳዮች (ማህበራዊ ፣ አስተዳደራዊ ፣ ትምህርታዊ ወዘተ) ለሚሰጠው ውሳኔ እና ለሚወሰደው እርምጃ በመረጃ ምንጭነት የሚያገለግል መሳሪያ መሆኑን Gronulonad (1981:3) ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ ፈተና በመማር ማስተማር ሂደት በተግባር ሲመነዘሩ የነበሩ የትምህርት አላማዎች ከግብ መድረስ አለመድረሳቸው ወይም በትምህርት መርሀ ግብሩ መጨረሻ በተማሪዎች ላይ ሊታዩ የተፈለጉት ለውጦች መታየት አለመታየታቸው በመፈተሽ መረጃ የሚሰበሰብበት መሳሪያ ነው።

Desalegn and Girma (2009:11) እንደሚገልጹት ፈተና ከሚከተሉት ጉዳዮች አንጻር እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳሉ።

➢ **ትምህርታዊ ውሳኔዎችን ለመስጠት**

በሂደት ላይ ያለው የመማር ማስተማር ተግባር ያቀዳቸውን አለማዎች ከማሳካት አንጻር በትምህርቱ ይዘት ፣ አቀራረብ ወይም በስነ- ዘዴው ረገድ ሊደረጉ የሚገባቸውን ማሻሻያና ለውጦችን በተመለከተ ውሳኔ ለመስጠት ፈተና አስፈላጊነቱ የላቀ ነው።

➢ **አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ለመስጠት**

በአስተዳደራዊ ውሳኔዎች ውስጥ የሚካተቱት የመረጣ (Selection) ፣ የክልሰፋ (Classification) እና የምደባ (Placement) ተግባራት ናቸው። በመሆኑም አንድ ተቋም በቀረጸው መርሀ ግብር ውጤታማና ተጠቃሚ ሊሆን የሚችል ተማሪ ለመምረጥ እና በየደረጃው በሚገኙ የተለያዩ የመርሀ ግብር አይነቶች ለመከፋፈልና ለመመደብ የፈተና ውጤት በመረጃ ምንጭነት መጠቀም ግድ ይላል።

➢ **ኃላፊነትን ለመወጣት እና መርሀ ግብሩን ለመገምገም**

ትምህርት ቤቶች በተማሪዎች ዘንድ የባህሪ ለውጥ ለማምጣት በማህብረሰቡ የተጣለባቸው ኃላፊነት ለመወጣት ፈተና ፈትነው ውጤቱን ማየት ይጠበቅባቸዋል። በተጨማሪም በመተግበር ላይ ያለውን የትምህርት መርሀ ግብር በቀጣይነት በመገምገም

የማህብረሰቡን ወቅታዊና ቀዳሚ ፍላጎቶችን በማገናዘብ የማሻሻያና የለውጥ ውሳኔ ለመስጠት ከፈተና የሚገኝ መረጃ ያስፈልጋል።

➢ **የምክር አገልግት ለመስጠት**

የተማሪዎችን ስነ ልቦናዊ ጉዳት ለመጠገንና ጠንካራና ደካማ ጎኖቻቸውን በመለየት የሚያሻሽሉበት ፣ ዝንባሌያቸውን የሚለዩበትና የሚያጠናክሩበት መንገድ ለመጠቆምና ድጋፍ ለመስጠት ከፈተና የሚገኘው መረጃ ወሳኝ ነው (Desalegn and Girma 2009:15)።

ከዚህ በተጨማሪም ፈተና በመማር ማስተማር ሂደቱ ዋነኛ ተዋናዮች ለሆኑት መምህራንና ተማሪዎች የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ያሉት በመሆኑ እጅግ አስፈላጊ ነው። እነሱም፡-

- ተተግባሪና ግልጽ የሆኑ አላማዎችን ለማስቀመጥ፣
- የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ጎን ለመለየት፣
- የተቀመጡ ዝርዝር አላማዎች ምን ያህል ከግብ እንደደረሱ ለመገምገም፣
- የምዘና ስልቶችን ለመምረጥና ለመወሰን፣
- በተማሪዎች ላይ የመማርና የማንበብ ተነሳሽነት ለመፍጠር፣
- ከትምህርቱ አላማዎችና ስልተ ትግበራዎች በብቃት ለመግባባት ያስችላል (Desalegn and Girma 2009:15)።

2.2 የጥሩ ፈተና መገለጫ ባህርያት

ፈተና የታለመለትን ጥሩ መለኪያና ትክክለኛ መረጃ አመንጪ የመሆን አላማ ከግብ እንዲያደርስ ከተፈለገ ማሟላት የሚገባቸው ባህርያት አሟልቶ መገኘት አለበት። ቀደም ሲል ሲገለፅ እንደነበረው ፈተና የተማሪዎችን የዕውቀትና ክህሎት ደረጃ የሚፈረጅበት፣ የአስተማሪው ዕውቀትና ችሎታ የሚገለፅበትና አጠቃላይ የመማር ማስተማር ሂደቱ ጥንካሬና ድክመት የሚወሰንበት መረጃ ነው። በመሆኑም ይህን ከባድ ውሳኔ ለመስጠት እንደ ዋነኛ መሳርያ የምንገለገልበት ፈተና ከዝግጅቱ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ውጤት ዘገባ ድረስ ያለውን ሂደት በትክክልና በጥንቃቄ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል።

አንድ ፈተና ጥሩ የመመዘኛ መሳሪያ ነው ተብሎ እንዲፈረጅ የሚያስችሉት በርካታ መገለጫ ባህርያት እንዳሉት ምሁራን ይገልፃሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ ባህርያት በተወሰኑና መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ማጠቃለል እንደሚቻል ምሁራኑ የሚስማሙበት ጉዳይ ነው። Grand man and Reed (1997:200) የተለያዩ የመስኩ ምሁራንን በመጥቀስ እንደሚገልፁት የፈተና ባለሙያዎች ብዙ ጊዜ የጥሩ ፈተና መገለጫ ባህርያት በማለት የሚገልጽዋቸውና በአብዛኞቹ ምሁራን ዘንድ የሚጠቀሱት አስተማማኝነት (Reliability)፣ ተተግባሪነት (Practicability) እና ተገቢነት (validity) የተባሉት ባህርያት ናቸው። በመሆኑም አንድ ፈተና በብቃት የተዘጋጀና ጥሩ ፈተና ነው ለመባል እነዚህን መሰረታዊ ባህርያት አሟልቶ መገኘት ይኖርበታል። ከዚህ በመቀጠል የሁለቱም መገለጫ ባህርያት በተወሰነ መልኩ፣ የሶስተኛውና የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የሆነው ባህሪ ደግሞ በዝርዝር ለመመልከት ይሞክራል።

2.2.1 አስተማማኝነት (Reliability)

Hughes (1989:37) ስለፈተና አስተማማኝነት አስመልክተው የሚከተለውን ሐሳብ አስፍረዋል።

> *አንድ ፈተና ተአማኒነት አለው የሚባለው አንድ ተፈታኝ አንድ ፈተና በሰአት ልዩነትም ይሁን በተለያዩ ቀናት ያንኑ ፈተና እንደገና ቢፈተን ከሞላ ጎደል ተቀራራቢ ውጤት ማምጣት የቻለ እንደሆነ ነው። በተቃራኒው ፈተናው አስተማማኝነት የለውም የምንለው ተፈታኙ አንድ ፈተና እንደሚፈተንበት የጊዜ ልዩነት አኳያ ውጤቱም እንዲሁ የሚለዋወጥ ሲሆን ነው።*

በተመሳሳይ ሁኔታ Weir (1990:20)ና Brown (1996:35) ሲገልፁ ‹‹አስተማማኝነት ተማሪዎች በአንድ ውቅት አንድ ፈተና ተፈትነው የሚያገኙት ውጤት በትክክልና በተደጋጋሚነት የራሳቸውን ዕውቀትና ችሎታ የማረጋገጥ ብቃት ነው›› ብለዋል። ይህን ሐሳብ በማጠናከር Heaton (1990:6)፣ Cohen (191:996) እና Grand man and Reed (1997:200) ሲያስረዱ፣ አስተማማኝነት አንድ ፈተና በተለያየ ጊዜ በተደጋጋሚ ለአንድ ግለሰብ በሚሰጥበት ጊዜ ተመሳሳይ ውጤት ማስመዝገቡን የሚያመለክት ነው ብለዋል። Harrison (1983:10) እና Brown (1994:253) የተባሉት ምሁራንም በአንድ የትምህርት አይነት ውስጥ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ፈተናዎች በተለያዩ ጊዜያት ሲቀርቡ በተፈታኞች ውጤት ላይ ሰፊ ልዩነት ከሌለና ተመሳሳይነት ከታየ ፈተናው አስተማማኝነት ያለው ነው ማለት እንደሚያስችለን ገልፀዋል።

2.2.2 ተተግባሪነት (Practicability)

ተተግባሪነት አንድ ፈተና ሊያሟላቸው ከሚገቡ መሰረታዊ ባህርያት መካከል የሚጠቀስ ሲሆን፣ ይህም ፈተናው በታቀደለት ጊዜና ቦታ በታሰበው መልኩ ከተፈታኞች እጅ ደርሶ በሚመለከተው ክፍል ታርሞና ውጤቱ ተመዝግቦ የተፈለገውን መረጃ መስጠት ከሚችልበት ደረጃ ሊደርስ የሚችል ስለመሆኑ የሚመለከት ጉዳይ ነው። ይህን በማስመልከት Brown (1994:253) ፣ Weir (1990:25) እና Hughes (1989:152) ሲገልፁ ተተግባሪነት አንድ ፈተና ለክንውኑ ከሚወጣለት ወጪ፣ ከሚያስፈልገው የሰው ኃይል ፣ የመፈተኛ ክፍሎች፣ ከጊዜና ሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮች አንፃር ያለምንም ችግር ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል መሆኑን የሚመለከት ነው ብለዋል።

የአንድን ፈተና ተተግባሪነት ከሚፈታተኑ ነገሮች መካከል የተማሪዎች ቁጥርና የፈተና ቦታዎች አለመጣጣም፣ ግልፅ መመሪያዎች አለመኖር፣ በቂ የሆነ ጊዜ አለመመደብና የሚቀርቡ አማራጮችም ወጥነት ያላቸው አለመሆን የሚጠቀሱ ናቸው በማለት Heaton (1975:158) ይገልፃሉ።

ስለዚህ የአንድን ፈተና ተተግባሪነት ሊያደናቅፉ የሚችሉ ጉዳዮች ከመጀመሪያው ታስቦባቸው እንዲወገዱ ካልተደረገ በፈተና ሂደትና ውጤት የሚያስከትለው ችግር ከፍተኛ መሆኑ መገመት አያዳግትም። ተተግባሪነቱ የተረጋገጠ ፈተና ለማዘጋጀት በቅድሚያ በተጨባጭ ያሉት ነገሮች እና እጥረቶች ለይቶ በማውጣት የፈተና ሂደት ፅቅድ በጥራት ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

2.2.3 ተገቢነት (Validity)

2.2.3.1 የተገቢነት ምንነት

በትምህርታዊ ግምገማና ምዘና ጥናት ዘርፍ ላይ የተሰማሩት ምሁራን እንደሚያስረዱት አንድ ፈተና በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጀና ማሰገኘት ያለበትን ትምህርታዊ መረጃ በትክክል የመያዝ ብቃት ያለው መሣርያ ተብሎ እንዲፈረጅ ከሚያስችሉት መሰረታዊ ባህርያት በቀዳሚነት የሚጠቀሰው የተገቢነት ባህሪ ነው። American Psychological Association (1985:9)ን በመጥቀስ Bachman (1990:243) እንደገለፁት ተገቢነት በፈተና ውጤት ላይ በሚመሰረተው አንድምታ ወይም አጠቃቀም እና በፈተናው

መካከል ያለውን ይሁንታዊ ግኑኝነት ወይም ትክክል መሆን አለመሆኑን የሚፈረጅበትና የሚረጋገጥበት መንገድ በመሆኑ ተገቢነት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው በማለት ምክንያቱን ያስረዳሉ። ይህም ተገቢነት የፈተና ውጤት ጥቅም ላይ እንዲውል ውሳኔ የሚሰጥበት ባህሪ መሆኑን ያመለክታል።

Henning (1987:89) ሲገልፁ ተገቢነት በአጠቃላይ ሲታይ አንድ ፈተና ለመፈተን ያሰበውን አላማ መሰረት አድርጎ ሲዘጋጅና አስቀድሞ ካስቀመጣቸው ባህሪያት ጋር ተስማሚ ሆኖ መገኘቱን የሚያመለክት ነው ብለዋል። በማንኛውም ደረጃ የሚዘጋጅ ፈተና ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ጥያቄ ለሁሉም የፈተና አዘጋጆች የማይቀር ጥያቄ ነው። ይህ የሚሆንበት ምክንያትም Alderson et al (1995:170) እንደሚሉት አንድ ፈተና ከተዘጋጀበት ዓላማ አንጻር ተገቢነት ያለው ሆኖ ካልተገኘ ከፈተናው ይገኛል ተብሎ የሚጠበቀውን መረጃ ማግኘት አይቻልምና ነው።

በተመሳሳይ መልኩ Heaton (1990:7) Brown (1994:254) Grand man and Reed (1997:210) Harrison (1983:11)እና Hughes(1989:22) የተባሉ ምሁራን ተገቢነት አንድ ፈተና መለካት ያለበትን ዕውቀትና ችሎታ በትክክል መለካት የሚችልበትን ብቃት ያለው መሆኑንና አለመሆኑን የሚያመለክት ባህሪ ነው በሚለው ብያኔ ይስማማሉ።

ይሽውም ፈተናው ያካተታቸው ጥያቄዎች በመርሀ ትምህርቱ የተቀመጡ የትምህርት አላማዎችን በተገቢ ሁኔታ የሚያመለክቱ፣ በመማርያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች በትክክል የሚወክሉ፣ የተፈታኞችን አካዳሚያዊ ብቃትን በአግባቡ መመዘን የሚችሉ በአጠቃላይ መሰረታዊ የፈተና አዘጋጃጀት መርሆችን ተከትለው የቀረቡ መሆን እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው።

ይህ እንዳለ ሆኖ Gronulonad (1981:66) እንደሚገልፁት ተገቢነት ከፈተና አንጻር ሲታይ የሚከተሉት ባህሪያት አሉት።

- ተገቢነት በደረጃ የሚቀመጥ እንጂ ፍፁማዊ አይደለም። ምሁሩ እንደሚያስረዱት በማንኛውም ጊዜ ፍፁም የሆነ ወይም እንከን የሌለው ነገር ማግኘት እንደማይቻልና ሁሉም የፈተና ውጤቶች ተገቢ ወይም አ- ተገቢ የሆነ በማለት

የምንፈርጃቸው አይደሉም። ይልቁስ የፈተና ውጤቶችም በደረጃዎች በማስቀመጥ ከፍተኛ ተገቢነት፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ ተገቢነት ያለው በማለት መፈረጅ ይኖርብናል።

- ተገቢነት ምንግዜም ቢሆን ለአንድ ተግባር ብቻ የተወሰነ ነው። ይህም ማለት ተገቢነትን እንደ አንድ አጠቃላይ ብቃት ወይም የጥራት ደረጃ በመውሰድ ለሁሉም ጉዳዮች የሚውል ሳይሆን ከአንድ ውስን ተግባር አንጻር ታይቶ የሚሰጥ ነገር ነው (Gronulonad1981:66)። ለምሳሌ አንድ የድርሰት ፈተና ውጤት ሥነ- ጽሁፋዊ ዕውቀትን ከመለካት አንጻር ከፍተኛ ተገቢነት ሊኖው ይችላል። በአንጻሩ ደግሞ ሥነ- ልሳናዊ ዕውቀት ከማሳየት አንጻር ዝቅተኛ ተገቢነት ሊኖረው ይችላል። ስለዚህ የአንድ ፈተና ተገቢነት የሚታየው መለካት ከተፈለገው ጉዳይ አንጻር ያለው የስምምነት ደረጃን በመመልከት ነው።

በአጠቃለይ የፈተና ተገቢነት የምንለው ፈተናው ከጅምሩ የተዘጋጀለትን አላማ ወይም ፈተናውን ለማዘጋጀት ያስፈለገበትን ምክንያት፣ በፈተና መዳሰስ የተፈለጉትን የትኩረት ነጥቦችን አሟልቶ መቅረብ አለመቅረቡን የሚመለከት የፈተና ትክክለኛነት ማረጋገጫና መፈተሻ መስፈርት ነው።

2.2.3.2 የተገቢነት አይነቶች

Bachman (1990:243) እንደሚገልፁት የአንድ ፈተና ውጤት አተረጓጎምና አጠቃቀም ተገቢነትነትን ለመፈተሽ በአንድምታው ወይም በውጤቱ አጠቃቀምና በፈተናው መካከል ያለውን ግኑኝነት የሚደግፉ መረጃዎችን የመሰብሰብ ስራን የሚጠይቅ ሂደት ነው። የምንሰበስባቸው መረጃዎች ደግሞ በሶስት አበይት ቡድኖች የተከፈሉ ናቸው። እነዚህም የይዘት ተገቢነት (Content Validity) የመስፈርት አመልካች ተገቢነት (Criterion reference validity) እና ተተኳሪ ችሎታን የማሳየት ተገቢነት (Construct validity) ናቸው።

Bachman እንደሚገልፁት እነዚህ ሶስት ጉዳዮች በተናጠል የሚጠሩ ቢሆኑም እርስበርስ የተያያዙና ተገቢነትን በማረጋገጥ ሂደት ላይ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ናቸው። ከዚህ በመቀጠል የይዘት ተገቢነትን በዝርዝር ሌሎች ደግሞ በአጭሩ እንመለከታለን።

- **መስፈርት አመላካች ተገቢነት** (Criterion reference validity)

በዚህ የተገቢነት አይነት መሰረት የአንድን ፈተና ተገቢነት የሚመዝንና እንደ አንድ መስፈርት ሆኖ የሚያገለግል በነባና ገለልተኛ አካል የተዘጋጀ ወይም የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ፈተና ይኖራል። ይህ እንደ መስፈርት ሆኖ የሚያገለግለው ፈተና ለፈተና የቀረበው ተማሪ ሊኖረው የሚገባውን የዕውቀትና ክህሎት ደረጃ በትክክልና በከፍተኛ ደረጃ ማንፀባረቅ የሚችል ነው ተብሎ የሚታመን ነው (Hughes 1989:23)።

እንደ ባለሙያው አገላለፅ ከዚህ አይነቱ የተገቢነት ማረጋገጫ መሳሪያ የሚሰበሰበው መረጃ ለተማሪዎች የቀረበውን ፈተና እንደ መስፈርት ተደርጎ ከተወሰደው ፈተና ጋር ያለው ተቀራራቢነት ምን ደረጃ ላይ መሆኑን በተመለከተ ነው። በዚህም መሰረት ፈተናው ከፍተኛ፣ መካከለኛ አልያም ዝቅተኛ ተገቢነት ያለው በማለት ይፈረጃል። Gronulonad (1981:72) እና Hughes (1989:25) ደግሞ የመስፈርት አመላካች ተገቢነት ላይ የምንመለከተው ይህ ብቻ ሳይሆን ፈተናው የተማሪዎችን ቀጣይ ብቃት ከማሳየት ረገድ ያውን ደረጃም የምንገመግምበትም ጭምር ነው ብለዋል።

በአጠቃላይ የመስፈርት አመልካች ተገቢነት የቀረበው ፈተና ከሌሎች ተገቢነት ያላቸው ፈተናዎች ጋር ያለውን ተቀራራቢነትና የተማሪዎች ቀጣይ ብቃት ከማሳየት ረገድ ያለውን ደረጃ የምንለካበትና መረጃውንም የምናገኝበት ነው።

- **ተተኳሪ ችሎታን የማሳየት ተገቢነት** (Construct validity)

ይህንን የተገቢነት አይነት አስመልክተው Hughes (1989:26) ሲገልፁ፣ ‹‹አንድ ፈተና አስቀድሞ ያስቀመጠውንና ሊለካው የፈለገውን ባህሪ ወይም ያተኮረበት ችሎታ በፈተናው ጥያቄዎች ላይ መንፀባረቁን የሚመለከት ነው›› ብለዋል።

Gronulonad (1981:93) ደግሞ የሚከተለውን ሀሳብ ይሰጣሉ፡-

> *... ተተኳሪ ችሎታን የማሳየት ተገቢነት የሚባለው የተገቢነት አይነት ግን በጣም ውስንና ክወዲያውኑ(ወቅታዊ) የፈተና አገልግሎት ጋር የተዛመደ ነው። ይህም የተማሪዎችን ባህሪ በተመለከተ በጣም ሰፊና ለብዙ የተለያዩ ጉዳዮች የሚውል መረጃ የሚያስገኝ ነው። ተተኳሪ ችሎታን የማሳየት ተገቢነት የፈተናን ብቃት ካለው ሰነ አዕምሯዊ ዋጋ አንጻር የሚመለከት ነው። ለምሳሌ ፈተናው የተማሪዎችን የአመክንዮት ችሎታ (reasoning ability) ያካተተ ከሆነ በተተኳሪ ችሎታን የማሳየት ተገቢነት አንድ ተግባር እንዳከናወነ ይቆጠራል። ስለዚህ ተተኳሪ ችሎታን የማሳየት ተገቢነት የአንድ ፈተና ብቃት ከተወሰነ ሰነ አዕምሯዊ ተግባራት አንፃር የመመልከትና የመተግበር ሂደት ነው ተብሎ ብያኔ ሊሰጠው ይችላል።*

እኚህ ምሁር እንደሚገልፁት ከሆነ አንድ ፈተና ተተኳሪ ችሎታን የማሳየት ተገቢነት አለው የሚባለው የተማሪዎችን አዕምሮ የማሰራት ብቃት ያላቸው የፈተና ጥያቄዎችን (Test items) ይዞ መገኘት ሲችል ነው። እነዚህም ደግሞ ከጅምሩ በትምህርቱ መነሻ እንደ ግብ ተደርገው የተቀመጡትን የትምህርት ውጤቶች የሚንፀባረቅባቸው ተግባራት ማለት ናቸው።

Hughes (1989:26) በበኩላቸው ‹‹አንድ ፈተና ተተኳሪ ችሎታን የማሳየት ተገቢነት አለው የሚባለው አስቀድሞ በፈተናው አማካኝነት ለመለካት የታሰበውን ችሎታ ለተፈተኞች በማቀርበው ፈተና ላይ ተካትቶ የተፈታኞች ምላሽም በታየበት ወቅት ነው›› ብለዋል። ይህም በምሳሌ ሲያስረዱ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመለካት ታስቦ በተዘጋጀ ፈተና ውስጥ የአንብቦ መረዳት ችሎታን በሚያመለክቱ ንኡሳን ክሂሎች አማካኝነት የተቀመጡ ጥያቄዎች ሊኖሩበት ይገባል ይላሉ። በአጠቃላይ ከምሁራን ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው ተተኳሪ ችሎታን የማሳየት ተገቢነት ፈተናው የተማሪዎችን አቅም ከመገንባት ረገድ የሚኖረው ሚና ምን ያህል መሆኑና ይህም ቀድሞ ከተቀመጠውና ሊለካ ከተፈለገው ችሎታ ጋር የሚሰማማ ስለመሆኑ የሚፈተሽበት ነው። ከዚህ በመቀጠል የጥናቱ ዋና የትኩረት ነጥብ የሆነውን የይዘት ተገቢነት በተመለከተ የምሁራንን ሀሳብ ለመቃኘት ይሞክራል።

- የይዘት ተገቢነት (content validity)

የይዘት ተገቢነት ቀደም ሲል ካየናቸው የተገቢነት አይነቶች ጋር በመሆን የአንድን ፈተና ትክክለኛነት፣ ትርጉም ሰጪነትና ጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል መረጃ የተሸከመ የተገቢነት አካል ነው። የይዘት ተገቢነት በፈተና ላይ ለሚደረጉ ማናቸውም ትንታኔና ግምገማ እንደ ቁልፍና መሰረታዊ ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ደግሞ ይዘት የሌለው ፈተና ባለመኖሩና የፈተና ውጤቱም ሆነ ፈተናው መሰረት የሚያደርጉት ይህንኑ ይዘት በመሆኑ ነው።

Bachman (1990:244) የይዘት ተገቢነት በሚተነትን ጽሁፋቸው በፈተና ተገልጋዮች እንደ መሆናችን መጠን በቀዳሚነት ልንገነዘበውና ልንተገብረው የሚገባን የፈተና ባህሪ የይዘት ተገቢነትን ነው በማለት ገልፀዋል። የይዘት ተገቢነት አንድ ፈተና

ለትምህርትነት ከቀረበው ይዘት ጋር ያለውን ጥብቅ ቁርኝነት የሚመለከት ሲሆን ይህ ከተዘነጋም ፈተናው የታለመለትን ዓላማ ማሳካት እንደማይቻለው Brown (1994:254) ይገልፃሉ። በመሆኑም አንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት ደረጃውን ጠብቆ መዘጋጀት አለበት።

2.3 የቋንቋ ፈተና ምንነት፣ አላማና አስፈላጊነት

በዚህ የተዛማጅ ዕሑፎች ቅኝት ንኡስ ክፍል ውስጥ ስለ ቋንቋ ፈተና ምንነት፣ ዓላማና አስፈላጊነት ለማየት ተሞክሯል። በዚህም መሰረት፣ የመስኩ ምሁራን ያነሱትን ሐሳብ ዋቢ በማድረግ በአጭሩ ለማቅረብ ተሞክሯል።

2.3.1 የቋንቋ ፈተና ምንነት

የቋንቋ ፈተና ተማሪዎች የተሰጣቸውን የቋንቋ ትምህርት ምን ያህሉን እንደጨበጡና የማወቅ ችሎታቸውም ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መረጃ የሚሰበሰብበት መሣርያ ነው። Mehrens and Lehmann (1974:3) እንደገለጹት የቋንቋ ፈተና ተማሪዎች የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን እንዲሁም የሥነ- ጽሑፍና የሥነ ልሳን ዕውቀቶችን ከመማራቸው በፊት ያላቸውን የቀደመ ዕውቀት ለመገምገም ወይም ከተማሩ በኋላ የቋንቋ ችሎታቸውን ለመለካትና ለማሻሻልና ምን ያህል ለውጥ እንዳመጡ ለመረዳት የምንገለገልበት የመመዘኛ መሣሪያ ነው። ይህም የቋንቋ ፈተና የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ከቋንቋ ትምህርት በፊት ወይም በኋላ ምን እንደሚመስል ለመለካት አገልግሎት ላይ የሚውለው የአራቱን የቋንቋ ክሂሎችንና ሁለቱን የቋንቋ ዕውቀቶች ይዘት ስብስብ የሆነና በስርአት ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የመረጃ ማግኛ ስልት መሆኑን ነው።

Ur (1996:33) እንደሚገልፁት ደግሞ ፈተና በአጠቃላይ አንድ መምህር የተማሪዎችን ችሎታ ወይም ዕውቀት ያለ አድልዎ መሰረታዊና ትክክለኛና በማያሻማ መንገድ በአህዝ የሚገልፅበት መሳርያ ነው። ከዚህ ገለፃ አንድ የቋንቋ መምህር ስለተማሪዎቹ የቋንቋ ችሎታ ወይም ዕውቀት ሚዛናዊና ትክክለኛ የሆነ መረጃ የሚያገኝበት መሳሪያ የቋንቋ ፈተና መሆኑን መረዳት ይቻላል።

Genesee and Upsher (1996:154) ደግሞ ‹‹ የቋንቋ ፈተና ስለ ቋንቋው ምንነት ወይም በቋንቋው አጠቃቀም ላይ ሊስተዋሉ የሚችሉ ምላሾችን የሚጠይቁ ተግባራትን አካቶ የያዘ ነው፡፡ ከምላሹ የሚገኘው ውጤትም የትምህርቱን ዓላማዎች መሰረት በማድረግ ይተነተናል›› በማለት ገልፀውታል፡፡ ከዚህ ገለፃ የቋንቋ ፈተና ስለቋንቋ ምንነት፣ በቋንቋው ስለ መገልገል (ማዳመጥ፣ መፃፍ፣ ማንበብና መናገር) ከክሂሎች እንዲሁም (ሥነ- ልሳንና ስነ- ዕሑፍ) ከዕውቀት ዘርፎች የተውጣጡ ጥያቄዎችን ይዞ ሊዘጋጅ የሚችል መሣሪያ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በለጠ (1995፡6) በድሩ ከድር (1994፡3) ን በመጥቀስ እንደገለፁት የቋንቋ ፈተና ተማሪዎች ከተማሩት መማርያ መፅሐፍ ውስጥ ምን ያህሉን እንደጨበጡ ለማረጋገጥ የሚረዱና በናሙናነት የተወሰዱ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ስብስብ ነው፡፡ ይህ ብያኔ የቋንቋ ፈተና ከማስተማሪያው መጽሐፍ ጋር ያለው ግንኙነት የሚያሳይ ሲሆን የቋንቋ ፈተና ተማሪዎች የቀረበላቸውን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘቡት ለማወቅ የሚረዳ የመገምገምያ መሳሪያ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በአጠቃላይ የቋንቋ ፈተና ምንነትን በተመለከተ የሰፈሩት ፅንሰ ሐሳቦች እንደሚያስረዱት፣ የቋንቋ ፈተና በቋንቋ ትምህርት ወቅት በሚካሄዱ መስተጋብሮች አማካኝነት ተማሪዎች የጨበጧቸው የቋንቋ ክሂሎችና የቋንቋ ዕውቀቶች ላይ መሰረት በማድረግ የሚቀርብ የዕውቀትና ክህሎት መመዘኛ መሳሪያ መሆኑ ነው፡፡

2.3.2 የቋንቋ ፈተና አላማ

ቀደም ሲል እንደተገለፀው በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ፈተና እንደዋነኛ የትምህርት መሣሪያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ አንድ ፈተና ሲዘጋጅ ደግሞ የራሱ የሆነ ዓላማ ሊኖረው የግድ ነው፡፡ Heaton (1975:6) እንደሚገልፁት ‹‹አንድ ፈተና ለተወሰነ ዓላማ ይዘጋጃል፣ ዓላማው በግልፅ የተቀመጠ ካልሆነ ደግሞ ለመለካት የተፈለገውን ነገር ወይም የተፈለገውን መረጃ ማግኘት አይቻልም፡፡ በመሆኑም የቋንቋ ፈተና ሲዘጋጅ ቀደም ብለው የተቀመጡትና መረጃ ሊገኝባቸው የተፈለጉ አበይት የመማር ውጤቶችን ይዞ የሚነሳ ነው የሚሆነው››ብለዋል፡፡

እነዚህ የመማር ውጤቶች በተማሪዎች ላይ በግልጽ እንዲታይ የሚያስችሉና ወደ እነዚህ ውጤቶች የሚያመሩ ዝርዝር የትምህርት አላማዎችን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በቋንቋው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ናቸው። በመሆኑም እነዚህ በመማሪያ መጽሐፍ የተካተቱ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በተማሪዎች ዘንድ መያዝ አለመያዛቸው ማረጋገጥ የቋንቋ ትምህርቱ ከጅምሩ ያስቀመጣቸውና በስተመጨረሻ ይታያሉ ያላቸው የመማር ውጤቶችን ስኬታማነት ማረጋገጥ ማለት መሆኑን ከምሁሩ መረዳት ይቻላል።

Clark and Star (1996:378) የቋንቋ ፈተና ተማሪዎች ምን መማር እንዳለባቸውና ምን እንደተማሩ በመለየት ለመምህራን ምጋቤ ምላሽ በመስጠት፣ ተማሪዎች ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን እንዲለዩ በመርዳት ለበለጠ ሥራ እንዲተጉ በማነሳሳት እንዲሁም አጠቃላይ የመማር ማስተማር ሂደት በመገምገም የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ የሚያገለግል ትልቅ መሣርያ ነው። በተጨማሪም ፈተና ተማሪዎች እየተማሩ መሆናቸውና የሥራቸውን ውጤት ለመለየት፣ የትምህርት መርሃ ግብሩን በማጠናቀቅ ወደ ተከታዩ የክፍል ደረጃ መሸጋገር የሚገባቸውን ለመለየት ቁልፍ ሚና ይጫወታል።

በመሆኑም የቋንቋ ፈተና አላማ መምህራንና ተማሪዎችን በመገምገም አጠቃላይ የመማር ማስተማር ሂደቱ ጤናማ በማድረግ አስቀድመው የተነደፉትን የትምህርት አላማዎች ከግብ እንዲደርሱና ውጤታማ የትምህርት ሂደት እንዲኖር ማስቻል ነው። ስለዚህ ፈተና መምህራን የአሰራር ሂደታቸውን በመፈተሽ ውጤቱን የሚመዝኑበት ተማሪዎችም ያላቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት ለተሻለ ውጤት እንደመነቃቂያ የሚገለገሉበት ነው።

በአጠቃላይ የቋንቋ ፈተና እንደ ሌሎች የፈተና አይነቶች የራሱን ዓላማ መሰረት አድርጎ የሚዘጋጅ ሲሆን፣ ይኸውም ተማሪዎች በቀረበላቸው የቋንቋ ትምህርት አማካኝነት ያስመዘገቡትን ውጤት ምን ደረጃ ላይ እንደሆነ ለመፈተሽና የትምህርት ሂደቱን ለመገምገም ነው። ይህም መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች የአሰራር ሂደታቸውን በመገምገም፣ ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን በመለየት ቀጣይ ጉዟቸውን የተሻለና ስኬታማ ለማድረግ ጥሩ ምጋቤ ምላሽና ተነሳሽነትን የሚያገኙበት ነው።

2.3.3 የቋንቋ ፈተና አስፈላጊነት

ከፍ ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው የቋንቋ ትምህርት በአንድ የትምህርት መርሃ- ግብር ቀርቦ ሲሰጥ ከቆየ በኋላ የነበረው ሂደት ምን ይመስል እንደነበረ ለመገምገምና ምን ውጤት እንዳስገኘ ለማወቅ በአማዛኙ ከዝበት ወይም አድልዎ (bias) ነፃ በመሆነ መልኩ መረጃ የምናገኝበት መሣርያ የቋንቋው ፈተና ነው።

Bachman (1990:54) የቋንቋ ፈተና የሚከተሉት ሁለት ዋና ዋና ጠቀሜታዎች እንዳሉት በመግለፅ አስፈላጊነቱን ያስረዳሉ።

ሀ. በትምህርት መርሀ- ግብር ትግበራ አውድ ውስጥ ትምህርታዊና አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ለመስጠት እንደ መረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል።

ለ. በቋንቋ ፅንሰ ሀሳቦችና ትውረቶች አውድ ውስጥ ለቋንቋ ለመዳና ለቋንቋ ትምህርት ምርምር በሚያስፈልግበት ጊዜ ለችሎታ(ባህሪ)መለያ አመላካች ሆኖ ያገለግላል።

በአጠቃላይ ከምሁራኑ ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው የቋንቋ ፈተና የተማሪዎችን የቋንቋ ዕድገት ለውጥ ለማወቅ፣ ተማሪዎች ለማበረታታት፣ በትምህርት ጊዜ የሚያጋጠሙ ችግሮች ለመለየት፣ የተማሪዎች ችሎታ ለመፈተሽ፣ ተማሪዎችን በችሎታቸውና እንደያዝንባሌያቸው ለመመደብ እንዲሁም የተማሪዎች የዕውቀት ደረጃን ለመወሰን እጅግ አስፈላጊ መሆኑ ነው።

ስለዚህ የተማሪዎችን ትምህርት ለመገምገም ፣ የመምህራን የማስተማር ሒደት ለመፈተሽና የማስተካከያ እርምጃዎችን ወስዶ የቋንቋ ትምህርቱን ስኬታማና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ ፈተና እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው።

2.4 የቋንቋ ፈተና አይነቶች

የቋንቋ ፈተና በቋንቋ ትምህርት ሒደት ውስጥ ለተለያዩ አገልግሎት ሊውል ይችላል። ከዚህ የተነሳም የፈተናዎቹ ይዘትና አቀራረብም የተለያየ መልክ ሊኖረው ግድ ይላል። የተለያዩ ምሁራን የቋንቋ ፈተናን ከተለያየ መስፈርት አንፃር በመመልከት በአይነት በአይነት ይመድቧቸዋል።

Caroll (1980:74) የቋንቋ ፈተና የሚሰጥበትን ጊዜ መሰረት በማድረግ የቅድመ ትምህርት ፈተና (የቅድመ ችሎታ መለኪያ፣ ብቃት መወሰኛ) ፣ የትምህርት ጊዜ ፈተና (ለውጥን፣ ጥንካሬና ድክመት መለኪያ ወይም ሂደታዊ) እንዲሁም ድህረ ትምህርት ፈተና (ማጠቃለያ ፈተና ፣ ዕድገትን ማሳያ) በማለት ይከፍሉታል። Hughes (1989:10) እና Harrison (1983:9) ደግሞ የቋንቋ ፈተናን ከሚቀርቡበት አላማ አንፃር በመመልከት የቅድመ ችሎታ መለኪያ፣ የደረጃ መለኪያ ፣ የጥንካሬና ድክመት መለኪያ እና የችሎታ መለኪያ ፈተና በማለት በአራት ከፍለው ያስቀምጧቸዋል።

በአጠቃላይ የመስኩ ምሁራን የቋንቋ ፈተናን የተለያዩ መስፈርቶችን በመጠቀም በአይነት አይነት በመመደብ የተለያየ ሐሳብ ለመስጠት ሞክረዋል። ለፈተናዎች አይነት መብዛትና መለያየት በምክንያትነት የሚጠቀሰውም ፈተናዎቹ የሚቀርቡበት ዓላማና ጊዜ የተለያየ በመሆኑ ነው በማለት ምሁራኑ ያስረዳሉ። ይሁን እንጂ ከእያንዳንዱ መስፈርት አኳያ የጋሪ ባህርያትን በመለየት ለተፈለገው አላማ መጠቀም ተገቢ እንደሆነ ሊቃውንቱ ያስገነዝባሉ። በመሆኑም በዚህ ጥናት ትኩረት የተሰጠው የፈተና አይነትን ጨምሮ ሌሎች በዋናነት የሚጠቀሱ የፈተና አይነቶች ለመዳሰስ ተሞክራል።

2.4.1 የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና (Aptitude Test)

የቅድመ ችሎታ ፈተና ስሙ እንደሚመለክተው ተማሪዎች ገና ያልተማሩትን ትምህርት ወደፊት ቢማሩት ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉ እንደሆነ ለመፈተሽ የሚዘጋጅ የፈተና አይነት ነው። Heaton (1975:164) ፣ Harrison (1983:4) እና Hughes (1989:145) የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች የተማሩትን የቋንቋ ትምህርት ዕውቀት የሚለካ ሳይሆን ያላቸውን የተፈጥሮ ዕውቀትና ዝንባሌ ለመመዘን የሚያገለግል ነው በማለት ያብራራሉ። በተመሳሳይ መልኩ Brown (1994:285) "ይህ የፈተና አይነት የአንድን ግለሰብ አጠቃላይ ዕውቀት ወይም ብቃት ለማወቅ እና የወደፊቱን ሁኔታ ለመወሰን ይረዳ ዘንድ የሚዘጋጅ ፈተና ነው" በማለት ይገልፁታል።

ከዚህ በተጨማሪ Heaton (1990:11) የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና አንድ ትምህርት ለተፈታኞች ከመቅረቡ በፊት ተማሪዎችን እንደ ቋንቋ ችሎታቸውና ዕውቀታቸው በቡድን ለመመደብ የሚያስችል ነው። በዚህ የፈተና ዝግጅት ጊዜም በተቻለ መጠን

አጠቃላይ ይዘት ያላቸው ጉዳዮች ማካተት ተገቢ ነው ብለዋል። Hughes (1989:14) እንደሚገልፁት ደግሞ የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና ባልታቀደ ወይም ኢ- መደበኛ በሆነ መንገድ በተገኘ ግንዛቤ ላይ የሚመሰረት ፈተና ሲሆን ተማሪዎች በአንድ ጉዳይ ላይ ያላቸውን ዕውቀት የምንለካበት ነው።

2.4.2 የደረጃ መለኪያ ፈተና (Proficiency Test)

የደረጃ መለኪያ ፈተና በተፈታኞች መካከል ያለውን የውጤት ልዩነት ላይ የሚመሰረት ሳይሆን የአንድ ግለሰብ የዕውቀትና ብቃት ደረጃ የሚያሳይ ነው። Bachman (1990:71) እና Brown (1994:257) ሲገልፁ የደረጃ መለኪያ ፈተና ሲዘጋጅ መሰረት የሚያደርገው የቋንቋ ንድፈ ሀሳቦችን ሲሆን በዚህም ዋና ትኩረት የሚያደርገው በቋንቋ ይዘት ላይ ነው። ይኸውም የቀረበው ፈተና አጠቃላይ ወይም ሁለገብ የቋንቋ ችሎታ የሚጠይቁ ነጥቦችን ያካተተ ነው።

Weir (1990:6) እና Brown (1994:258) እንደሚገልፁት የደረጃ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች በአንድ የተወሰነ ዘርፍ ያላቸውን ችሎታ የሚያሳይ ሲሆን ዋና ተግባሩም በተገኘው ውጤት አማካኝነት ደረጃ መስጠት ነው።

ከተሰጡት ብያኔዎች መረዳት እንደሚቻለው የደረጃ መለኪያ ፈተና እና የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና ተቀራራቢነት ያላቸው ይመስላሉ። ይህን በተመለከተም Lado (1961፡78) እና Alderson (1988፡2) ሲያብራሩ የደረጃና የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ተፈታኞችን በአንድ የተወሰነ ምድብ ውስጥ ለመፈረጅ የሚያስችሉ በመሆናቸውና ከመደበኛ የትምህርት መርሀ ግብር በፊት ተመስርተው የሚዘጋጁ በመሆናቸው ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል ብለዋል። ይሁን እንጂ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ሁለቱም ለተለያየ ዓላማ የሚውሉ የተለያዩ የፈተና አይነቶች መሆናቸው ምሁራኑ ያስገነዝባሉ።

2.4.3 የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና (Diagnostic Test)

Bachman (1990:46) እንደሚገልፁት የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ብለን የምንፈርጀው የቋንቋ ፈተና መደበኛ ያልሆነ ፈተና ሲሆን መምህራን ለራሳቸው ክፍል ተማሪዎች በራሳቸው የሚያዘጋጇቸው ፈተናዎች ናቸው። ይህ ፈተናም የመምህራንና የተማሪዎች

እንዲሁም የትምህርት መሳሪያዎች ጥንካሬና ድክመት ምን እንደሆነ የሚያመለክት ነው።

Hughes (1989:13) እንደሚገልፁት ደግሞ የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና መምህራንና በተለያዩ ጊዜያት ለተማሪዎቻቸው የሚያቀርቡት ሲሆን ተማሪዎች በየትኛው የትምህርት ክፍል ላይ ተጨማሪ እገዛ እንደሚያስፈልጋቸው ለመለየት የሚዘጋጅ የፈተና አይነት መሆኑን ነው።

የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የታዩትን መሰናክሎች ለይቶ በማውጣት ጤናማና ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲፈጠር ትልቅ ፋይዳ ያለው ነው። ይህ አይነቱ ፈተና ትኩረት የሚያደርገው በተማሪዎች ላይ የሚታየውን የቋንቋ ችግርና ሌሎች ወቅታዊ ችግሮች በተከታታይ መፍትሔ በመስጠት ላይ ሲሆን ይህም ተገቢ የሆነ የማስተማሪያ ዘዴና መሳሪያ ለመለየት ወሳኝ ሚና ይጫወታል (Baker 1989:3 ፣ Harrison 1983:6 እና Brown 1994:259)።

በአጠቃላይ ከተሰጡት ብያኔዎች መረዳት እንደሚቻለው የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና በመማር ማስተማር ሂደት የሚፈጠሩ ችግሮችን በመለየት የቋንቋ ትምህርቱን በቅርበት የሚከታተልና ድጋፍ የሚሰጥ፣ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች በሂደት ላይ ያለውን ትምህርታዊ ተግባራቸው የሚፈትሹበት መሆኑን ነው። ከዚህ ቀጥሎ የጥናቱ የትኩረት ነጥብ የሆነው የፈተና አይነት ዘርዘር ባለ መልኩ ለማየት ተሞክሯል።

2.4.4 የችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement Test)

2.4.4.1 የችሎታ መለኪያ ፈተና ምንነት

Finocchiaro and Brumfit (1983:186) የችሎታ መለኪያ ፈተናን አስመልክተው የሚከተለውን ሀሳብ ሰጥተዋል።

> *የችሎታ መለኪያ ፈተና ለትምህርትነት የቀረበው አንድ ምዕራፍ፣ ሞጁል ወይም የመማሪያ መፅሐፍ ካለቀ በኋላ የቀረበውን ትምህርት ተማሪዎች ምን ያህል እንደተረዱት ለመፈተሽ ተብሎ የሚዘጋጅ ወይም የተለያዩ ክሂሎች ዓላማዎችን ምን ያህል ከግብ እንደደረሱ ለማወቅ በትምህርቱ የጊዜ መርሐ ግብር መጨረሻ ወይም አጋማሽ ላይ የሚሰጥ የፈተና አይነት ነው።*

ይህ ብያኔ የችሎታ መለኪያ ፈተና በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተከናወኑትን ትምህርታዊ ተግባራት መሰረት አደርጎ የሚዘጋጁና የተማሪዎችን የሰሚስተር ወይም የግማሽ ሴሚስተር የትምህርት ቆይታቸው የሚፈተሽበት መሆኑን የሚያስረዳ ነው። Heaton (1975:163) ም አብዛኞቹ በየአመቱ መጨረሻና አጋማሽ የሚሰጡ የትምህርት ቤት ፈተናዎች እንዲሁም ማንኛውም በብሔራዊ ደረጃ ተዘጋጅተው አንድ ተማሪ የተወሰነ የትምህርት መርሀ- ግብር ማጠናቀቁን ወይም የተወሰነ ዕውቀት ማዳበሩን ለማወቅ የሚሰጡ ፈተናዎች የችሎታ መለኪያ ፈተና ውስጥ የሚከተቱ መሆናቸው ይገልፃሉ።

Weir (1990:5) በበኩላቸው ጠቅለል አድርገው ሲገልፁ ‹‹የችሎታ መለኪያ ፈተና አጠቃላይ ዓላማ ተማሪዎች በተማሩት ቋንቋ አማካኝነት በመቀበልና በማፍለቅ ክህሎት መጠቀም መቻላቸውን ለማረጋገጥ የሚቀርብ ነው። ይህ አይነቱ ፈተናም በክፍል ውስጥ ከሚሰጠውና በማስተማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከተከተተው የትምህርት ይዘት በቀጥታ የሚገናኝ መሆን አለበት›› በማለት ይገልፃሉ።
የችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች ለትምህርትነት በቀረበላቸው ይዘት ላይ ተመርኩዞ የሚዘጋጅ እንደ መሆኑ መጠን ከድክመትና ጥንካሬ መለኪያ ጋር ተመሳሳይነት ሊኖረው ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ ሁለቱም የተለያዩ መሆናቸውን ምሁራን ያስረዳሉ። Alderson et al (1995:12) ይህን አስመልክተው ማብራራያ ሲሰጡ ‹‹ይህ የፈተና አይነት ከጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና ጋር በእጅጉ ይመሳሳል ነገር ግን የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና በተወሰኑ የቋንቋ ክሂሎችና ውስን ዘርፎች ላይ ተማሪው የሚያሳየውን ለውጥ የሚመረመርበት ነው›› ብለዋል። በተመሳሳይ መልኩ Harison (1983:5) ‹‹የችሎታ መለኪያ ፈተና የአጠቃላይነት ባህሪ ያለውና የትምህርት ሂደትን ተከትሎ የሚመጣ ሲሆን የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና ግን በዝርዝርና ውስን ጉዳዮችን ላይ የሚያተኩር የክፍል ውስጥ ልዩ ልዩ መልመጃዎችን ጭምር ያካተተ በትምህርቱ ሂደት ላይ የሚከናወን ነው›› በማለት ልዩነቱን ያስረዳሉ።

የችሎታ መለኪያ ፈተና አንድ ተማሪ በተወሰነ የጊዜ ክልል ውስጥ የቀረበለትን ትምህርት ምን ያህል እንደጨበጠው የምንገመግምበትና በተሰጠው ትምህርት ያሳየው የዕውቀትና ክህሎት ለውጥ የምንመዘንበት የፈተና አይነት ነው። ይህ ደግሞ በተማሪው ላይ

የሚጠበቀውን የአስተሳሰብና የአሰራር ለውጥ ለመከታተልና አጠቃላይ የመማር ማስተማር ሂደቱን አቅጣጫ ለመረዳት ብሎም አስፈላጊ የሆኑ አካዳሚያዊ ሆነ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ለመወሰድ በግብአትነት የሚያገለግል ነው።

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ግን የቋንቋ ፈተናዎች መደበኛ የትምህርት መርሀ ግብር ከመተግበሩ በፊት የቅደመ ዕውቀት ለመፈተሽና በተወሰነ ደረጃ ለመፈረጅ ተብለው የሚዘጋጁ አልያም ከትምህርት በኋላ ያለው የግንዛቤና የችሎታ ደረጃ ለመለካት ተብለው የሚዘጋጁ መሆናቸው ግልፅ ነው። ትምህርት ከመሰጠቱ በፊት የሚዘጋጁት የቋንቋ ፈተናዎች በአጠቃላይ የቋንቋ ንድፈ ሀሳብ ላይ ተመስርተው ዝርዝር ጉዳዮችን ሳይነኩ ጥቅል የቋንቋ ዕውቀትና ክህሎት ላይ የሚያተኩሩ ሲሆኑ፣ ከትምህርት በኋላ የሚዘጋጁት የቋንቋ ፈተናዎች ግን ዝርዝር የቋንቋ ይዘቶችን በመገምገም አጠቃላይ የቋንቋ ዕውቀትና ክህሎት ደረጃን ለማወቅ በሚረዳ መልኩ የሚዘጋጁ ናቸው። የዚህ ጥናት ትኩረት የአንድን ትምህርት መርሀ-ግብር መጠናቀቅን ተከትሎ የሚሰጠው ፈተና ላይ በመሆኑ ከዚህ ቀጥሎ የሚሰጡ ሀሳቦች ይህንኑ መሰረት ያደረጉ ናቸው።

2.4.4.2 የችሎታ መለኪያ ፈተና ይዘት አመራረጥ

ቀደም ሲል እንደተገለፀው የችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች እንዲማሩት የቀረበላቸውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱት ለመለካት የሚያስችል በመማሪያ መፅሐፉ የሰፈሩት የትምህርት ይዘቶች መሠረት አድርጎ የሚዘጋጅ ፈተና ነው። በመሆኑም የዚህ አይነቱ ፈተና ይዘት ሲመረጥም ተማሪዎች ከተማሩበትና የቋንቋ ትምህርት አላማ መሰረት አድርጎ ከተዘጋጀው መማሪያ መፅሐፍ ነው። Alderson et al (1995:12) እንደገለፁት የችሎታ መለኪያ ፈተና ለትምህርትነት የቀረበውን መማርያ መጽሐፍ መሰረት አድርጎ የሚዘጋጅና የትምህርቱ መርሀ- ግብር ሲጋመስ ወይም ሲጠናቀቅ ለተማሪዎች የሚቀርብ የፈተና አይነት ነው።

Hughes (1989:10) ም የችሎታ መለኪያ ፈተና በመርሐ ትምህርቱ ንኡስን ክፍሎች ዝርዝር ላይ ማለትም በመማሪያ መፅሐፉና ሌሎች ጥቅም ላይ በዋሉ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ላይ ተመስርቶ የሚዘጋጁ የፈተና አይነት መሆኑን ጨምረው ይገልፃሉ። በማስከተልም ተማሪዎች የተማሩትን ነገር በመፈተናቸው ጠንካራ ጎን ይታይበታል። ነገር ግን የማስተማሪያ መሳሪያዎች በአግባቡ የተዘጋጁ ካልሆኑና በፈተናው ይዘት

አመራረጥ ላይ ጥንቃቄ የማይደረግ ከሆነ በተማሪዎች ትምህርት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር በመሆኑ ደካማ ጎን እንዳለው ይጠቅሳሉ።

የምሁራኑ ገለፃ እንደሚያመለክተው የችሎታ መለኪያ ፈተና ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሩትን ይዘት ምን ያህል ይዘውታል? የሚል ጥያቄን ለመመለስ የሚዘጋጁ እንደመሆኑ መጠን ይህን ጥያቄ በትክክል ሊመልስልን የሚችል ፈተና ማዘጋጀት የሚቻለው ደግሞ ከዚያ ከተማሩበት መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ካሉት ይዘቶች መካከል በናሙናነት በመውሰድ ብቻ ነው። ይህን ሐሳብ በማጠናከር Finocchiaro and Brumfit (1986:186) ሲገልፁ ‹‹የችሎታ መለኪያ ፈተና በአንድ መደበኛ የትምህርት መርሀ ግብር ውስጥ በመርሀ-ትምህርቱ የተጠቆሙትና በመማሪያ መፅሐፍ በዝርዝር የሰፈሩትን የትምህርት ይዘቶች በትምህርት ዘመኑ አጋማሽ ላይ አልያም በአመቱ ማጠቃለያ የሚተገበር የፈተና አይነት ነው›› ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪም Cronbach (1970:147) የተባሉት ምሁር ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘቡት ለመዳሰስ ተብለው የሚዘጋጁት ፈተናዎች በፈተናው ይዘት አመራረጥ ላይ ትልቅ ትኩረት ሊያደርግባቸው እንደሚገባ ያስጠነቅቃሉ። አንዳንድ የፈተና አዘጋጆች በትምህርት ይዘቱ የተወሰነ አካባቢ ወይም ለጥያቄ ይመቻል ባሉት አካባቢ ብቻ ያተኩራሉ፣ ይህ ደግሞ የተማሪዎችን ውጤት ከማበላሸት በተጨማሪ የትምህርቱ አላማ መሳካት አለመሳካቱ በትክክል ሊገመግመልን የማይችል አካሄድ ነው በማለት ይገልጻሉ። በመሆኑም ይህን ችግር ለመቅረፍ የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ (Table of Specification) በማዘጋጀት ይህንን የሚወክል የፈተና ይዘት ጥንቃቄ በተሞላው ናሙና መውሰድ ያስፈልጋልም ብለዋል።

Brown (1994:259) ም እንዲሁ የችሎታ መለኪያ ፈተና በቀጥታ በመማርያ መፅሐፍ ውስጥ ከተዳሰሱት ምዕራፎችና ባጠቃላይ ሰርአተ ትምህርቱን ካዘጋጀው የትምህርት ይዘት ተመርኩዞ የሚዘጋጅ በመሆኑ ይህንኑ የሚወክል የፈተና ይዘት በአግባቡ መቅረብ እንዳለበት ያስገነዝባሉ። የቋንቋ መርሐ ትምህርቱና የመማርያ መፅሐፍ ይዘቶች የቋንቋ ትምህርት አላማዎችን በዝርዝር ለማስፈር ታቅደው የተዘጋጁ እንደመሆናቸው መጠን በፈተና ናሙና አመራረጥ ላይ ይበልጥ ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል። እያንዳንዱ

በመማርያ መፅሐፍ ላይ ያለው ይዘት ለቋንቋ ትምህርት አላማ መሳካትና አለመሳካት የሚያደርገው የራሱ አስተዋፅኦ አለው። በመሆኑም ይህን ለመለካት በሚያስችለው ፈተና ላይ በአግባቡና በትክክል ተወክሎ ሊገኝ ይገባል (Harrison 1983:9 እና Madsen 1983:189)።

ከላይ ከተሰነዘሩት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው የችሎታ መለኪያ ፈተና በሰርዓተ ትምህርቱ የተቀመጡትን አጠቃላይ የትምህርቱ አላማዎች ለመተግበር ያስችል ዘንድ በተለያዩ ይዘቶች የተደራጀ የማስተማርያ መፅሐፍ አማካኝነት ጊዜና ቦታ ተበጅቶለት ሲከናወን የነበረውን የመማር መስተማር ሂደት ያስገኘውን ውጤት የሚመዘንበት የፈተና አይነት ነው። ይህ አይነቱ ፈተና ተማሪዎች እንዲማሩት፣ እንዲጨብጡት የተሰጣቸውን ትምህርት ይዘውታል ወይስ አልያዙትም ለሚል ጥያቄ ምላሽ የሚሆን ነው። በመሆኑም ይህን በትክክል የመመለስ ብቃት ያለው ፈተና ማዘጋጀት የሚቻለው ሁሉም በትምህርትነት የቀረቡት ይዘቶች በትክክለኛና ወካይ ናሙና (Representative Sampling) ተመርጠው በፈተናው ላይ መታየት ሲችሉ ነው። ይህን ለማደረግ ደግሞ የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ መጠቀም ተመራጭ መንገድ እንደሆነ ከምሁራኑ መረዳት ይቻላል።

2.5 የቋንቋ ፈተና እና የቋንቋ ትምህርት

ተስፋዬ (1981፡122) "ፈተና ተማሪዎች የተሰጣቸውን፣ እንዲማሩት የተደረጉትን ትምህርት ማወቅ አላማወቃቸውን መለያ ስለሆነ መፈተን ያላባቸውም ይህንኑ እንዲያውቁት የተደረጉትን፣ የተማሩት ሊሆን ይገባል" በማለት ይገልፃሉ። ይህም ለፈተና የሚቀርቡ ጥያቄዎች በትምህርት የቀረበውን ይዘት መሰረት ያደረጉና በሚፈለጉት የተማሪዎች ባህርያት ላይ የተመረኮዙ መሆን እንዳለባቸው ያስረዳናል።

ከዚህ በተጨማሪ የፈተናና የመማር ማስተማር ሂደቱ ጠንካራ ትስስር ለመግለፅ Hughes (1989:31) እና Heaton (1990:22) ‹‹ፈተናን ከመማር ማስተማሩ ሂደት ነጥሎ መመልከት አይቻልም፣ በተለይ ከፈተና አይነቶች መካከል የመማር ውጤት መለኪያ ፈተና የሚባለው መሰረት የሚያደርገው ተማሪውን የተማረውን ትምህርት ወይም ይማረዋል የተባለውን የትምህርት መርሀ ግብር በመሆኑ ከመማር ማስተማር

ሂደቱ ጋር ጥብቅ የሆነ ግኑኝነት እንዲኖረው ይጠበቃል›› በማለት ይገልጻሉ፡፡ Heaton (1975:15) ሲገልፁ ‹‹ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ሁለቱም መስኮች ተነጣጥለው ሊሰጡ የማይችሉ፣ ጥብቅ ቁርኝነት ያላቸው የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት አካላት ናቸው፡፡ በመሆኑም አንደኛውን ከሌላኛውን ነጥሎ ማየት ፍፁም አይቻልም፡፡ ስለዚህ የሁለቱን የጠበቀ ትስስር በውል በመገንዘብና አስፈላጊውን ትኩረት በመስጠት ጎን ለጎን ማራመድ ይኖርብናል›› ብለዋል፡፡ Davies (1988:5) ም "ጥሩ ፈተና ያስተማርነውን በመፈተን ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ከማስተማር በኋላ የሚመጣ ተከታይ ሂደት ነው" ሲሉ የቋንቋ ፈተናና የቋንቋ ትምህርት ያላቸውን ግኑኝነት ለማሳየት ሞክረዋል፡፡

Weir (1990:5) የሁለቱም ግኑኝነት በተመለከተ ‹‹የመማር ውጤት መለኪያ ፈተና ቀድሞ በክፍል ውስጥ ከተሰጠው ትምህርት ጋር የማይያያዝ ከሆነ ምንጊዜም ቢሆን ችግር መከሰቱ አይቀሬ ነው›› በማለት የፈተናና የመማር ማስተማር ሂደቱን ጥብቅ ግኑኝነት ያስገነዝባሉ፡፡
አንድ ፈተና የመማር ማስተማር ሂደት ተከትሎ በአግባቡ ከተዘጋጀ ፈተናው በመማር ማስተማር ሂደት ላይ አዎንታዊ ምጋቤ ምላሽ ያስከትላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፈተና የተለያዩ መረጃዎችን በመስጠት የመማር ማስተማር ሂደቱን እንደሚያጠናክር የመስኩ ባለሙያዎች ይገልፃሉ፡፡ Baker (1989:106) የተባሉት ምሁር ሲገልፁ ፈተና አንድ የቋንቋ ትምህርት አይቀሬ አካል ነው፡፡ ይህ የሚሆንበት ዋና ምክንያትም መምህራን፣ ተማሪዎችና የትምህርት ቤት የአስተዳደር አካላት የጥረታቸውን ተጨባጭ ውጤት ወይም መረጃ ይሻሉ፡፡ ይህ ደግሞ ከፈተና ውጤቶች የሚገኝ ነው›› ብለዋል፡፡ ስለሆነም ፈተና በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሚሳተፉ አካላት ሁሉ ስለሚሰጠው ትምህርት በቂ መረጃ ከፈተናዎች ማግኘት ይችላሉ፣ ፈተናዎችም ለዚህ ጉልህ ሚና ያላቸው ናቸው፡፡

ቀደም ሰል ለመግለፅ እንደተሞከረው መምህራን ፈተናዎችን ለተለያዩ ዓላማዎች ሊገለገሉባቸው ይችላሉ፡፡ ብዙውን ጊዜ ግን ፈተናዎች የሚዘጋጁት ተማሪዎች የተማሯቸውን ይዘቶች ምን ያህል እንደጨበጧቸው ለመገምገም ነው፡፡ በተለይ የመማር ውጤት መለኪያ የምንላቸው የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ያለውን ለውጥ ለመገምገም የሚያግዙ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡትን ሀሳቦች የሚያሰገነዝቡት ጉዳይ ቢኖር የቋንቋ ትምህርትና የቋንቋ ፈተና ሊነጣጠሉ የማይችሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ መሆናቸውን ነው። ስለሆነም በክፍል ውስጥ ለሚከናወነው የመማር ማስተማር ሂደትም ሆነ ለአጠቃላይ የቋንቋ መርሀ ግብር መሳካት ሁለቱም እጅና ጓንት ሁነው ሊሄዱ ይገባል። ይህ እንዲሆን ደግሞ የሚዘጋጁት የቋንቋ ፈተናዎች፣ ተማሪዎች ሊማሯቸው ተብለው በመማርያ መፅሐፍ ውስጥ በተካተቱት ይዘቶች መመሰረት ይኖርባቸዋል።

2.6 የቋንቋ ፈተና እና የቋንቋ መማርያ መፅሐፍ

የቋንቋ መማርያ መፅሐፍ ስርአተ ትምህርቱን መሰረት በማድረግ በተቀረፀው የቋንቋ መርሐ ትምህርት ውስጥ በጥቅሉ የተቀመጡት አላማዎችንና ርዕሰ ጉዳዮች በክፍል ውስጥ በመምህሩና በተማሪው ተራክቦ ሊተገበሩ በሚችሉበት መንገድ ተዘርዝረው የሚገኙበት የትምህርት መሳርያ ነው። Nunan (1988:98) ‹‹የመማሪያ መፃሕፍትና የመርሐ ትምህርት ግኑኝነት አስመልክተው ሲገልፁ የቋንቋ መማርያ መፅሐፍ ያለምንም ጥርጥር መርሐ ትምህርቱ በዝርዝር የሚታይበትና በተግባር የሚገለፅበት ነው›› በማለት ገልጸዋል።

Dubin and Olshtain (1986:35) እና Cunning worth (1995:53) የተባሉት ምሁራን እንደሚገልጹትም የቋንቋ መርሐ ትምህርት ከሥርአተ ትምህርት የሚፈልቅ አንድን ውሱን የቋንቋ ትምህርት እንዴት ማስተማር እንደሚቻል የሚጠቁም፣ የትምህርቱን አላማ፣ ይዘት፣ አቀራረብ፣ ጊዜና ግምገማ የሚያመለክት ሰነድ ነው። ይህ በጥቅሉ የቀረበ አጠቃላይ የመማር ማስተማር አቅጣጫ ጠቋሚ ሰነድ ተግባራዊ ክዋኔው የሚገለፀው በመማርያ መፅሐፉ አማካኝነት ነው።

የቋንቋ መማርያ መፅሐፍ በመርሐ ትምህርቱ የተገለፁትንና እለት እለት ክፍል ውስጥ ተግባራዊ በመሆን የሚታዩትን የትምህርት ዓላማዎች ስኬታማ ለማድረግ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። በመማርያ መፅሐፍ መሪነት የሚከናወነውን የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ስኬት ተደምሮ በመርሐ ትምህርቱና በስርአተ ትምህርቱ ያሉትን የትምህርት አላማዎች ለውጤት የሚያበቃ ነው። ይህም እነዚህ ሶስት አካላት ያላቸውን ጥብቅ ቁርኝነት በግልፅ ያሳያል (Richards and Rodgers

1986:24፣ Harmer 1991:256):: Carter (1973:605) እንደገለፀት የመማርያ መፅሐፍ የተወሰነ የትምህርት ጥናትን የያዘ፣ ሥርዓት ባለው መንገድ የተደራጀ፣ ለተወሰነ የትምህርት ደረጃ የሚዘጋጅና ለአንድ የትምህርት ዘርፍ እንደ ዋና የጥናት ምንጭ ሆኖ የሚያገለግል የትምህርት መሳሪያ ነው።

ከምሁራኑ ገለፃ መረዳት እንደሚቻለው በመምህሩና በተማሪው ተራክቦ የሚከናወነው የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ተግባር የቋንቋ መማርያ መፅሐፉን መሰረት ያደረገ ሲሆን፣ ይህ መማርያ መፅሐፍ መሰረት የሚያደርገው ደግሞ አጠቃላይ ስርአተ ትምህርቱን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀውን የቋንቋ መርሀ ትምህርቱን ነው። በቋንቋ መማርያ መፅሐፉ ውስጥ ያሉት የትምህርት አላማዎች በስኬት መጠናቀቅ በቋንቋ መርሀ ትምህርቱ የተቀመጡ አላማዎችን ማሳካት ይሆናል። የዚህ ድምር ውጤት ደግሞ አጠቃላይ ስርአተ ትምህርቱ የያዛቸው የአስተሳሰብና የአሰራር ለውጥ የሚያስከትሉ አበይት የትምህርት አላማዎችን ከግብ ለማድረስ ያስችላል።

ይህ አይነቱ የተንሰላሰለ የስኬት ጉዞ እውን ለማድረግ የግምገማና የማሻሻያ ተግባራት ማከናወን ቁልፍ ጉዳይ ነው። Heaton (1975:6) እንደሚገልፁት በማንኛውም መልኩ የሚካሄዱ የግምገማ ተግባራት እየተካሄደ ያለውን የመማር ማስተማር ተግባር ምን ያህሉን በተፈለገው መንገድ እየተጓዘ እንደሆነ፣ የታቀደው አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ የመምህሩ፣ የአስተዳደር አካላትም ሆነ የተማሪዎች ተግባራት እንዴት እየተተገበሩ እንዳለ ወዘተ መረጃ በመስጠት መወሰድ የሚገባውን የእርምት እርምጃ በጊዜው እንዲወሰድ ሂደቱን ከግብ እንዲደርስ የማይተካ ሚና የሚጫወቱ ናቸው። ታድያ ይህ የግምገማ ተግባር የታለመለትን አላማ እንዲያሳካ ተገቢው ጥንቃቄ ተደርጎበት መሰረታዊ የግምገማ አዘገጃጀት መርሆች፣ አቀራረቦችና ባህርያት አሟልቶ ሊገኝ ይገባል።

2.7 የቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት፣ ምንነትና አስፈላጊነት

2.7.1 የቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት ምንነት

በትምህርት ቤት ደረጃ የሚዘጋጁና በብሄራዊ ደረጃ የሚዘጋጁ (ሀገር አቀፍ) ፈተናዎች ተማሪዎች በቀረበላቸው ትምህርት አማካኝነት ያመጡትን የዕውቀትና ክህሎት ለውጥ

ለመለካት ያለመ እንደመሆናቸው መጠን መሰረት የሚያደርጉትም ያንኑ የተማሩትን ትምህርት ነው Bachman (1990) ፣ Heaton (1975) ፣ Harrison (1983) እና Brown (1994) ። በተለይም ደግሞ በየትምህርት አይነቱ መምህራን በየትምህርት ቤቱ የሚዘጋጇቸው ፈተናዎች ተማሪዎች ስለ ቀሰሙት ትምህርት ያላቸውን ግንዛቤ በመለካት የወዲያውኑ ምላሽ (Immediate Feedback) የሚሰጥባቸው እንደመሆናቸው መጠን ይዘታቸው ከመማርያ መፅሀፍ ወይም ከተማሩት ትምህርት ውጭ መሆን የለበትም።

የይዘት ተገቢነት ምንነት በማስመልከት በርካታ የፈተና ባለሙያዎች የየራሳቸውን ሀሳብ ወይም ብያኔ ሰጥተዋል። ከነዚህ የተሰጡት ብያኔዎች መካከል የተወሰኑትን ለመጥቀስ የሚከተሉትን እንመለከት። Hughes (1989:22) ሲገልፁ ‹‹የይዘት ተገቢነት አንድ ፈተና መለካት የተፈለገው አንድ የባህሪ አውደ ግዛት (Behavioral domain) ን የሚወክል ናሙና መሆኑን ለማረጋገጥ የሚደረግ ስርዓታዊ ግምገማ ነው›› ብለዋል። እንደ እሳቸው አገላለፅ አንድ ፈተና ለመለካት የሚፈልጋቸው የትምህርት ዓላማዎች አሉት፣ ፈተናው እነዚህ የትምህርት አላማዎችን የሚወክሉ ናሙናዎች ይዞ የቀረበ መሆኑን የማረጋገጥ ተግባር ደግሞ የይዘት ተገቢነት እንደሚባል ነው።

Hughes (1989:10) ደግሞ የፈተና ይዘት በተለይ የችሎታ መለኪያ ፈተናዎች ይዘት በቀጥታ ከመርሀ ትምህርቱ ይዘት ወይም ከመማሪያ መፀሐፍ የተወሰደ መሆን አለበት በማለት አቋማቸውን በመግለፅ፤ የይዘት ተገቢነት ማለት በፈተናው ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች ምን ያህል የመርሀ ትምህርቱን ወይም የመማሪያ መፅሐፉን የሚወክሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ ተግባር የሚገልፅ ፅንሰ ሀሳብ ነው በማለት ያስረዳሉ። Madsen (1983:195) ም ‹‹የአንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት የሚመዘነው የፈተናው ይዘት ምን ያህል የትምህርት አይነቱ በስተመጨረሻ ይደረስባቸዋል ብሎ ያስቀመጣቸው ማጠቃለያዎችን የሚወክል መሆኑን በመመልከት ነው›› ብለዋል።

በሌላ በኩል Harrison (1983:11) እና Brown (1994:255) ሲገልፁ ‹‹የይዘት ተገቢነት አንድ ፈተና በውስጡ የያዛቸው የፈተና ጥያቄዎች በመርሀ ትምህርቱ ያለውን የትምህርት አላማዎችን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀውንና ለትምህርት የቀረበውን

የማስተማሪያ መሳሪያ (መማሪያ መፅሐፍ) የሚወክል መሆን አለመሆኑን መፈተሽን የሚመለከት ጉዳይ ነው›› ብለዋል። እንደነዚህ ምሁራን ገለጻ የይዘት ተገቢነት የሚባለው የአንድ ፈተና ይዘት ለትምህርትነት ከቀረበው ወይም በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከተካተቱ የትምህርት ይዘቶች ጋር ትስስር እንዲኖረው የማድረግና ወካይ ንሞና (Representative Sampling) የማካሄድ ተግባር መሆኑን ያመለክታል። Alderson et al (1995:171) ም ይህንን ሲያጠናክሩ ‹‹የይዘት ተገቢነት ተማሪዎች የተፈተኑት ፈተና ይዘት ከተማሩት ትምህርት ጋር የማነጻጸር ስልት ነው›› በማለት ይገልፃሉ። በተመሳሳይ መልኩ Finocchiaro and Brumfit (1983:189) ‹‹የይዘት ተገቢነት አንድ ፈተና ምን ያህል የተመሰረተበትን መርህ ትምህርት በትክክል ያንፀባርቃል? የሚል ጥያቄን ለመመለስ የሚደረግ ዳሰሳን የሚመለከት ነው›› በማለት በይነውታል።

የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በቋንቋ በመርህ ትምህርቱ የተጠቆሙት አጠቃላይ የትምህርት ይዘቶች መሰረት በማድረግ ዝርዝር የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን ለክፍል ውስጥ ለሚደረገው የመምህርና ተማሪ መስተጋብር በሚያመች መልኩ ተዘጋጅተው የቀረቡበት የማስተማሪያ መሳሪያ መሆኑን ቀደም ሲል ተገልጿል። ስለዚህ እነዚህ ምሁራን የይዘት ተገቢነት አንድ ፈተና ምን ያህል የተመሰረተበትን መርህ ትምህርት ያንፀባርቃል ሲሉ በመማሪያ መፅሐፉ የተካተቱ ዝርዝር የትምህርት ይዘቶችን የሚመለከት መሆኑን መረዳት ይቻላል።

በአጠቃላይ የይዘት ተገቢነት ከፈተና አዘጋጃጀትና አጠቃቀም መርህ አንጻር ሲታይ ሁለት ነገር ግን መሰረታዊ ልዩነት የማይታይባቸው ሀሳቦች ሲሰነዘሩ ይስተዋላል። እነሱም የመጀመሪያው የይዘት ተገቢነት የሚባለው የአንድ ፈተና ይዘቶች ፈተናው ሊለካው በሚፈልገው ባህርይ ወይም አላማ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን የማረጋገጥ ተግባር ነው የሚል ሲሆን፣ በዚህ አባባል መሰረትም ከአጠቃላይ የትምህርቱ አላማዎች መካከል በፈተና ለመካት የሚፈለጉ ችሎታዎች (ባህሪያት ወይም አላማዎች) ይለያሉ። የእነዚህ ባህርያት ስብስብ የሚገኝበት የባህሪ አውደ ግዛት (behavior domain) በፈተናው ላይ በትክክልኛ ናሙና መወከሉን የማረጋገጥ ሂደት የይዘት ተገቢነት ይመለከታል። ይሁን እንጂ Bachman (1990:244) በቋንቋ ፈተና ላይ መፈተን

ያለባቸው ችሎታዎች በግልፅና በማያሻማ መንገድ ቀደምብለው የተቀመጡ በመሆናቸው ይህንን አካሄድ ለመከተል አስቸጋሪ መሆኑን እኚህ ምሁር ይገልጻሉ።

ሁለተኛው ሀሳብ እና ይህን ጥናት የተመለከተበት የብያኔ አቅጣጫ ደግሞ የይዘት ተገቢነት አንድ ፈተና ከመርሀ ትምህርቱ ወይም ከመማሪያ መፅሐፉ ይዘቶች ጋር ያለውን የውክልና ደረጃ ምን ያህል እንደሆነ የመገምገም ተግባር የሚመለከት እንደሆነ የሚገልፅ ነው። በዚሁ አስተሳሰብ መሰረት በመማርያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት የቋንቋ ክሂሎችና ዕውቀቶች በብቃትና በትክክል የሚወክሉ የፈተና ጥያቄዎች ተከትተው መገኘት አለባቸው። በፈተናው የቀረበው የጥያቄዎች ስብስብ የመማሪያ መፅሐፉ ይዘት በበቂና ትክክለኛ መንገድ ወካይ ናሙና ሆኖ መቅረቡን የማረጋገጥ ሂደት የይዘት ተገቢነትን ይመለከታል።

2.7.2 የቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት አስፈላጊነት

ይህ የይዘት ተገቢነትን የማረጋገጥ ተግባር የመማር ማስተመር ሂደትን ውጤታማ ለማድረግ ካለው አስተዋጽኦ አንፃር ሲታይ እጅግ አስፈላጊና የማይተካ ዋጋ ያለው መሆኑን Cronbach (1970:145) ያስረዳሉ። Bachman (1990:244) ም በፈተና ዝግጅትም ሆነ አጠቃቀም ላይ የፈተና ይዘት ትልቅ ትኩረት የሚሻ መሆኑን በመግለፅ ይዘቱን ተገቢ የማድረግ ተግባር ፈተናው በአጠቃላይ ትርጉም ያለው፣ ትክክለኛና ተአማኒ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክት መሆኑ ገልፀዋል።

ከዚህ በተጨማሪ Hughes (1989:22) የፈተና ይዘት ተገቢነቱን እንዲጠብቅ የማድረግ ተግባር በሚከተሉት ሁለት አበይት ምክንያቶች አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻሉ። እነሱም:-

ሀ. የአንድ ፈተና የይዘት ተገቢነት ደረጃ ከፍ ባለ መጠን ፈተናው ለመፈተን ያሰበውን ጉዳይ በትክክል የመፈተን ብቃቱም ከፍ እያለ ይሄዳል። በትክክለኛ ናሙና ላይ ያልተመሰረተና ሁሉንም ይዘቶች በእኩልነት ያላሳተፈ ፈተና የትክክለኛነቱ ደረጃም የወረደ ነው። ለዚህም ሲባል የይዘት ተገቢነት ደረጃ በመፈተሽ የፈተናውን ተገቢነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

ለ. አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥር ምጋቤ ምላሽ ስለሚያስከትል። አብዛኛውን ጊዜ በፈተና ላይ ያልተካተቱ የትምህርት ይዘቶች በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይም ትኩረት ያላገኙ

ናቸው ተብሎ ይታመናል። አብዛኛዎቹ የፈተና ይዘቶችም ለፈተናው ካላቸው አስተዋፅኦ ሳይሆን ለመፈተን ካላቸው አመቺነት አንጻር የሚመረጡ ናቸው። ስለዚህ ፈተናው እንዲህ አይነቱ ምጋቤ ምላሽ ከመሰጠቱ በፊት የይዘት ተገቢነቱን መጠበቅና ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

2.8 የቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት ደረጃን መጠበቂያ መንገዶች

የቋንቋ ፈተና በአወንታዊነት የሚፈረጅ የይዘት ተገቢነት ያለው አድርጎ ማዘጋጀትም ሆነ የተዘጋጀውን መርምሮ የይዘት ተገቢነትን ያሟላ መሆኑንና አለመሆን ማረጋገጥ ቀላል ስራ እንዳልሆነ ምሁራን ይገልጻሉ። ሆኖም ግን ችግሩን ለማቃለል የሚረዱና የይዘት ተገቢነትን የጠበቀ ፈተና ለማዘጋጀት የሚያስችሉ ልዩ ልዩ መንገዶች በመጠቆም ላይ ናቸው።

ከነዚህ ውስጥ Weir (1990:25) የገለፅዋቸውን የይዘት ተገቢነትን ለመጠበቅ የሚያስችሉ መመሪያዎች እንደሚከተለው ይቀርባሉ። እነሱም፡-

- መጠየቅ የሚገባቸው የተተኳሪው ይዘት ክፍሎች በፈተናው ጥያቄዎች ውስጥ እንዲካተቱና ተመጣጣኝ ውክልና እንዲያገኙ የሚመዘኑበት የባህሪ ክፍል ሰርዓታዊ በሆነ መንገድ መተንተን አለበት።
- ፈተናው ከመዘጋጀቱ በፊት ትኩረት የሚሰጠው ክፍል (domain) በሚገባና በተሟላ መንገድ በቅድሚያ መገለፅ አለበት።
- ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዱን የባህሪ ክፍል በፈተናው ከሚኖራቸው ድርሻ

አንጻር የሚወከልበት አሰራር በመከተል ፈተናው ማዘጋጀት የሚሉ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ Gronulonad (1981:69) እንደገለፁት በፈተና ዝግጅት ወቅት የይዘት አመራረጥ ላይ ተገቢ ትኩት ስለማይሰጥ የፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ብዙ ጊዜ አጠያያቂ ሲሆን ይታያል። በመሆኑም የፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ደረጃ ለመጠበቅ ከሚያስችል ስርዓታዊ ስልተ ትግበራዎች መካከል የሆነውንና በስፋት የሚታወቀውን የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ (Table of Specification) መጠቀም ያስፈልጋል።ይህ የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ የሚባለው ባለሁለት ረድፍ ሰንጠረዥ ሲሆን ለመፈተን የሚፈለጉ የትምህርት ልምዶችንና እነዚህን የሚወክሉ ጥያቄዎችን የሚያመለክት ነው። የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ ሲዘጋጅ የትምህርቱ ይዘቶች

ከእያንዳንዱ የትምህርቱ ዝርዝር አላማዎች አንፃር እየተመጠኑ በቁጥር መመልከት አለባቸው (Gronulonad 1981:70 ፣ Cronbach 1970:145)::

ይህ አይነት ሰንጠረዥ በፈተና አዘጋጆች ቢለመድ የፈተና የይዘት ተገቢነት ደረጃን ለመጠበቅ እጅግ ጉልህ ሚና የሚጫወት መሆኑን Alderson et al (1995:173) ይገልጻሉ:: በመቀጠልም ይህ የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ የፈተናው ግብ ምን መሆኑ፣የትኞቹን የቋንቋ ክፍሎችና ዕውቀቶች ለመፈተን እንደተፈለገና ለእያንዳንዱ ክፍል ምን ያህል ጥያቄዎች እንደሚያስፈልጉ መረጃ የሚሰጥ መሆኑን ገልፀዋል::

በአጠቃላይ የቋንቋ ፈተናን የይዘት ተገቢነት ደረጃን ለመጠበቅ አንድ ስርአቱን የጠበቀ መንገድ መከተል እንዳለብን መረዳት ይቻላል:: ይህም ምሁራኑ እንደሚያስረዱት መፈተን የተፈለጉት የትምህርት ልምዶች (ተግባራት) በዝርዝር በመለየት እያንዳንዳቸውን የትምህርት ልምዶችን የሚወክሉ የፈተና ጥያቄዎችን መወሰን ያስፈልጋል:: ይህ ወሰነ- ሰንጠረዥ የተባለው ስልትም ይህንን ለመተግበር አመቺነት ያለው በመሆኑም ምሁራኑ የፈተና አዘጋጆችን ይህንኑ እንዲጠቀሙ በአፅንኦት ይመክራሉ::

2.9 የቋንቋ ፈተና የይዘት ተገቢነት መገምገምያ ስልቶች

በፈተና መዳሰስ ያለባቸው የባህሪ ክፍሎች ከትምህርቱ ልምዶች አንጻር ተተንትነው ከቀረቡ በኃላ የተዘጋጀው ፈተና ያለው የይዘት ተገቢነት ደረጃውን ለማወቅ የተለያዩ ስልቶች መከተል ይቻላል:: Weir (1990:25) እንደገለፁት እያንዳንዳቸው የተማሪዎች የፈተና መልሶች ቀድሞ ትኩረት ከተሰጣቸው የባህሪ ክፍሎች ጋር ያላቸውን ዝምድና በመመልከት የፈተናውን የይዘት ተገቢነት ማረጋገጥ ይቻላል::

Alderson, et al (1995:193) ከዚህ ስልት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን የማረጋገጫ ስልቶች ገልፀዋል:: እነሱም:-

- የመጀመሪያው ተማሪዎች የተፈተኑት ፈተና ይዘት ከተማሩትና በመርሀ ትምህርት ወይም መማሪያ መፅሐፍ ካለው ይዘት ጋር ያለው ቀጥተኛ ግኑኝነትና ውክልና የማነፃፀር ስልት ሲሆን፤

- ሁለተኛው የፈተናው የይዘት ተገቢነትን በተመለከተ የጽሁፍ መጠይቆችን በማዘጋጀት መምህራን፣የዘርፉ ባለሙያዎችና የተግባራዊ ስነ- ልሳን ሊቃውንትን በማስሞላት መረጃ መሰብሰብ እንዲሁም በቃለ መጠይቅ ምላሻቸውን መቀበል የሚሉት ናቸው።

ይህም በፈተናው የተካተቱ ይዘቶች እንዲለካ የታቀደውን አላማና ይህንን የሚንፀባረቅባቸው የትምህርት ይዘቶችን መያዝ አለመያዛቸውን በመፈተሽ ያላቸው ውክልና ወይም የተገቢነት ደረጃ ማረጋገጥ እንደሚቻል የሚያመለክት ነው።

በአጠቃላይ ተስፋዬ ሽዋየ (1981) ፣ Madsen (1983) ፣ Hughes (1989)፣ Weir (1990) እና Brown (1996) ጥሩ ፈተናን ለማዘጋጀት የሚከተሉትን የፈተና አዘገጃጀት መርሆች መከተልና መገንዘብ ያስፈልጋል ብለዋል።

- ማንኛውም ፈተና የሚያዘጋጅ አካል ፈተናው ለምን ጉዳይ እንደሚዘጋጅ በውል ማወቅ አለበት። ይህም የፈተናው ይዘት፣ መጠንና ቅርፅ በተመለከተ በቂ መረጃ እንዲኖር ያግዛል።
- በፈተና የሚቀርቡ ጥያቄዎች በሚፈለጉት ባህርያትን በተሰጠው ትምህርት ላይ የተመሰረቱ መሆን አለባቸው። ከዚህ ጋር ማንኛውም ጥያቄ የሚፈለገውን ባህርይ በትክክል ሊወክል ስለማይችል ተስማሚነቱን በትክክል መረዳት ያስፈልጋል።
- የችሎታ መለኪያ ፈተና በክፍል ውስጥ ከቀረበው ትምህርት ጋር መዛመድ ይኖርበታል፤ ናሙናው ሲወስድም ወካይ በሆነ መልኩ ሊከናወን ይገባል።
- የፈተና ጥያቄዎች ሲወጡ ፈተናው የተዘጋጀላቸውን ተማሪዎች (ተፈታኞች) ችሎታ የሚመጥን እና በተፈታኞችም መካከል ያለውን የዕወቀት ልዩነት አጉልቶ የሚያሳይ መሆን አለበት።
- የሚዘጋጀው ፈተና ለተሰጠው ጊዜ ብዙ መሆን ብቻ ሳይሆን የትምህርት ይዘት ትክክለኛነትና ተአማኒነት ብቃት ለማወቅ የጥያቄዎች ብዛት አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ አለብን።
- ተማሪው ከፈተናው ብዙ ሊገነዘበው የሚችል ነገር እንዲኖረው እና መምህሩም በዚያው አንጻር ከተማሪው መልስ መነሻነት ነገሮችን የማስተካከል ተግባር ማከናወን መቻል አለበት።

2.10 የቀደምት ስራዎች ቅኝት

እስካሁን ድረስ በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ላይ የተካሄዱት ጥናቶች በአጠቃላይ ሲታዩ በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ እነሱም፡- በትምህርት ቤት ደረጃ ቋንቋውን በሚያስተምሩ መምህራን በተዘጋጁ ፈተናዎች ላይ የተካሄዱ ጥናቶች እና በሀገር አቀፍ እና ክልል አቀፍ ደረጃ በተዘጋጁት ብሄራዊ ወይም ክልላዊ ፈተናዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ናቸው፡፡

በትምህርት ቤት ደረጃ በተዘጋጁት ፈተናዎች ላይ የተደረጉ ጥናቶችም ቢሆኑ በሁለት ምድብ ተከፍለው ሊታዩ የሚችሉ ናቸው፡፡ ይኸውም የተወሰኑ ጥናቶች በአጠቃላይ የቋንቋው ክሂሎችና ዕውቀቶች ላይ የሚያተኩሩ ሲሆኑ፣ ሌሎች ጥናቶች ደግሞ በተወሰኑ የቋንቋው ክሂሎች ወይም ንኡሳን ክሂሎች ላይ በማተኮር የተደረጉ ናቸው፡፡ ይህ ጥናት በትምህርት ቤት ደረጃ በተዘጋጁት ፈተናዎች አጠቃላይ የቋንቋ ይዘት ግመገማ ላይ ትኩረት ከሚያደርጉ ጥናቶች ጋር የሚመደብ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጥናቶች ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡

አጥኚው ባገኘው መረጃ መሰረት በትምህርት ቤት ደረጃ የተዘጋጁትን የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች በመገምገም ቀዳሚ ስራ ሆኖ የተገኘው ሰለሞን ደስታ በ 1976 ዓ.ም ‹‹በአዲስ አበባ በአራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ 1975 ዓ.ም የተሰጡ የአማርኛ ፈተናዎች ግምገማ›› በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለ ቢ.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበው ጥናት ነው፡፡ አጥኚው በጥናታቸው በየትምህርት ቤቱ የተዘጋጁት ፈተናዎች ከጠንካራ ጎን ይልቅ ደካማ ጎንን ጎልቶ እንደሚታይባቸው አመልክተዋል፡፡

እንደ ጥናቱ ባለቤት አገላለፅ ፈተናዎቹ በመርሀ-ትምህርቱ ወይም መማርያ መፅሃፍ አለመመስረታቸውና ከቋንቋ ትምህርት ውጭ የሆኑ ጥያቄዎች ማካተታቸው እንዲሁም የተመሰረቱበት ዓላማ በውል አለመታወቅ የመሳሰሉ አበይት ደካማ ጎኖች የሚታዩባቸው ናቸው፡፡ ሰለሞን ያቀረቡት ጥናት በትምህርት ቤት ደረጃ በተዘጋጁ ፈተናዎች ላይ የተካሄደ በመሆኑና በተወሰነ መልኩ የፈተናዎቹን ይዘት ከመማሪያ መፅሐፍ አንጻር የተመለከተ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ቢኖረውም፣ ጥናቱ ከተካሄደበት ዘመንና ቦታ እንዲሁም ካተኮረበት ነጥብ አንጻር ሲታይ ከዚህ ጥናት የተለየ ነው፡፡

ከዚህ በመቀጠል የተገኘው ስራ የጥላሁን ንጉሴ (1989) ጥናት ሲሆን፣ ‹‹ሐረር ከተማ በሚገኙ ሁለት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ 1987 እና 1988 ዓ.ም የተሰጡ የአማርኛ ፈተና ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ ግምገማ›› በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለቢ.. ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡

የጥናቱ አቅራቢ በ 1987 እና በ 1988 ዓ.ም ለዘጠነኛ፣ ለአስረኛ እና ለአስራ አንደኛ ክፍል የተዘጋጁትን ፈተናዎች ከአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርትና መማሪያ መፅሐፍ ጋር ያላቸውን ግኑኝነት ገምግመዋል፡፡ በጥናታቸው ባገኙት ውጤት መሰረትም የተዘጋጁት ፈተናዎች ከመርሀ ትምህርቱም ሆነ ከመማሪያ መጽሀፉ ጠንካራ ግኑኝነት እንዳላቸው አመልክተዋል፡፡ ይህ ጥናትም ከተካሄደበት ዘመንና ቦታ እንዲሁም ፈተናዎቹ ከተነጻጸሩበት መርሀ ትምህርቱና መማሪያ መጽሐፍ የአገልግሎት ዘመን እና ጥናቱ ካተኮረባቸው የክፍል ደረጃዎች ሲታይ ልዩነት ያለው ሲሆን፣ በትምህርት ቤት ደረጃ የተዘጋጁት ፈተናዎች ከመርሀ ትምህርትና መማሪያ መፅሐፍ አንጻር መገምገሙ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳሰለዋል፡፡

ሌላው በትምህርት ቤት ደረጃ በተዘጋጁት የአማርኛ ፈተናዎች ላይ ጥናት ያደረገው በለጠ ያዕቆብ ነው፡፡ በለጠ (1995) ‹‹ለዘጠነኛ ክፍል የሚዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ለደረጃ ከሚቀርበው ትምህርት ጋር ያላቸው የይዘት አግባብነትና ያጠያየቅ ብቃት ትንተና›› በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናት በ 1994 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገኙ አስር የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለዘጠነኛ ክፍል የተሰጡት የማጠቃለያ ፈተናዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ጥናቱ ፈተናዎቹን በዘጠነኛ ክፍል መርሀ ትምህርትና መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ካሉት ይዘቶችና የመስኩ ባለሙያዎች ከሚያቀርቧቸው የአጠያየቅ ብቃት አንጻር ገምግሟቸዋል፡፡ በውጤቱም ፈተናዎቹ በመርሀ ትምህርቱም ሆነ በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ካሉት ይዘቶች ጋር ያላቸው ግኙኝነት ጠንካራ እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡ በለጠ ያቀረቡት ጥናት የፈተናዎቹ ይዘት ከመርሀ ትምህርትና መማሪያ መፅሀፍ አንጻር በመመልከቱ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ቢሆንም ጥናቱ ካተኮረበት የክፍል ደረጃ፣ ጥናቱ ከተካሄደበት ጊዜና ቦታ አንጻር ሲታይ ግን ከዚህ ጥናት የሚለይ መሆኑን ማስተዋል ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ እስካሁን ድረስ በትምህርት ቤት ደረጃ በሚዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ላይ የተካሄዱ ጥናቶች የፈተናዎቹ ይዘት ከመርሀ ትምህርቱና ከመማሪያ መፅሐፍ ይዘቶች አንጻር የገመገሙ በመሆናቸው ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉ ሁነው ተገኝተዋል። ነገር ግን ጥናቶቹ ከተካሄዱበት ዘመንና ቦታና እንዲሁም ካተኮሩበት የክፍል ደረጃ አንጻር ሲታይ ግን ግኑኝነት የሌላቸው መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል።

ቀደምት የጥናት ስራዎቹ የፈተናውን አጠቃላይ ብቃት በጥቅል መገምገም ወይም የይዘት ተገቢነቱና የአጠያየቅ ብቃት በአንድነት በመገምገም ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ፣ ይህ ጥናት ግን የፈተናዎችን የይዘት ተገቢነት ደረጃን በተናጠል በመገምገም ላይ ብቻ ተወስኖ የሚካሄድ ጥናት በመሆኑም ከሌሎቹ የተለየ ያደርገዋል።

ምዕራፍ ሶስት:-የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት የትምህርት ቤት መደበኛ መርሀ ግብር መሰረት አድርገው መምህራን በሚያዘጋጁት ትምህርት ቤት አቀፍ ፈተናዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። በትምህርት ቤት ከሚዘጋጁት ፈተናዎች መካከል ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚዘጋጁትን የአስረኛ ክፍል መደበኛ የሆኑትን ማለትም የሰሚስተር አጋማሽ፣ የማጠቃለያና የሞዴል ፈተናዎች ላይ ያተኮረ ሲሆን እነዚህ ፈተናዎች ለደረጃው ከቀረበው መማሪያ መፅሐፍ አንጻር ያላቸውን የይዘት ተገቢነት ደረጃ መፈተሽ የጥናቱ ዋና ተግባር ነው።

በጥናቱ ሂደት በናሙናነት ከተመረጡ ትምህርት ቤቶች ለአስረኛ ክፍል የቀረቡት የተተኳሪው ቋንቋ ፈተናዎች እና ለክፍል ደረጃው በቀረበ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ያሉት ይዘቶች ሰብስቦ ለማጥናት ጥረት የሚደረግ ሲሆን፣ ከነዚህ የሚገኘውን መረጃ ለማጠናከርና ተጨማሪ መረጃ ለማግኘትም ፈተናዎቹን ከሚያዘጋጁ መምህራን ጋር ቃለ-መጠይቅ ተካሂዷል። ስለዚህ የሚካሄደው ጥናት በዋናነት የሰነድ ምርመራ (document analysis) የተባለው የምርምር አይነት ነው። በዘህም መሰረት ይህን ጥናት ለማካሄድ አይነታዊ የምርምር ዘዴ (Qualitative Research) እና አህዛዊ (Quantitative Research) የምርምር ዘዴዎች በጥምረት ተጠቅሟል።

3.1 የናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት ለማካሄድ ያተኮረበት ክልል፣ ዞን፣ ትምህርት ቤቶችና የክፍል ደረጃ እንዲሁም ለቃለ መጠይቅ የቀረቡ መምህራን ለመምረጥ የተከተላቸው የናሙና ስልቶች ከዚህ ቀጥሎ ቀርበዋል።

3.1.1 የጥናቱ ክልልና ዞን ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ በትግራይ ክልል ሰሜናዊ ምዕራብ ዞን በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ላይ ያተኮረ ሲሆን ቦታውም አጥኚው ካለው የጊዜና የፋይናንስ አቅም አንጻር አንዲሁም በአካባቢው በመደረው ለሶስት አመት በማገልገሉ ካለው ልምድና ቅርበት አንጻር በአመቺ የናሙና ስልት የተመረጠ ነው።

3.1.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

በተጠቀሰው የጥናቱ ቦታ በ2002 ዓ.ም የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን በመቀበል ያስተምሩ የነበሩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ስድስት ሲሆኑ፣ ለሁሉም ትምህርት ቤቶች እኩል እድል የሚሰጠውን ቀላል የእጣ ናሙና (Simple Random Sampling) በመጠቀም ሶስቱን በጥናቱ እንዲከታተሉ ተደርጓል።

3.1.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በናሙናነት በተመረጡ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአጠቃላይ አስራ አንድ የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን ይገኛሉ። ከሁሉም ትምህርት ቤቶች ተመጣጣኝ መረጃ ለማግኘት ሲባል ስብጥር የድርሻ ናሙና (Proportionate stratified sampling) ስልት በመጠቀም ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ሁለት ሁለት መምህራን በጥናቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጓል።

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ጥናቱ ፈተናዎች ያላቸውን የይዘት ተገቢነት ደረጃ የሚመለከት እንደመሆኑ መጠን በዋናነት የሚከተለው የምርምር አይነት የሰነድ ምርመራ መሆኑ ተገልጿል። በመሆኑም በዚህ ጥናት አስፈላጊውን መረጃ የሚሰበሰብባቸው የጥናቱ የመረጃ ምንጮች የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ይዘቶች፣ በ 2002 እና 2003 ዓ.ም ለክፍል ደረጃው የቀረቡትን የተተኳሪው ቋንቋ ትምህርት ቤት አቀፍ ፈተናዎች ናቸው።

ቀደም ሲል እንደተገለፀው አጥኚው ከተጠቀሱት የመረጃ ምንጮች የሚገኘውን መረጃ ለማጠናከር ይረዳ ዘንድ ከፈተና አዘጋጅ መምህራን የተወሰነ መረጃ መውሰዱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል። በዚህ መሰረት የትምህርት ቤቶቹ የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አስተማሪዎችም የዚህ ጥናት ሌሎቹ የመረጃ ምንጮች ናቸው።

በአጠቃላይ ይህ ጥናት የአስረኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍና ፈተናዎች እንዲሁም ከአስተማሪዎች የተገኘውን መረጃ በግብአትነት የሚጠቀም ሲሆን የተጠቀሱ ሰነዶችን በመፈተሽና ቃለ መጠይቅ በማካሄድ መረጃዎችን በመሰብሰብ ለመተንተን ተሞክሯል።

3.3 የመረጃ ትንተና ዘዴ

ቀደም ባሉት ክፍሎች እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች እና ለክፍል ደረጃው የቀረቡት ትምህርት ቤት አቀፍ ፈተናዎች ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ያላቸውን ተመጣጣኝ ውክልና በመፈተሽ የፈተናዎቹን የይዘት ተገቢነት ደረጃ መገምገም ነው።

በዚህ መሰረት በመማሪያ መፅሐፉና በፈተናዎቹ የተካተቱ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ብዛት ወይም ሽፋን በቁጥርና በመቶኛ በማስቀመጥ ያላቸውን ተመጣጣኝነት እንዲተነተን ተደርጓል። በመማሪያ መፅሐፉ በእያንዳንዱ የቋንቋ ትምህርት ይዘት ስር የሚገኙ የመልመጃ መመሪያዎች (instructions) እና አጫጭር ማብራሪያዎች እንዲሁም በፈተናዎቹ የተካተቱ ጥያቄዎች ቁጥር የይዘቶቹ ሽፋን ወይም ብዛት የሚገልፅ እንዲሆን ተደርጎ ተወስዷል።

የይዘቶቹ ተመጣጣኝነት በቁጥርና በመቶኛ ከመግለፅ በተጨማሪ የደረጃ ልዩነት ዝምድና አመልካች ስሌት (Rank difference correlation coefficient) በመጠቀም ይዘቶቹ ያላቸው ተመጣጣኝ ዝምድና እንዲገልፅ ተደርጓል። ይህ ስሌት ይዘቶቹ በመማሪያ መፅሐፉም ሆነ በፈተናዎቹ ከተሰጣቸው ሽፋን አንጻር ደረጃ በመስጠት ያሳዩት የደረጃ ልዩነት የሚያስቀምጥ ሲሆን ከጠቅላላ ስብስቦች አንጻር በማስላት ውጤቶችን የሚገልፅ ነው። የስሌቱ ውጤትም የየራሳቸው ትርጉም ያላቸው ሲሆን ቀመሩ የሚከተለው ይመስላል።

$$P = 1 - \frac{6x\sum D^2}{N(N^2-1)}$$

P= አጠቃላይ የተዛምዶ ደረጃ የሚገልፅ አሀዛዊ መረጃ

$\sum$ = ድምር ውጤት

D = የደረጃ ልዩነት

N = የስብስቦች ብዛት

የዚህ ስሌት ውጤት ወይም P= 1.00 ከሆነ ፍፁም አወንታዊ (ቀጥተኛ) ግንኙነት አለ

= 0.00 ከሆነ ምንም አይነት ግኑኝነት የለም

= -1.00 ከሆነ ፍፁም አሉታዊ (ኢ-ቀጥተኛ) ግኑኝነት

አለ ማለት ነው Gronulonad (1981)።

ይህን ስልት በመጠቀም እንዲሁም ይዘቶቹን በቁጥር በመቶኛ በመግለፅ ከሰነዶቹ የተገኘውን መረጃ ለመተንተን ተሞክሯል። ከቃለ-መጠይቁ የተገኘው መረጃ ደግሞ ከመረጃ ሰጪዎች የተሰጠውን ምላሽ ግኑኝነትና አንድምታው ከነማጠቃለያው በገለጻ መልክ በማቅረብ ተተንትኗል።

ምዕራፍ አራት:-የመረጃ ትንተና እና ውጤት

በዚህ ምዕራፍ ጥናቱ ይዞት የተነሳውን አላማ ከግብ ለማድረስ ያስችለው ዘንድ የሰበሰባቸው መረጃዎች ይቀርባሉ፣ የመረጃዎቹን ውጤትና ግንኙነት በተመለከተም ማብራሪያ ይሰጣል።

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ይህ ጥናት በዋናነት ይዞት የተነሳው አላማ በትግራይ ክልል ሰሜናዊ ምዕራብ ዞን በሚገኙ ሶስት በናሙናነት በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚዘጋጁ የችሎታ መለኪያ ፈተና የሚባሉት (ትምህርት ቤት አቀፍ) የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችን ይዘት ለደረጃው ከተዘጋጀ የቋንቋው መማሪያ መፅሐፍ ይዘቶች አንጻር ያላቸውን የይዘት ተገቢነት ደረጃ ለመገምገም ነው።

ጥናቱ የፈተና የይዘት ተገቢነት ደረጃን ለመጠበቅ ከፍተኛ ሚና የሚጫወተውን የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ የተባለው ስልት የቋንቋ ፈተናው በሚያዘጋጁ የትምህርት ቤቶቹ መምህራን ዘንድ ምን ያህል የተለመደ መሆኑን ለመፈተሽ ጭምር ያለመ ሲሆን፣ እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት ደግሞ የሰነድ ምርመራና የቃል መጠይቅ ተካሂዶ አስፈላጊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተሞክሯል። ጥናቱ የሰበሰባቸው መረጃዎች የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ይዘቶች እና የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ቤት አቀፍ ፈተናዎች እንዲሁም ከቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ሲሆኑ የመረጃዎቹ ትንተና እንደሚከተለው ቀርበዋል።

4.1 ከሰነዶች የተገኙ መረጃዎች

4.1.1 የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ

4.1.1.1 የመፅሐፉ አጠቃላይ ገፅታ

ጥናቱ በመረጃ ምንጭነት ከተጠቀመባቸው መካከል ለአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ አንዱ ነው። በናሙናነት በተመረጡ ትምህርት ቤቶች አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኘው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ

መፅሐፍ በ 1992 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስተር አሳታሚነት ለመጀመሪያ ጊዜ ታትሞ በ 1997 ዓ.ም ደግሞ ተሻሽሎ የቀረበው መፅሐፍ ነው።

የመማሪያ መፅሐፉ በአስራ ስምንት ምዕራፎች የተከፋፈሉ ልዩ ልዩ ይዘቶችን ያካተተ ሲሆን፣ በአነስተኛ ቅርፅና ተማሪዎች ለአያየዝ በሚያመቻቸው መልኩ የቀረበ ነው። አብዛኛዎቹ የመፅሐፉ ምዕራፎች በአንብቦ መረዳት፣ ፅሑፍ፣ ንግግርና ማዳመጥ እንዲሁም በሰዋሰውና በሥነ ፅሑፍ ክፍል ስር የተካተቱ ልዩ ልዩ መልመጃዎችና ማብራሪያዎች የያዙ ናቸው። አንዳንድ ምዕራፎች ደግሞ ምንባቡን ብቻ ወይም በተወሰነ ክፍሎች ስር የተቀመጡ መልመጃዎችን ብቻ ይዘው የቀረቡ ናቸው።

4.1.1.2 በመማሪያ መፅሐፉ የሚገኙ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች

ጥናቱ ለማነጻጸርያ የሚወስዳቸው ይዘቶች መማሪያ መፅሐፉ አራቱን ክሂሎችና ሁለቱን የፅውቀት ዘርፎች ለማዳበር ያስችላሉ በማለት በተለያዩ ምዕራፎች ርዕስ ስር ያካተታቸው ልዩ ልዩ የመለማመጃ መመሪያዎች እና ማስታወሻዎች (ማብራሪያዎች) ናቸው። በእያንዳንዱ መመሪያና ማስታወሻ ለማለማመድ የተፈለገ አንድ የቋንቋ ትምህርት ይዘት ይንጸባረቃል። ከዚህ በመነሳት ለጥናት በተመረጠው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ ያሉት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችና ለነዚህ ይዘቶች የቀረቡት የመልመጃ መመሪያዎች ማስታወሻዎች ቀጥለው ቀርበዋል።

በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የንባብና የፅሕፈት ክሂሎች ከሌሎቹ በተሻለ ሁኔታ በምዕራፎቹ የተካተቱ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሲሆኑ የማዳመጥ ክሂል ደግሞ በጣም ዝቅተኛ ስርጭት ያለው ይዘት ነው።(ለዝርዝሩ አባሪ አንድን ይመልከቱ)

ለክፍል ደረጃው በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ውስጥ በቃላት ትምህርት ላይ የሚያተኩሩና የቃላት ቀጥተኛና አውዳዊ ፍቺ እንዲሁም ተቃራኒና ተመሳሳይ ፍቺ የሚጠይቁ ይዘቶች ይገኛሉ። በመሆኑም ለትንተናው ያመች ዘንድ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ለብቻ ለይቶ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። የቃላት ትምህርት በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ በብዛት ተካቶ የሚገኘው በንባብና ፅሕፈት ክሂሎች ትምህርት ውስጥ ነው። ይህም ከምንባብ የተውጣጡ ቃላት

አይዳዊ ፍቺ ስጡ፣ ተመሳሳይና ታቃራኒ ፍቺ ፈልጉ፣ ቀጥተኛ ትርጉም ስጡ፣ ቃላቱን በሌላ አገላለፅ አብራሩ ወዘተ. በሚሉ መመሪያዎች የቀረበ ነው።

ሌሎች የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በውስጣቸው ያካተታቸው ንኡሳን ይዘቶች ስንመለከት፤ በማዳመጥና በንግግር ክሂሎች ውስጥ የተለያዩ ጭውውቶች፣ ክርክሮችና ውይይቶችን ማድረግና ማዳመጥ፣ ሀሰብን በተጠየቃዊ አስተሳሰብ መግልፅ፣ በእውነትና በግል አስተያየት መካከል ያለ ልዩነት መረዳት፣ የመንስኤና ውጤት ግኙኝነት፣ የተለያዩ ነገሮች ማወዳደርና ማነጻጸር፣ የውሳኔ ሀሳብ ወይም አስተያየት መስጠት የሚሉ ጉዳዮች የተካተቱ ሲሆን በንባብ ክሂል ከቀረቡት ደግሞ ከቀረበው ምንባብ ዝርዝር መረጃዎችን ለይቶ ማውጣት፣ ፍሬ ሀሳብን መረዳት መቻል፣ አንድን ሀሳብ በራስ አባባል መግልፅና የቀረበው ምንባብ ክራስና አካባቢ ጋር በማገናዘብ መረዳት የሚሉት ንኡሳን ይዘቶች ይገኛሉ።

በሥነ- ልሳን ስር የተካተቱ ንኡሳን ይዘቶች የቋንቋ መሰረተ-ሀሳቦችና ፣ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ማረም፣ የእርባታና የምስረታ ምዕላድ፣ የሀረግ አይነቶችና ተግባር፣ ዓረፍተ-ነገርና ሐረጎችን መመስረትና መለየት እንዲሁም ጥብቀት የሚመለከቱ ናቸው።

በሥነ- ፅሑፍ በኩል ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮች፣ የልብ ወለድ አላ ባዊያን የአጭርና ረጅም ልቦለድ ልዩነት፣ ቃላዊ ግጥሞች፣ ግጥም ወደ ዝርው መለወጥ እንዲሁም የዘይቤ አይነቶች የተካተቱ ሲሆን የደብዳቤ አይነቶችና ክፍሎች፣ አንቀፅና የአንቀፅ ቅርፆች፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም፣ ዘገባና የዘገባ አቀራረብ፣ የሕይወት ታሪክና ግለ ታሪክ፣ ጅምር ታሪኮችን መጨረስ እንዲሁም የተሰጡ ሀሳቦችን በራስ አገላለፅ አስፋፍቶ መጻፍ የሚሉ ንኡሳን ይዘቶች ደግሞ በፅሕፈት ክሂል ስር የተካተቱ ናቸው።

ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዳቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መፅሐፉ ያላቸውን የይዘት ሽፋን ምን ያህል እንደሆነ በቁጥርና በመቶኛ ተሰልቶ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 1.1 የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በመፅሐፍ ያላቸው የይዘት ሽፋን

ተ.ቁ	የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች	የይዘት ሽፋን	
		በቁጥር	በመቶኛ
1	የንባብ ክሂል	46	23%
2	የፅሕፈት ክሂል	41	20.5%
3	የንግግር ክሂል	33	16.5%
4	የማዳመጥ ክሂል	08	4.0%
5	የሥነ- ልሳን ዕውቀት	28	14.5%
6	የሥነ- ፅሁፍ ዕውቀት	33	16.5%
7	የቃላት ትምህርት	11	5.5%
ድምር		200	100%

በመማሪያ መፅሐፉ ከተካተቱት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች መካከል 23% ወይም አርባ ስድስት የመልመጃ መመሪያዎችና ማብራሪያዎች በመያዝ ከፍተኛው የመፅሐፉ የይዘት ሽፋን የያዘው የንባብ ክሂል መሆኑ በሰንጠረዥ 1.2 ከቀረበው መረጃ መረዳት ይቻላል። ከንባብ ክሂል ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የምናገኘው ደግሞ የፅሀፈት ክሂልን የተመለከተ ይዘት ሲሆን 20.5% ወይም አርባ አንድ የመልመጃ መመሪያዎችና ማብራሪያዎችን ይዞ ይገኛል። እያንዳንዳቸው 16.5% ወይም ሰላሳ ሶስት የመልመጃ መመሪያዎችና ማብራሪያዎችን በመያዝ ቀጥሎ ያለውን ደረጃ ይዘው የሚገኙት የንግግር ክሂልና የሥነ ጽሁፍ እውቀት ይዘቶች ናቸው። የሥነ- ልሳን ዕውቀት ከመፅሐፉ ጠቅላላ ይዘት ሀያ ዘጠኝ የመልመጃና መመሪያዎችና ማብራሪያዎችን በመያዝ ወይም 14.5% ቀጣዩን ደረጃ የያዘ ሲሆን የቃላት ትምህርት 5.5% እንዲሁም የማዳመጥ ክሂል ደግሞ 4.0% በመያዝ የመጨረሻውን ደረጃ ላይ ይገኛሉ።

በአጠቃላይ በሰንጠረዡ ካለው አሀዛዊ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የንባብና ፅሕፈት ክሂሎች በከፍተኛ ደረጃ ፣ የንግግር ክሂልና የሥነ- ፅሁፍ ዕውቀት በተመሳሳይ መጠን በሁለተኛ ደረጃ ፣ የሥነ- ልሳን እውቀት በሶስተኛ ደረጃ እንዲሁም የቃላት ትምህርትና የማዳመጥ ክሂል ይዘትን ደግሞ በአራተኛ ደረጃ ትኩረት ያደረገ መሆኑን ነው።

4.1.2 የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ይዘት

አጥኚው የሰበሰባቸው ፈተናዎች በናሙናነት በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ2003 ዓ/ም በአንደኛው መንፈቅ አመት የተዘጋጁት የሰሚስቴር አጋማሽና ፈተናን ጨምሮ በ2002 ዓ/ም በአንደኛውና በሁለተኛው መንፈቅ አመት የተዘጋጁት የሰሚስቴር አጋማሽ ፈተና ፣ የሲሚስተር ማጠቃለያ አንዲሁም ሞዴል ፈተናዎች ናቸው።

ፈተናዎቹ ከቀረቡበት ወቅት አንጻር በመከፋፈል በውስጣቸው ያሉትን የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ዝርዝርና መጠን እንደሚከተለው ቀርቧል።

4.1.2.1 የ2002 ዓ/ም የሴሚስተር አጋማሽ ፈተናዎች ይዘት

ይህ በትምህርት ቤቶቹ መርሀ- ግብር መሰረት ከሚሰጡ ፈተናዎች መካከል በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጥ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ከ 25-30% የሰሚስተሩን ውጤት የሚሸፍንነው። በ2002 ዓ.ም በመጀመሪያው መንፈቅ አመት በሶስቱ ትምህርት ቤቶች የተሰጠው የሰሚስተር አጋማሽ ፈተና ይዘት የሚከተለውን ይመስላል ።

ሰንጠረዥ 1.2 በ 2002ዓ.ም የተዘጋጀ የሰሚስቴር አጋማሽ ፈተናዎች ይዘት

ተ.ቁ	ይዘት	የሽሬ ሁ/ደ/ት/ቤት		እ/ጉና ሁ/ደ/ት/ቤት		ዓ/ዳ/ሁ/ደ/ት/ቤት		ጠቅላላ ድምር	
		በቁጥር	በመቶኛ	በቁጥር	በመቶኛ	በቁጥር	በመቶኛ	በቁጥር	በመቶኛ
1	የፅሕፈት	2	10%	-	-	-	-	2	3.64%
2	የንግግር	-	-	2	10%	-	-	2	3.64%.
3	የማዳመጥ	-	-	-	-	-	-	-	-
4	የንባብ	-	-	-	-	-	-	-	-
5	የሥነ ልሳን	5	25%	-	-	10	66.67%	15	27.27%
6	የሥነ ፅሁፍ	13	65%	1	5%	3	20%	17	30.90%
7	የቃላት	-	-	17	85%	2	13.33%	19	34.55%
	ድምር	20	100%	20	100%	15	100%	55	100%

በሰንጠረዡ የተመለከተው መረጃ እንደሚያሳየው በ2002 ዓ.ም በሶስቱ ትምህርት ቤቶች ከተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ይዘት 34.55% የሚሆነው ቃላትን በተመለከተ ነው። ቃላትን በተመለከተ የቀረበው ይዘትም ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸው ቃላት ማዛመድና ጥቅል ቃላትን በተመለከተ የቀረበው ይዘትም ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸው ቃላት ማዛመድና ጥቅል ስያሜን በመስጠት ላይ ያተኮረ ነው። ከቃላት ትምህረት ቀጥሎ በፈተናው ትኩረት

ያገኘው የቋንቋ ትምህርት ይዘት የስነ- ጽሁፍ እውቀት ነው። ይህም ከጠቅላለው ይዘት 30.90% የሚሸፍን ሲሆን በስነ-ግጥም፣በልብ-ወለድ አላባዊያን፣ በምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮች ላይ የሚያተኩር ነው። የስነ-ልሳን ይዘት የፈተናው 27.27% በመያዝ በሶስተኛ ደረጃ የተቀመጠ የፈተናው ይዘት አካል ሲሆን ስለ ቋንቋ መሰረተ ሀሳቦች፣ስለ ቅጥያ ምዕላዶችንና አገልግሎታቸው የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ይሏል። የዕሕፈት ፈተና የንግግር ክሂሎች በተመሳሳይ መጠን በ3.64% ያህል በፈተናው ይዘት የተካተቱ ሲሆኑ የንባብና የመዳመጥ ክሂሎች ደግሞ በፈተናው ላይ ያልተካተቱ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ናቸው።

የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በፈተናው የተሰጣቸው ሽፋን በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ከተሰጣቸው ትኩረት አንፃር ሲታይ ተመጣጣኝ የሆነ ውክልና አላቸው ለማለት አያስደፍርም። የመማሪያ መፅሐፉ ይዘቶች ሽፋን በሚዘረዝረው ሰንጠረዥ እንደተመለከተው መማሪያ መፅሐፉ 43.5% በመስጠት ከፍተኛ ሽፋን የሰጣቸው ይዘቶች የንባብና የፅሕፈት ክሂሎችን ሲሆን በፈተናው ግን ለእነዚህ ይዘቶች የተሰጠው ትኩረት ከአራት በመቶ ያነሰ ነው። ከዚህ አንፃር ሲታይ ፈተናው የመማሪያመፅሃፉ ይዘቶችን ተመጣጣኝ በሆነ ውክልና ያካተተ ነው ለማለት አይቻልም።

በአጠቃላይ በ2002 ዓ.ም በሶስቱ ትምህርት ቤቶች የተዘጋጁት የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የሰሚስተር አጋማሽ ፈተና ለቃላት ትምህርት፣ ለሥነ- ፅሁፍና ስነ- ልሳን የእውቀት ዘርፎች ሰፊ ሽፋን የሰጠ፣ የንግግርና የፅህፈት ክሂል ይዘቶች ደግሞ በተውሰነ ደረጃ ያካተተነው። በፈተናው ውስጥ ያተካተቱት የንባባና የንግግር ክሂል ይዘቶች ፈተናው እስከ ተሰጠበት ድረስ በትምህርትነት እንዲቀርቡ በመማሪያ መፅሐፉ የተጠቆመ ቢሆንም የፈተና አዘጋጆቹ ትኩረት አላደረጉበትም። በመሆኑም ይህ ፈተና የሰሚስተር አጋማሽ ፈተና እንደ መሆኑ መጠን ሁሉም የቋንቋ ተምህርት አላካተተምና በደፈናው ተገቢነት የለውም ተብሎ ባይወቀስም እነዚያን ይዘቶች ለመመዘን የሚያስችሉ ጥያቄዎች ማካተት እንደነበረበት አያከራክርም።

4.1.2.2 የ2002 ዓ/ም አንደኛ መንፈቅ አመት ማጠቃለያ ፈተናዎች ይዘት

ይህ ፈተና በትምህርት ዘመኑ በመጀመሪያ መንፈቅ አምት (አንደኛ ሲሚስተር) መጨረሻ ላይ የሚዘጋጅ ነው። ፈተናው አብዛኛውን ጊዜ 50% (ሀምሳ በመቶ)

የሚሆነውን የተማሪዎች ውጤት ይሸፍናል። በሶስቱ ትምህርት ቤቶች የተዘጋጁት የአንደኛ መንፈቅ አመት ማጠቃለያ ፈተናዎች ያላቸው ይዘት ምን እንደሚመስል ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 1.3 በ2002ዓ.ም የተዘጋጁት የአንደኛ መንፈቅ አመት ማጠቃለያ ፈተናዎች ይዘት

ተ.ቁ	ይዘት	የሽሬ/ሁ/ደ/ት/ቤት		የእ/ጉ/ሁ/ደ/ት/ቤት		የዓ/ዳ/ሁ/ ደ/ት/ቤት		ጠቅላላ ድምር	
		በቁጥር	በመቶኛ	በቁጥር	በመቶኛ	በቁጥር	በመቶኛ	በቁጥር	በመቶኛ
1	ማዳመጥ ክሂል	-	-	-	-	-	-	-	-
2	ንግግር ክሂል	-	-	-	-	1	2.85%	1	0.95%
3	የንባብ ክሂል	7	20%	10	28.57%	-	-	17	16.19%
4	የፅህፈት ክሂል	1	2.85%	8	22.85%	2	5.71%	11	10.47%
5	የሥነ ልሳን	16	45.71 %	4	11.43%	12	34.28%	32	30.48%
6	የሥነ ፅሁፍ	10	28.57 %	5	14.28%	16	45.71%	31	29.53%
7	የቃላት ትምህርት	1	2.85%	8	22.85%	4	11.43%	13	100%
	ድምር	35	100%	35	100%	35	100%	105	100%

በ2002ዓ.ም ለአንደኛው መንፈቅ አመት ማጠቃለያ ፈተና የተዘጋጁት ጥያቄዎች 60.01% ያህሉ በስነ- ልሳንና ሥነ- ፅሁፍ የእውቀት ዘርፎች ላይ ያተኮሩ መሆናቸው በሰንጠረዡ ከቀረበው መረጃ መረዳት ይቻላል። በፈተናው ከቀረቡት የስነ- ልሳን ይዘቶች መካከል የቋንቋ መሰረተ ሀሳቦች፣ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ማረም፣ቅጥያ ምእላዶችን መለየት፣ የሀረግ አይነቶችን መለየት እንዲሁም የተለያዩ ቃላትና ሐረጋት በዓረፍተ-ነገር ውስጥ ያላቸውን ተግባር መለየት የሚሉት ይገኙባቸዋል። በስነ-ፅሁፍ በኩል ደግሞ የልቦለድ አላባዊያን ምንነትና ተግባር፣ የግጥም አይነቶችና ክፍሎች፣ የተለያዩ ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮችን በተመሳሳይ ማዛመድ እና አጭ ትርጉም መፈለግ የመሳሰሉ ጥያቄዎች ይገኙበታል። ከነዚህ በመቀጠል በፈተናው ትኩረት የተሰጠባቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች የንባብ ክሂልንና የቃላት ትምህርት ሲሆኑ፣ የንባብ ክሂል 16.19% በመያዝ የቃላት ትምህርት ደግሞ 12.38% በመያዝ በተከታታይ ይገኛሉ።

በንባብ ክሂል በኩል በሁለቱም ትምህርት ቤቶች በተዘጋጁት ፈተናዎች ላይ ለንባብ የቀረበ ፅሁፍ ያለ ሲሆን ተማሪዎች አንብቦ የመረዳትና ዝርዝር መረጃዎችን ለይቶ የማውጣት ችሎታቸውን የሚለኩባቸው ጥያቄዎች ተካትተውበት ይገኛል። የቃላት ትምህርት በተመለከተም በአውድ ወስጥ እና ከአውድ ውጭ የተለያዩ ቃላት ቀርበው አቻ ትርጉም እንዲሰጣቸው በጥያቄነት ተካትተዋል።

የፅህፈት ክሂል በፈተናው መጠነኛ ትኩረት የተሰጠው ሌላ የቋንቋ ትምህርት ይዘት ነው። ክሂሉ በፈተናው የተሰጠው ሽፋን 10.47% የሚያክል ሲሆን በሁሉም ትምህርት ቤቶች በተወሰነ መልኩም ቢሆን በፈተናዎቹ ይዘት እንዲካተተ የተደረገ ነው። በፈተናው አንቀፅንና የድርሰት ክፍሎችን የተመለከቱ ጥያቄዎች ተካትተው ይገኛሉ።

በ2002ዓ.ም የተዘጋጁት የአንደኛ መንፈቀ አመት የማጠቃለያ ፈተናዎች ላይ ለእያዳንዱ የቋንቋ ትምህርት ይዘት የተሰጠው ትኩረት በመማሪያ መፅሐፉ ከተሰጠው ሽፋን አንጻር ሲታይ ሙሉበሙሉ ተመጣጣኝነት ይታይበታል ለማለት አያስደፍርም። በሰንጠረዥ 1.1 ላይ እንደተመለከተው በመማሪያ መፅሐፉ ካሉት ይዘቶች መካከል ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው የንባብና የፅሕፈት ክሂሎች ሲሆኑ በፈተናው ደግሞ የስነ-ልሳንና የስነ- ፅሑፍ ይዘቶች ከፍተኛ ትኩረት ተሰጧቸዋል። የንባብና የፅሕፈት ክሂሎች በአማካይ 13.33% በፈተናው ካለው ጠቅላላ ይዘት የሚሸፍኑ ሲሆኑ በመማሪያ መፅሐፉ ደግሞ በአማካይ 21.75% ይሸፈናሉ። የተገለፀው አሃዛዊ መረጃ አንድ ይዘት በፈተና ላይ ሊኖረው ከሚገባ ሽፋን አንፃር ሲታይ በጣም ሰፊ ልዩነት ይታይበታል ለማለት ባይቻልም በመማሪያ መፅሐፉ 20.5% ሽፋን የተሰጣቸው የንግግርና የማዳመጥ ክሂሎችም በፈተናው የአንድ በመቶ ሽፋን እንኳ አለማግኘታቸው ፈተናው ይዘቶችን በተመጣጣኝ ውክልና በማካተት ረገድ ችግር እንዳለበት የሚያመለክት ነው።

4.1.2.3 የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ሞዴል ፈተና ይዘት

የትምህርት ሚኒስቴር ባስቀመጠው ስርአተ ትምህርት መሰረት ተማሪዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀውን ብሔራዊ ፈተና ወስደው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቅቃሉ። ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸውን ለዚህ ሀገራዊ ፈተና ዝግጅት ይረዳ ዘንድ በሁለተኛው መንፈቀ አመት ሞዴል ፈተናን ያዘጋጃሉ።

በሶስቱ ትምህርት ቤቶች በ 2002 ዓ.ም ለተማሪዎች የቀረበው የአማርና ቋንቋ ሞዱል ፈተና ምን ምን ይዘቶች በምን ያህል መጠን ያካተተ እንደሆነ ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ተመልክታል።

ሠንጠረዥ 1.4 የ 2002ዓ.ም የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ሞዱል ፈተና ይዘት

ተ.ቁ	በፈተናው የተካተቱ ይዘቶች	የሽፊ/ሁ/ደ/ት/ቤት		የእ/ጉ/ሁ/ደ/ት/ቤት		የዓ/ዳ/ሁ/ ደ/ት/ቤት		ጠ. ድምር	
		በቁጥር	በመቶኛ	በቁጥር	በመቶኛ	በቁጥር	በመቶኛ	በቁጥር	በመቶኛ
1	የማዳመጥ	-	-	-	-	-	-	-	-
2	የንግግር ክሂል	-	-	-	-	-	-	-	-
3	የንባብ ክሂል	-	-	5	7.14%	12	17.14%	17	9.44%
4	የፅሀፈት ክሂል	9	22.5%	-	-	11	15.71%	20	11.11 %
5	የሥነ ልሳን ዕውቀት	7	17.5%	26	37.14%	21	30.0%	54	30.0%
6	የሥነ ፅሁፍ ዕውቀት	22	55%	26	37.14%	22	31.42%	70	38.81 %
7	የቃላት ትምህርት	2	5.0%	13	18.57%	4	5.71%	19	10.56 %
	ድምር	40	100%	70	100%	70	100%	180	100%

በሰንጠረዥ የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው በ 2002 ዓ.ም ለአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበው የአማርኛ ቋንቋ ሞዱል ፈተና ይዘት 68.89% ወይም ከስድሳ ስምንት በመቶ በላይ የሚሆነው በሁለቱም የእውቀት ዘርፎች ማለትም በስነ- ልሳንና በስነ- ፅሑፍ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። በፈተናዎቹ የሀረግ አይነቶች፣ የሐረግ ተዋቃሪዎችና ተግባራት፣ የቋንቋ መሰረ-ሀሳቦች፣ ቅጥያ ምዕላዶችና ተግባሮቻቸው እንዲሁም የዓረፍተ-ነገር አይነቶች በስነ-ልሳን ትኩረት የተሰጠባቸው ጉዳዮች ሲሆኑ የግጥም አይነቶችና ክፍሎች፣ የልቦለድ አላባዊያንና ስልቶች፣ ተውኔት፣ ዘይቤ፣ ቅኔ እና የተለያዩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ደግሞ በስነ- ፅሁፍ በኩል የተካተቱ ርእስ ጉዳዮች ናቸው።

በፈተናዎቹ የተካተተው ሌላው ይዘት የቃላት ትምህርት ሲሆን፣ ይህም ከአጠቃላይ የፈተናዎቹ ይዘት 10.56% የሚሆነውን የሚሸፍንነው። ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት፣ አውዳዊ ትርጉም መስጠት እና ቃላትን በተገቢ ቦታ አስገብቶ ዓረፍተ-ነገሩን ማሟላት በሚሉ ንኡሳን ይዘቶች ዙርያ የሚያውጠነጥኑ የቃላት ትምህርት ጥያቄዎች በፈተናዎቹ ተካትተው ይገኛሉ።

ሞዴል ፈተናዎቹ ለክሊኖች የሰጡት ትኩረት 20.55% ወይም ከሀያ አንድ በመቶ በታች ሲሆን ይህም የንባብና የፅሐፍት ክሂልን ብቻ የሚሸፍን ነው። በፈተናዎቹ አንብቦ መረዳት ችሎታን ለመፈተሽ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን አስከትሎ የቀረበ ምንባብ እንዲሁም በፅህፈት ክሂል ዙሪያ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የአንቀጽ ባህሪያት፣ አይነትና ቅርፆች፣ ድርስትና የድርሰት ክፍሎች፣ የደብዳቤ ክፍሎች የተመለከቱ ጥያቄዎች ተካትተዋል። በሌላ በኩል ፈተናዎቹ የማዳመጥና የንግግር ክሂልን በተመለከተ አንድም ጥያቄ በይዘታቸው አላካተቱም። የሞዴል ፈተናው በነዚህ አበይት ይዘቶች ስር ያካተታቸው ንኡሳን ይዘቶች በመማሪያ መፅሐፉ ከተካተቱ ንኡሳን ይዘቶች አንጻር ሲታይ የተወሰነ ችግር ይታይበታል። ይኸውም በመማሪያ መፅሐፉ ያልተካተቱ ይዘቶች በፈተናው መካተታቸውን ነው። ለምሳሌ፡- በሥነ-ፅሁፍ ይዘት በኩል የቀረበው ቅኔን የሚመለከት ንኡስ ይዘት በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የማይገኝ ነው።

በአጠቃላይ የሞዴል ፈተናዎቹ ይዘት ሲታይ በስነ- ልሳንና ስነ- ፅሁፍ የእውቀት ዘርፎች ላይ በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት ያደረገ ሲሆን፣ የፅህፈት የንባብ ክሂል እንዲሁም የቃላት ትምህርትን በአንጻሩ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ አካትቶ የያዘ ነው። የማዳመጥና የንግግር ክሂል ደግሞ በፈተናዎቹ ዝግጅት ላይ ምንም አይነት ትኩረት ያልተሰጣቸው ወይም ፍፁም የተዘነጉ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሁነዋል።

4.1.2.4 የ 2003ዓ.ም የሰሚስቴር አጋማሽ ፈተናዎች ይዘት

ይህ ፈተና ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በትምህርት ዘመኑ በመጀመሪያው መንፈቅ አመት አጋማሽ ላይ ተዘጋጅቶ የሚቀርብ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ከ25-30% (ከሀያ አምስት እስከ ሰላሳ በመቶ) የሚሆነውን የተማሪዎች ውጤት የሚሸፍን ነው።

በተመረጡት ሶስት ትምህርት ቤቶች ለአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጁት የተተኳሪው ቋንቋ ፈተናዎች ያካተታቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችና መጠናቸው እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 1.5 የ 2003ዓ.ም የሰሚስቴር አጋማሽ ፈተናዎች ይዘት

ተ.ቁ	በፈተናው የተካተቱ ይዘቶች	የሽሬ/ሁ/ደ/ት/ቤት		የእ/ጉ/ሁ/ደ/ት/ቤት		የዓ/ዳ/ሁ/ደ/ት/ቤት		ጠ. ድምር	
		በቁጥር	በመቶኛ	በቁጥር	በመቶኛ	በቁጥር	በመቶኛ	በቁጥር	በመቶኛ
1	የማዳመጥ	-	-	-	-	-	-	-	-
2	የንግግር ክሂል	-	-	-	-	1	66.67 %	1	1.67%
3	የንባብ ክሂል	-	-	-	-	-	-	-	-
4	የፅህፈት ክሂል	-	-	1	4	-	-	1	1.6%7
5	የሥነ ልሳን ዕውቀት	6	30%	7	28%	5	33.33 %	18	30%
6	የሥነ ፅሁፍ	8	40%	8	32%	7	46.67 %	23	38.33 %
7	የቃላት ትምህርት	6	30%	9	36%	2	13.33 %	17	28.33 %
	ድምር	20	100%	25	100 %	15	100%	60	100%

በሠንጠረዥ የሰፈረው መረጃ እንደሚያለክተው በ 2003 ዓ.ም የተዘጋጁት የአስረኛ ክፍል የአመርኛ ቋንቋ የሰሚስቴር አጋማሽ ፈተናዎች ይዘት 38.33% (ሰላሳ ስምነት ነጥብ ሶስት በሞቶ) የሥነ- ፅሑፍ ዕውቀት 30% (ሰላሳ በመቶ) የሥነልሳን እውቀት 28.33% (ሀያ ስምንት ነጥብ ሶስት ሶስት በመቶ) የቃላት ትምህርት እንዲሁም የንግግርና የፅህፈት ክሂል እያዳንዳቸው 1.67% (አንድ ነጥብ ስድስት ሰባት በመቶ ያካተተ ነው። ምሳሌያዊና ፊሊጣዊ ንግግሮች፣ ዘይቤና የልቦለድ አለባዊያን በፈተናው ውስጥ የተካተቱ ስነ- ጽሁፋዊ ይዘቶች ሲሆኑ ምዕላድና የምዕላድ አይነቶች፣ የቋንቋ መሰረተ ሀሳቦች፣ ዓረፍተነገር እና ልዩ ልዩ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ማረም የሚሉት

ደግሞ ከስነ-ልሳን የእውቀት ዘርፍ የተካተቱ ይዘቶች ናቸው። የክርክር አተገባበር የተመለከተ ከንግግር ክሂል፣ የድርሰት አይነት በተመለከተ ከፅሕፈት ክሂል በፈተናው የተካተቱ ይዘቶች ሲሆኑ የቃላት ትምህርትን በተመለከተ ደግሞ ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸው ቃላትን ማዛመድ፣ ተቃራኒ ፍቺ መስጠት፣ አጠቃላይ ስያሜና አውዳዊ ፍቺ መስጠት የሚሉ ጥያቄዎች ይገኛሉ።

ፈተናው በንኡስነት ባካተታቸው ይዘቶች በኩል ከመማሪያ መጽሐፉ የሚጣጣም ቢሆንም ይዘቶቹ በመማሪያ መፅሐፉ ካላቸው ሽፋን አንፃር በተመጣጠነ መልኩ በማቅረብ ረገድ ግን ክፍተት ይታይበታል። በሰንጠረዥ 1.5 ላይ እንደሚታየው ከስድሳ ስምንት በመቶ በላይ በስነ-ልሳንና ስነ-ፅሁፍ ላይ የሚያተኩር ሲሆን መማሪያ መፅሐፉ ደግሞ ከስድሳ አራት በመቶ በላይ ትኩረት ያደረገው በክሂሎች ላይ ነው።ይሁን እንጂ ፈተናው ለክሂሎች የሰጠው ሽፋን 3.34% (ሶስት ነጥብ ሶስት አራት በመቶ) ብቻ ነው። ስለዚህ ፈተናው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን በትክክልና ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ አካታል ለማለት አይቻልም።

በአጠቃላይ የሰሚስቴር አጋማሽ ፈተናው በሁለቱም የእውቀት ዘርፎችና በቃላት ትምህርት ላይ ከፍተኛ ትኩት ያደረገ ሲሆን እነዚህም ከአጠቃላይ ይዘታቸው 96.66% (ዘጠና ስድስት ነጥብ ስድስት ስድስት በመቶ) የሚሆነው የሚሸፍኑ ናቸው። የቋንቋ ክሂሎች ደግሞ በፈተናው የተሰጣቸው ቦታ በጣም ዝቅተኛ ወይም 3.34% (ሶስት ነጥብ ሶስት አራት በመቶ) ከመሆኑ በተጨማሪ የማዳመጥና የንባብ ክሂልን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ፈፅሞ አልተከተቱም።

4.1.2.5 **የመማሪያ መፅሐፍ እና የፈተናዎቹ ይዘት አጠቃላይ ተዛምዶ**

ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተገለፀው በአንድ ትምህርታዊ መርሀ-ግብር የቀረቡት ፈተናዎች የይዘት ተገቢነታቸው ለመፈተሽ ከምንጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ መማሪያ መፅሐፉና ፈተናዎቹ ያካተታቸውን ይዘቶች አይነትና መጠን ተዘማዶ በመመልከት ነው።

በዚህም መሰረት በተጠቀሰው የጊዜ ክልል ውስጥ ለአስረኛ ክፍል የቀረቡት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ቤት አቀፍ ፈተናዎች ይዘት ለደረጃው ከተዘጋጀው መማሪያ መፅሐፍ ይዘት አንጻር በአይነትና በመጠን ያለው ዝምድና ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

በሁለቱም መካከል ያለው ዝምድና በቁጥርና በመቶኛ ከተመለከተው መረጃ በተጨማሪ የደረጃ ልዩነት ዝምድና አመልካች (Rank difference correlation coefficient) ስሌት በመጠቀም ለመግፅ ተሞክሯል።

ሠንጠረዥ 1.6 የመማሪያ መፅሐፍና የፈተናዎቹ ይዘት ተዛምዶ

ተ.ቁ	በፈተናው የተካተቱ ይዘቶች	በመማሪያ መፅሐፉ ያለው ሽፋን		በፈተናዎቹ የተሰጠው ሽፋን	
		በቁጥር	በመቶኛ	በቁጥር	በመቶኛ
1	የማዳመጥ	08	4%	-	-
2	የንግግር ክሂል	33	16.5%	4	1.03%
3	የንባብ ክሂል	46	23%	34	8.71%
4	የፅሀፈት ክሂል	41	20.5%	34	8.71%
5	የሥነ ልሳን ዕውቀት	28	14.0%	119	30.51%
6	የሥነ ፅሁፍ	33	16.5%	141	36.15%
7	የቃላት ትምህርት	11	2.2%	68	17.43%
	ድምር	200	100%	390	100%

በሠንጠረዡ በሰፈረው መረጃ መሰረት እያንዳንዳቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መፅሐፉና በፈተናዎቹ የተሰጣቸው የሽፋን መጠንና ተዛምዷቸው እንደሚከተለው መግለፅ ይቻላል።

ሀ. የመዳመጥ ክሂል - ይህ ክሂል በመማሪያ መፅሐፉ ካለው አጠቃላይ ይዘት 4% (አራት በመቶ) የሚሆነውን ይዘት የሚሸፍን ሲሆን፣ በፈተናዎቹ ግን 0% (ዜሮ በመቶ) ወይም ምንም አይነት ሽፋን አልተሰጠውም።

ለ. የንግግር ክሂል- በመማሪያ መፅሐፍ 16.5% (አስራ ስድስት ነጥብ አምስት በመቶ) የሚሆነውን ይዘት የሚሸፍን ሲሆን፣ በፈተናዎቹ የተሰጠው ሽፋን ግን 1.03% (አንድ ነጥብ ዜሮ ሶስት በመቶ) ብቻ ነው።

ሐ. የንባብ ክሂል- በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ለክሂሎች ከተሰጠ የሽፋን መጠን ከፍተኛው ወይም 23% (ሀያ ሶስት በመቶ) ሲሆን፣ በፈተናዎቹ ከተካተቱ ይዘቶች

መካከል ደግሞ ከማዳመጥና ንግግር ክሂል ቀጥሎ ዝቅተኛ ሽፋን የተሰጠው ወይም 8.71% (ስምንት ነጥብ ሰባት አንድ በመቶ) የሚሆነውን ይዘት የያዘ ነው።

መ. የፅሕፈት ክሂል- ይህ ክሂል ደግሞ በመማሪያ መፅሐፉ ለይዘቶቹ ከተሰጠው ሽፋን 20.5% (ሀያ ነጥብ በመቶ) በመያዝ በሁለተኛ ደረጃ የሚገኝ ሲሆን፣ በፈተናዎቹ ይዘት ደግሞ ከንባብ ክሂል በተመሳሳይ 8.71% (ስምንት ነጥብ ሰባት አንድ በሞቶ) ይዟል።

ሠ. የሥነ- ልሳን እውቀት በመማሪያ መፅሐፉ ለማዳመጥ ክሂልና ለቃላት ትምህርት ከተሰጠው ሽፋን በመቀጠል ያለውን አነስተኛ ሽፋን ማለትም 14% (አስራ አራት በመቶ) የተሰጠው ሲሆን፣ በፈተናዎቹ ይዘት ደግሞ ከፍተኛ ትኩረት ከተሰጠው የሥነ- ፅሁፍ እውቀት ቀጥሎ 30.51% (ሰላሳ ነጥብ አምስት አንድ በመቶ) የሚሆነውን ሽፋን ይዞ ይገኛል።

ረ. የሥነ- ጽሁፍ እውቀት በመማሪያ መፅሐፍ 16.50% (አስራ ስድስት ነጥብ አምስት በመቶ) የሚሆን ይዘት በመሸፈን ከንባብና ከፅሕፈት ክሂል ቀጥሎ ከንግግር ክሂል ጋር በሶስተኛ ደረጃ ከፍተኛ ሽፋን የተሰጠው ሲሆን፣ በፈተናዎቹ ካሉት ይዘቶች ግን 36.15% (ሰላሳ ስድስት ነጥብ አንድ አምስት) በመያዝ በአንደኛ ደረጃ ተቀምጧል።

ሰ. የቃላት ትምህርት - ይህ ይዘት በመማሪ መፅሐፍ 5.5% (አምስት ነጥብ አምስት በመቶ) በመያዝ ከማዳመጥ ክሂል ቀጥሎ በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝ ነው። ነገር ግን በፈተናዎቹ ይዘት ከሥነ- ፅሑፍና ስነ- ልሳን በመቀጠል በ 17.43% (አስራ ሰባት ነጥብ አራት ሶስት በመቶ) በመያዝ በሶስተኛ ደረጃ ይገኛል።

በአጠቃላይ በመማሪያ መፅሐፍ ያለው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች መጠን ወይም ሽፋን በፈተናዎቹ ካለው የይዘቶች መጠን ተመጣጣኝ ነው ለማለት አይቻለም። ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው በመማሪያ መፅሐፉ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ይዘት በፈተናዎቹ ላይ ተመሳሳይ እድል አልተሰጠውም። በአንጻሩ ደግሞ በመማሪያ መፅሐፉ ዝቅተኛ ሽፋን የተሰጠው በፈተናዎቹ ይዘት በኩል ከፍተኛ ሽፋን ሲሰጠው ይስተዋላል። ከዚህ በመነሳት የፈተናዎቹ ይዘት በመማሪያ መፅሐፉ ካለው የይዘቶች ሽፋን መጠን የተዛመደ እንዳለሆነ መረዳት ይቻላል።

በመማሪያ መፅሃፉና በፈተናው በኩል ለእያንዳንዳቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች የተሰጣቸው አህዛዊ መረጃ ስንመለከት ከፍተኛ የሆነ ልዩነት እንመለከታለን። ለምሳሌ

አራቱ ክሂሎች ከሥነ- ልሳንና የስነ- ፅሑፍ የእውቀት ዘርፎች በመማሪያ መፅሃፍና በፈተናው ያላቸው ልዩነት እንመልከት፡፡

አራቱ ክሂሎች 64.5% (ስድሳ አራት ነጥብ አምስት በመቶ)የሚሆን የመማሪያ መፅሃፉ ሽፋን የነበራቸው ሲሆን የስነ- ልሳንና የስነ- ፅሁፍ እውቀቶች ደግሞ 30.5% (ሰላሳ ነጥብ አምስት በመቶ) የሸፈኑ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል አራቱ ክሂሎች በፈተናው የተሰጣቸው ሽፋን 18.42% (አስራ ስምንት ነጥብ አርባ ሁለት በመቶ) ሲሆን ለሁለቱም የፅውቀት ዘርፎች ደግሞ 66.66% (ስልሳ ስድስት ነጥብ ስልሳ ስድስት) ነው፡፡ በአራቱ ክሂሎችና በሁለቱም የእውቀት ዘርፎች መካከል በመማሪያ መፅሐፉ ያለው ልዩነት 34.0% (ሰላሳ አራት በመቶ) ሲሆን በፈተናው ደግሞ 48.24% (የአርባ ስምንት ነጥብ ሁለት አራት በመቶ) ልዩነት ይታያል፡፡ ይህም ክሂሎቹም ሆኑ የእውቀት ዘርፎቹ በመማሪያ መፅሐፉ የተሰጣቸው ሽፋንና በፈተናው ላይ የተሰጣቸው ትኩረት ተመጣጣኝ እንዳልሆነ ያመለክታል፡፡

ከዚህ በመቀጠል በመማሪያ መፅሐፉ እና በፈተናዎቹ ይዘቶች መካከል ያለውን ተዛምዶና የደረጃ ልዩነት ዝምድና አመልካች ስሌትን በመጠቀም እንመለከታለን፡፡ ይህን ለማድረግ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶቹ በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ካላቸው ሽፋን እና በፈተናዎቹ ውስጥ ከተሰጣቸው ሽፋን አንጻር የሚይዙት ደረጃ ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ በቅድምያ ይዘቶቹን በደረጃ የሚያስቀምጥ ሰንጠረዥ እንመልከት፡፡

ሠንጠረዥ 1.7 የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መፅሐፉና በፈተናዎቹ ከተሰጣቸው ሽፋን አንጻር ያላቸው ደረጃ

የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች	የማዳመጥ ክሂል	የንግግር ክሂል	የንባብ ክሂል	የፅሕፈት ክሂል	የሥነ-ልሳን እውቀት	የሥነ ፅሁፍ እውቀት	የቃላት ትምህርት
በመማሪያ መፅሐፍ ካላቸው ሽፋን አንጻር ያለው ደረጃ	7	3	1	2	5	3	6
በፈተናዎቹ ከተሰጣቸው ሽፋን አንጻር ያለው ደረጃ	7	6	3	3	2	1	5
D	0	-3	-2	-1	3	2	1
D	0	9	4	1	9	4	1
$\sum D^2$							28

የደረጃ ልዩነት ዝምድና አመልካች ቀመር መጠቀም በሁለቱም መካከል ያለውን ዝምድና እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

$$P = 1 - \frac{6x\sum D^2}{N(N^2-1)}$$

$$= 1 - \frac{6x28}{7(7^2-1)}$$

$$= 1 - \frac{168}{336}$$

$$= 1 - 05$$

$$= 0.5$$

በስሌቱ መሰረት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶቹ በመማሪያ መፅሐፉ እና በፈተናዎቹ ከተሰጣቸው ሽፋን አንጻር በተሰጣቸው ደረጃ መካከል ያለው የተዛምዶ ደረጃ 0.5 (ዜሮ ነጥብ አምስት) ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ቀደም ሲል በምዕራፍ ሦስት እንደተገለፀው የስሌቱ ውጤት 1.00 ከሆነ ፍፁም አወንታዊ (ቀጥተኛ) ግንኙነት አለ፣ 0.00 ከሆነ ደግሞ ምንም አይነት ግኑኝነት የለም እንዲሁም -1.00 ከሆነ ፍፁም አሉታዊ (አ-ቀጥተኛ) ግኑኝነት የሚያመለክት እንደሆነ ተገልጿል፡፡

በዚህ መሰረት የተገኘው ውጤት በመማሪያ መፅሐፉና በፈተናዎቹ ያሉት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ፍፁም የተገናኙ ወይም የተራራቁ ሳይሆኑ በመካከለኛ የተዛምዶ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው።

ስለዚህ ከተመረጡ ሦስት ትምህርትቤቶች የተሰበሰቡ የ2002 እና 2003 ዓ/ም የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ይዘቶች ለደረጃው ከቀረበው መማሪያ መፅሐፍ ይዘቶች ጋር ያላቸው የይዘት ተገቢነት ደረጃ መካከለኛ (moderate) የሚባለውን ደረጃ የሚይዙ ናቸው።

ይህ አሀዛዊ መግለጫ መካከለኛ የተዛምዶ ደረጃ የሚያመለክት ይሁን እንጂ ከቀጥተኛው ወይም ትክክለኛ ተዛምዶ ከሚያመለክተው መጠን በታች መሆኑን ግን መረዳት ያስፈልጋል። ምክንያቱም የስሌቱ ውጤት ቀጥተኛ ተዛምዶ ከሚያመለክተው መጠን እየራቀ በሄደ ቁጥር የይዘት ተገቢነት ደረጃውም በዚያው ልክ እየቀነሰ የሚሄድ በመሆኑ ነው።

4.2 ከቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተናና ውጤት

ቀደም ሲል እንደተጠቆመው ቃለ መጠይቅ የቀረበበት ዋና አላማ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችን የሚያዘጋጁ መምህራን በፈተና ዝግጅት ወቅት የሚከተሉት አካሄድ ለማወቅና የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥን የመጠቀም ልምዳቸውን ምን ያህል እንደሆነ ለመፈተሽ ነው።

በዚህም መሰረት እነዚህ ጉዳዮች የተመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበው ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል። በመቀጠል የመረጃ ሰጪዎቹ አጠቃላይ መረጃና የጥያቄዎች ምላሽ ከዚህ በታች ቀርቧል።

4.2.1 የመረጃ ሰጪዎች አጠቃላይ መረጃ

በጥናቱ በመረጃ ሰጪነት የተሳተፉት መምህራን በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች አስረኛ ክፍልን ከሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በፈተና ዝግጅት ላይ ተሳትፎ የነበራቸው ናቸው። በዚህ መሰረት ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ሁለት ሁለት መምህራን በናሙናነት በመውሰድ በአጠቃላይ ስድስት መምህራን በቃለ መጠይቁ ተሳታፊ ሁነዋል። የተሳታፊዎቹ አጠቃላይ መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 1.8 የመረጃ ሰጪዎች አጠቃላይ መረጃ

መረጃ ሰጪዎች	የሚያስተምሩበት የትምህርት ቤት	የሚያስተምሩት የክፍል ደረጃ	የሰለጠኑበት ትምህርት አብይና ንኡስ	በማስተማር ላይ የቆዩበት ዓመት	የትምህርት ደረጃ
መረጃ ሰጪ -1	ሽሬ ሁ/ደ/ት/ቤት	9ኛ እና 10ኛ	አማርኛ-እንግሊዝኛ	4	ዲግሪ
መረጃ ሰጪ -2	ሽሬ ሁ/ደ/ት/ቤት	10ኛ	አማርኛ-እንግሊዝኛ	10	ዲግሪ
መረጃ ሰጪ -3	እ/ጉ/ና ሁ/ደ/ት/ቤት	9ኛ እና 10ኛ	አማርኛ -ትግርኛ	8	ዲግሪ
መረጃ ሰጪ -4	እ/ጉ/ና ሁ/ደ/ት/ቤት	9ኛ እና 10ኛ	አማርኛ-እንግሊዝኛ	3	ዲግሪ
መረጃ ሰጪ -5	ዓ/ዳ/ ሁ/ደ/ት/ቤት	9ኛ እና 10ኛ	አማርኛ-ትግርኛ	4	ዲግሪ
መረጃ ሰጪ -6	ዓ/ዳ/ ሁ/ደ/ት/ቤት	9ኛ እና 10ኛ	አማርኛ-ትግርኛ	4	ዲግሪ

ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው አብዛኞቹ መምህራን ዘጠነኛና አስረኛ ክፍል የሚያስተምሩ አማርኛን በአብይነት እንግሊዝኛን ደግሞ በንኡስነት የሰለጠኑ እንዲሁም በመለስተኛ የስራ ልምድ ደረጃ ላይ የሚገኙና የትምህርት ደረጃቸውም ዲግሪ የያዙ ናቸው። ይህም በሚሰጡት መረጃ ላይ ሊፈጠር በሚችለው ልዩነት የሚኖረው አስተዋጽኦ የጎላ ነው ተብሎ ይታሰባል።

4.2.2 የቃለ- መጠይቅ ምላሽና ማብራሪያ

ቃለ መጠይቁ ስድስት ቁልፍ ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን፣ መረጃ ሰጪዎቹ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሰጡትን ምላሽ ጠቅለል ባለ መልኩ እንደሚከተለው በገለጻ ስልት ቀርቧል።

በመጀመሪያ ደረጃ ለመምህራኑ የቀረበው ጥያቄ ‹‹በትምህርት ቤት ደረጃ በሚዘጋጁ የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መደበኛ ፈተናዎቹ ዝግጅት ላይ ይሳተፋሉ?›› የሚል ጥያቄ ሲሆን ሁሉም ‹‹አዎ፤ እንሳተፋለን›› የሚል ነው።

ከዚህ በኋላ የቀረበው ጥያቄ ‹‹የአስረኛ ክፍል ትምህርት ቤት አቀፍ የአማርኛ ፈተናዎቹ በዚሁ ትምህርት ቤት እንዴት እንደሚዘጋጁ ቢገልፁልኝ?›› የሚል ጥያቄ ሲሆን መምህራኖቹ (መረጃ ሰጪዎቹ) የሰጡት መልስ በሁለት አበይት ነጥቦች የሚጠቃለል ነው። የመጀመሪያው ምላሽ የትምህርት ክፍሉ አባላት እያንዳንዳቸው የሚፈለገውን ያህል ጥያቄዎች በተለያዩ መመሪያዎች ከፋፍለው ይዘው እንዲመጡ ይደረጋል። ከዚህ

በኋላ ለተማሪዎቹ ይመጥናል ተማሪዎች ተምረውታል ወይስ አልተማሩትም በሚል መስፈርት ከእያንዳንዱ መምህር የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲቀርና በሌላ እንዲተካ ወይም እንዲካተት ይደረጋል። በዚህ መልኩ የፈተና ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ለተማሪዎች ይቀርባሉ የሚል ነው። ሁለተኛው ደግሞ በዲፓርትመንቱ ካሉት አባላት መካከል አንድ ፍቃደኛ የሆነ ወይም በተራ ተደልድሎ ፈተና ይዘጋጅ በሚባልበት ወቅት ፈተና እንዲያዘጋጅ ይደረጋል፣ ይህ አይነቱ አካሄድ አብዛኛው ጊዜ ለሰሚስተር አጋማሽ ፈተናዎች ሲሆን ለማጠቃለያ ወይም ሞዴል ፈተና ዝግጅት ግን ሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑትን የዲፓርትመንቱ አባላት እንዲያዘጋጁ በዲፓርትመንት በሚደረገው ስብሰባ ስምምነት ላይ ይደረሳል፣ በዚህ መልክም ፈተና ተዘጋጅቶ ይቀርባል የሚል ነው።

በሶስተኛ ደረጃ የቀረበው ጥያቄ ‹‹በፈተናዎቹ ዝግጅት ተሳታፊ እንደመሆንዎ መጠን የፈተናዎቹ ጥያቄዎች ስትመርጡ በምንጭነት የምጥቀሙት ምንድን ነው ማለቱ የፈተና ጥያቄዎች የሚወጡት ወይም የሚመረጡት ከየት ነው?›› የሚል ነው። መረጃ ሰጪዎቹ እንደገለፁት አብዛኛውን ጊዜ መምህራን በግላቸው ወይም ከትምህርት ክፍሉ ጋር በመነጋገር ለየክፍል ደረጃው ምን ምን ይዘቶች ለምን ያህል ጊዜ ማስተማር እንዳለባቸው ለይተው ያስቀምጣሉ። በዚህ መሰረት ለአስረኛ ክፍል የሚሆኑ ይዘቶች በቅደምተከተል በማስቀመጥ የራሳቸው ማስታወሻ በማዘጋጀት ያስተምራሉ። የሚዘጋጀው ማስታወሻም በስነ- ልሳንና ስነ- ጽሁፍ ይዘቶች ላይ የሚያተኩር ሲሆን፤ የፈተና ጊዜ ሲደርስ ከዚሁ ማስታወሻ ተማሪዎች እስከ ተማሩበት ርዕሰ ጉዳይ የሚያጠቃልል የፈተና ጥያቄ በመምረጥ ዝግጅት ይደረጋል። ሌሎች መረጃ ሰጪዎች ደግሞ በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ከሚገኙ ማስታወሻዎች፣ መልመጃዎችና ሙዳየ ቃላት በቀጥታ ጥያቄዎችን እንደሚመርጡ ገልጸዋል። በአጠቃላይ ከመረጃ ሰጪዎቹ መረዳት እንደሚቻለው የፈተና ጥያቄዎች የሚመረጡት መምህራን በግልም ሆነ በትምህርት ክፍል ደረጃ ይዘቶችን ለይተው ካስቀመጡበት የማስታወሻ ደብተር እንዲሁም በመማሪያ መፅሐፉ ከሚገኙ መልመጃዎች፣ ማስታወሻዎችና ሙዳየ ቃላት ነው።

በመቀጠል ‹‹በፈተና ዝግጅቱ ላይ እርስዎም ተሳታፊነዎትና፣ የፈተና ጥያቄዎቹን ሲመርጡ በብዛት ትኩረት የሚያደርጉበት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘት የትኛውን ነው?›› የሚል ጥያቄ የቀረበ ሲሆን በአብዛኞቹ መልስ ሰጪዎች ዘንድ ልዩነት የፈጠረ ነበር። አንዳንድቹ በስነ- ልሳንና በስነ- ፅሑፍ ላይ ትልቅ ትኩረት እንደሚሰጡ በመግለፅ ምክንያታቸውም አብዛኛውን ግዜ በሀገር አቀፍ ፈተና ላይ የሚታዩ ጥያቄዎች በነዚህ ይዘቶች ላይ በብዛት ትኩረት ስለሚያደርግና ጥያቄ ለማዘጋጀትም እነዚህ ይዘቶች የሚመቹ በመሆናቸው ነው በማለት ያሰረዳሉ። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ መልስ ሰጪዎች ፈተና ከሁሉም የትምህርት ይዘቶች የተውጣጡ ጥያቄዎች አሰባስቦ የያዘ መሆን እንዳለበት ግልፅ ነው። ነገር ግን አንዳንድ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በተመለከተ ጥያቄ ለማዘጋጀት ብዙም የተመቹ አይደሉም። ለምሳሌ የማዳመጥ ክሂል በተመለከተ በለሚስተር አጋማሽ ፈተና ወይም በማጠቃለያ ፈተና ውስጥ ከማካተቱ ይልቅ በቋንቋ ላባራቶሪ ውስጥ ለብቻው ቢካሄድ ይሻላል። ይሁን እንጂ ይህን ለማድረግም የትምህርት ቤቱ አቅም የሚፈቅድ አይደለም። በዚህና መሰል ችግሮች ምክንያት በተወሰኑት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ላይ ትኩረት ለሚደረግ ግድ ይላል በማለት ይገልጻሉ።

ከመረጃ ሰጪዎቹ መረዳት እንደተቻለው በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ወቅት ሁሉም የቋንቋው ትምህርት ይዘቶች በተመጣጣኝ ውክልና ለማካተት አዳጋች መሆኑና ከይዘቶቹ መካከል ለፈተና ተብሎ በአመቺነት የሚመረጥ ይዘት መኖሩን ነው። በሰነድ ምርምራ ላይ በፈተናዎቹ የታየው የይዘቶች አሃዛዊ መረጃም ከዚህ ሀሳብ ጋር የሚጣጣም ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም በፈተናዎቹ ትንተና እንድተገለጸው የፈተናዎቹ ትኩረት ከክሂሎች ይልቅ በስነ- ልሳንና በስነ- ጽሑፍ ላይ መሆኑ ለዚህ ሀሳብ መጠናከር በማስረጃነት የሚቀርብ ነው።

በአምስተኛ ደረጃ የቀረበው ጥያቄ ‹‹በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ዝግጅት ወቅት የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ (Table of specification) ስለ መጠቀም ያለዎት ልምድ ምን ይመስላል›› የሚል ነው። ለዚህ ጥያቄ የተሰጠ ምላሽ እንደሚያመለክተው በአብዛኛዎቹ መረጃ ሰጪዎች ስለ ጉዳዩ የሚያውቁት ነገር አለመኖሩ ጭምር የሚያመለክት ነው። አብዛኞቹ መላሾች እንደገለፁት በፈተና ዝግጅት ወቅት የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ መጠቀም በሌሎች መምህራንም ቢሆን መኖሩን

ይጠራጠራሉ። የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ የቋንቋ ትምህርት አላማዎችና ይዘቶች በመማሪያ መፅሐፍ ላይ ካላቸው መጠን አንጻር በመመልከት የፈተና ይዘቶች መጠንና ስፋት የሚወሰንበት ስልት መሆኑ ይታወቃል። ይሁን እንጂ መረጃ ሰጪዎቹ እንደሚገልፁት የፈተና ጥያቄዎች የሚመረጡት እያንዳንዱ መምህር በጥያቄው በተገለፀው ርዕስ ጉዳይ ማስተማር አለማስተማሩንና የተማሪዎችን የመመለስ ብቃት በማገናዘብ ብቻ መሆኑን ነው። ከመረጃ ሰጪዎቹ መካከል አንዱ ግን ጉዳዩ እንደሚያውቀውና ነገር ግን ካለው የሥራ ጫና እና በብዙዎቹ መምህራን ዘንድ የማይታወቅ በመሆኑ የተነሳ ለመተግበር እንዳልቻለ ይገልፃል። በአጠቃላይ ግን የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ ስልት የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችን ለማዘጋጀት በተግባር ላይ እየዋለ እንዳልሆነ ከመረጃ ሰጪዎቹ መረዳት ይቻላል።

በመጨረሻ ለመረጃ ሰጪዎቹ የቀረበ ጥያቄ ‹‹በአጠቃላይ የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ወይም የፈተናዎቹ ይዘቶች ከመማሪያ መፅሐፍ ይዘቶች አንጻር ያላቸውን ተመጣጣኝ ውክልና በተመለከተ ምን የሚነግሩኝ ነገር አለ›› የሚል ሲሆን መረጃ ሰጪዎቹም የተለያየ መልስ ሰጥተዋል። ከመልስ ሰጪዎቹ መካከል አንዱ እንደገለፁት በትምህርት ቤታቸው የሚዘጋጁ የአስረኛ ክፍል ፈተናዎች በአጠቃላይ በተለይ ደግሞ ሞዴል ፈተናዎች ለሀገር አቀፍ ፈተናው ዝግጅት ይረዳል በሚል ሰበብ በብዛት ትኩረት የሚያደርጉት ከመፅሐፍ ውጭ ባሉት ይዘቶች ላይ ነው። ሌላኛው መልስ ሰጪ እንደሚሉት ደግሞ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች በብዛት ትኩረት የሚያደርጉት በተለያዩ ሥነ ልሳናዊ ይዘቶች፣ ምሳሌያዊና ፈሊጣዊን ንግግሮች በመሳሰሉ ስነ ፅሑፋዊ ይዘቶች እንዲሁም በቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺዎች ላይ በመሆኑ በመማሪያ መፅሐፍ ያሉት ሁሉም የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በፈተናዎች ላይ ተመጣጣኝ የሆነ ውክልና ይኖራቸዋል ብሎ ለመናገር አስቸጋሪ ነው። ሌሎች መልስ ሰጪዎችም በትምህርት ቤቶቻቸው የሚዘጋጁት የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች በመማሪያ መፅሀፉ ካሉት ይዘቶች አንጻር ሲታዩ ተመጣጣኝ የሆነ ውክልና ይኖራቸዋል ብለው ለመናገር እንደሚከብዳቸውና ይህን ለማድረግም አስቸጋሪ እንደሆነ ገልፀዋል (ለዝርዝሩ አባሪ አራትን ይመልከቱ)።

በአጠቃላይ በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች አስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተና የሚያዘጋጁ መምህራን በቃለ መጠይቁ ከሰጡት ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ፈተናዎቹ ከትምህርት ክፍሉ አባላት መካከል አንድ ወይም ከዛ በላይ በሆኑ ፈቃደኛ ወይም ተረኛ መምህራን የሚዘጋጅ ሲሆን በትምህርት ክፍሉ አባላት ሁሉ ከተደረሰባቸው ምዕራፎች የተውጣጡ ጥያቄዎች መሆናቸውን እየታዩ የፈተናው ይዘት እንዲሆኑ በመወሰን ነው። በፈተናው የስነ- ልሳንና ስነ ፅሑፍ ይዘቶች እንዲሁም ቃላት ትልቅ ትኩረት እንደሚሰጣቸውና የይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ በመጠቀም የፈተና ይዘቶች በመማሪያ መፅሐፉ ካላቸው ሽፋን አንጻር ተመጣጣኝ ውክልና እንዲኖራቸው የማደረግ ጥረትም እንደሌለ ከተሰጠው ምላሽ መረዳት ተችሏል።

አጥኚው በሰነድ ምርመራው ባገኘው መረጃ ላይ ያደረገው ትንተና እንደተመለከተው የፈተና አዘጋጅ መምህራን በቃለ መጠይቁ ከሰጡት ሀሳብ ጋር የሚስማማ ሆኖ አግኝቶታል። በሰንጠረዥ 1.3፣1.4፣1.5 እና 1.6 ላይ የሰፈረው መረጃ እንደሚያመለክተው ፈተናዎቹ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥባቸው የትምህርት ይዘቶች የስነ- ልሳንና የስነ- ፅሑፍ እውቀቶች እንዲሁም የቃላት ትምህርት ናቸው። በሰንጠረገዦቹ እንደተመለከተው ለቋንቋ ክሂሎች የተሰጠው ሽፋን በመማሪያ መፅሐፉ የተሰጠው ያህል አይደለም ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ይዘቶች ከተሰጠው ሽፋን በጣም ያነሰ ነው። በተለይ ደግሞ ለማዳመጥና ንግግር ክሂሎች ፍፁም ትኩረት የማይሰጡ ፈተናዎች እንዳሉ ለመመልከት ተችሏል። የፈተና አዘጋጅ መምህራን የሰጡት ምላሽም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው።

ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያና አስተያየት

5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በዋናነት ይዞት የተነሳው አላማ በትግራይ ክልል ሰሜናዊ ምዕራብ ዞን በሚገኙ ሶስት የተመረጡ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚዘጋጁ የአስረኛ ክፍል ትምህርት ቤት አቀፍ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ደረጃቸውን መገምገም ሲሆን የፈተናዎቹ አዘጋጅ መምህራን ፈተናዎቹን ለማዘጋጀት የሚከተሉት ስልት ማወቅና የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ (Table of Specification) የመጠቀም ልምዳቸውን ምን ይመስላል? የሚሉት ንኡሳን አላማዎችንም ያካተተ ነው።

አጥኚው እነዚህ አላማዎችን ከግብ ለማድረስ የሚያስችል መረጃ ለማግኘት የሰነድ ምርመራንና የቃል መጠይቅ በማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሞክሯል። መረጃዎችን በመሰብሰብ ሂደት ቀላል የእጣ ናሙና እና ስብጥር የድርሻ ናሙናን በጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆኑ፣ በናሙናነት በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች ለአስረኛ ክፍል የቀረቡና በ 2003ዓ.ም የተዘጋጀው የሰሚስተር አጋማሽ ፈተናን ጨምሮ በ 2002 ዓ.ም የተዘጋጁት የሰሚስቴር አጋማሽ፣ የሰሚስተር ማጠቃለያ እና ሞዴል የአማርኛ ፈተናዎች እንዲሁም ከፈተና አዘጋጅ መምህራን ጋር የተደረገ ቃል መጠይቅ በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል።

ከመረጃ ምንጮቹ የተሰበሰበው መረጃ በቁጥርና በመቶኛ፣ የደረጃ ልዩነት ዝምድና አመልካች ስሌት እና የገለጻ ስልት በመጠቀም ትንተና ለመስጠትና ውጤቱን ለማስቀመጥ ተሞክሯል። በዚህ መሠረት ጥናቱ በአጠቃላይ ያገኘውን ውጤት እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል።

- በትግራይ ክልል ሰሜናዊ ምዕራብ ዞን በሚገኙ ሶስት የተመረጡ ትምህርት ቤቶች የሚዘጋጁ የአስረኛ ክፍል ትምህርት ቤት አቀፍ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ደረጃቸው መካከለኛ (Moderate) በሚባለው ደረጃ ላይየሚገኙ ናቸው።

- በፈተናዎቹ ውስጥ የተካተቱ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በመጠንና በአይነት በመማሪያ መጽሐፉ ከተሰጣቸው ሽፋን አንጻር ሲታዩ ተመጣጣኝ የሆነው ውክልና አላቸው ለማለት አያስደፍርም።
- የመማሪያ መፅሐፉ ለክሊሎች ትልቅ ትኩረት በመስጠት ለሌሎች የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችም በአመዛኙ ተመጣጣኝ ትኩረት ይሰጣል። ፈተናዎቹ ግን ለሁለቱም የዕውቀት ዘርፎች (ሥነ- ልሳንና ሥነ- ፅሑፍ) ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ለክሊሎች ደግሞ ዝቅተኛ ትኩረት ከመስጠት ባሻገር ጨርሶ ያለማካተት ሁኔታ ይታይባቸዋል። በጥናቱ የማዳመጥ ክሂል በፈተናዎቹ ፍፁም የተዘነጋ ክሂል መሆኑ ለመረዳት ተችሏል።
- በትምህርት ቤቶቹ የሚዘጋጁ የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች በዲፓርትመንቱ ከሚገኙ መምህራን መካከል አንድ ወይም ሁለት ሰው በፍቃደኝነት አልያም በተዘጋጀላቸው ተራ መሰረት ተዘጋጅተው በቀጥታ ለፈተና የሚቀርቡ ናቸው። በመሆኑም እያንዳንዳቸው የፈተና ጥያቄዎች አብዛኛውን የትምህርት ክፍሉ አባል በማስተማር ቆይታው የዳሰሰው ርዕሰ ጉዳይ የያዙ መሆናቸውን ከመነጋገር ባለፈ ከየትኛው የቋንቋ ትምህርት ምን ያህል ጥያቄዎች በፈተናው ጥያቄነት ተካተተ? ወይም የትኛውን የትምህርት ይዘት ተካተተ? የትኛውስ አልተካተተም? የሚል ጉዳይ የፈተና ጥያቄዎች በመምረጥና በማደራጀት ሂደት ብዙ ትኩረት አይሰጠውም።
- መምህራን ከመማሪያ መፅሐፍ ውጭ ምን ምን መስተማር እንደለባቸው ከትምህርት ክፍሉ ጋር በመስማማት በጋራ አልያም በግል ደረጃ ይዘቶችን በመለየት ያስተምራሉ። እነዚህ ይዘቶች ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ በሀገር አቀፍ ፈተና ላይ ሊከሰቱ ይችላሉ ተብሎ በተሰቡት በስነ- ሐረግ፣ የቃል ክፍል፣ ዓረፍተ ነገር፣ የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ፣ ፊሊጣዊና ምሳሌያዊ ንግግር፣ ዘይቤ፣ ቅኔ፣ ስነ- ግጥምና ልብወለድ ላይ ያተኩሩ ናቸው። የፈተና ጥያቄዎች ደግሞ ከነዚህ ይዘቶች ተመርጠው ይቀርቡና አብዛኛው መምህራን ያልደረሰበት ርዕሰ ጉዳይ የሚዳስስ ጥያቄ ካለ ብቻ እንዲቀየር በማድረግ ዝግጁ ይሆናሉ።
- በመሆኑም በተጠቀሰው ቦታ ባሉት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በፈተና ዝግጅት ላይ ተመጣጣኝ የሆነ ትኩረት በመስጠት

በፈተናው ይዘት እንዲካተቱ የሚያደርጉት ጥረት በጣም ዝቅተኛ ነው። ከዚህ የተነሳ የፈተናዎቹ ይዘቶች በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ካላቸው ሽፋን አንጻር ሲታይ ተመጣጣኝ የሆነ ውክልና ያላቸው ናቸው ማለት እንደማይቻል መምህራኖቹ አምነውበታል።

5.2 አስተያየት

አጥኚው በጥናቱ ያገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ ለመምህራንና ሌሎች የትምህርት ባለ ድርሻ አካላት የሚከተለውን አስተያየት ይሰጣል።

- መማር ማለት መለወጥ ማለት ነው። ይህ ለውጥ ደግሞ በትምህርትነት የቀረቡ ይዘቶች ሁሉ ድምር ውጤት ነው። በመሆኑም ለትምህርትነት የቀረቡ ይዘቶች በተማሪዎች ላይ ያስከተሉትን ለውጥ ለመገምገም ሁሉም በትምህርትነት የቀረቡ ይዘቶች ተመጣጣኝነት ባለው ውክልና በፈተና ላይ መታየት አለባቸው። ስለዚህ መምህራን ይህን በመረዳት በትምህርትነት የቀረቡት እያንዳንዳቸው ይዘቶች ባስተማሯቸው ተማሪዎች ላይ ያስከተሉትን ለውጥ ለማወቅ በሚያስችል መልኩ የፈተናዎቻቸውን ይዘቶች ቢመርጡ ውጤታማ ያደርጋል።
- የአስረኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተመሰረተባቸው አበይት አላማዎች ማለትም የማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ ክሂሎች እንዲሁም የስነ- ልሳንና የሥነ- ጽሁፍ ዕውቀት ለማዳበር የሚያስችሉ ይዘቶች በአንጻራዊ መልኩ አመጣጥኖ ለማካተት ሞክሯል። የፈተና ዋና አላማው ደግሞ እነዚህ አላማዎችን ለማሳካት ተብሎ በትምህርትነት የቀረቡት የትምህርት ይዘቶች አላማዎቹን ከማሳካት አንጻር ምን ያህል ውጤታማ እንደነበሩ መረጃ ለመስጠት ነው። መረጃው ትክክልኛ፣ ተአማኒና ተገቢ እንዲሆን ደግሞ ከአንዱ ወይም ከተወሰኑ የትምህርቱ ይዘቶች ብቻ የሚሰበሰብ መሆን የለበትም። ስለዚህ የፈተና አዘጋጅ መምህራን ስላስተማሩት ትምህርት ውጤታማነት ትክክለኛ፣ ተአማኒና ተገቢ መረጃ መስጠት የሚችል ፈተና ለማዘጋጀት በሁሉም ለትምህርትነት የቀረቡ ይዘቶች ላይ ትኩረት ቢያደርጉ ተመራጭ ይሆናል።

- ለአንድ ደረጃ የሚዘጋጀው የመማሪያ መጽሐፍ ለደረጃው በደረሱ ተማሪዎች ላይ ሊታይ የተፈለጉትን ባህሪያት እንዲያሳዩ እና ተማሪዎቹ ማወቅ ወይም መማር ይገባቸዋል ተብሎ የታመነባቸው የትምህርት ይዘቶች አካትቶ የያዘ ነው። ለደረጃው የደረሱ ተማሪዎች ችሎታና እውቀታቸውን በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱትን የትምህርት ይዘቶች ከሚያስገኙት ድምር ውጤት አንጻር የሚለካ ነው። በመሆኑም ለዚህ ደረጃ የደረሱ ተማሪዎች እውቀትና ችሎታ ለመለካት የሚፈልግ ማናቸውም የምዘና መሳሪያ ለትምህርትነት የቀረቡትን ይዘቶች በመጠንና በአይነት ወሳይ በሆነ ናሙና ማካተት ይኖርበታል። ስለዚህ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና አዘጋጅ መምህራንም ይህን ግምት ውስጥ ያስገባ የፈተና ጥያቄዎች ይዘት የመምረጥ ሂደት በመከተል ቢያዘጋጁ የተገቢነት ደረጃውን ከፍ ያለ ፈተና ለማዘጋጀት ይረዳቸዋል።
- የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ የፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ደረጃን ለመጠበቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ በሁሉም የአማርኛ ቋንቋ ፈተና አዘጋጅ መምህራን ዘንድ ቢለመድ ጠቃሚነቱ የጎላ ነው።
- የትምህርት ባለድርሻ አካላት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በፈተና አዘገጃጀት ወይም የይዘት ተገቢነት ደረጃን በመጠበቅ ረገድ የሚታይባቸውን ክፍተት ለመቅረፍ የሚያስችሉ የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ተሞክሮዎቻቸውን እንዲለዋወጡና ሙያዊ ብቃታቸውን ከፍ የሚያደርጉበት ሁኔታ ቢያመቻቹ መልካም ነው።
- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እና ተማሪዎች በሀገር አቀፉ ፈተና ላይ ይገጥሟቸዋል ተብለው የሚጠበቁትን ይዘቶች መካከል ያለውን ልዩነት እንዲጠብ በማድረግ የመማሪያ መፅሐፉ ይዘት እና የሚቀርበው ትምህርት እንዲሁም የሚሰጠው ፈተና አብሮ እንዲሄድ በሚያስችል መንገድ ቢቀርብ።

ዋቢ መፃሕፍት

ሰለሞን ደስታ (1976)። "በአዲስ አበባ ከተማ በአራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ1975 ዓ.ም የተሰጡ የአማርኛ ፈተናዎች ግምገማ።" ለቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)።

በለጠ ያዕቆብ (1995)። "ለዘጠነኛ ክፍል የሚዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች ለደረጃው ከሚቀርበው ትምህርት ጋር ያላቸው የይዘት አግባብነት እና ያጠያየቅ ብቃት ትንተና" ለኤም. ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)።

ተስፋዬ ሸዋዬ (1981)። "ሥነ ልሳን እና ቋንቋን ማስተማር።" አዲስ አበባ የኒቨርስቲ (ያልታተመ)።

ትምህርት ሚኒስተር (1997)። *የአስረኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ*። አዲስ አበባ። ሜጋ አሳታሚዎች ደርጅት።

ጠጅቱ በረቻ (1999)። "በአዲስ አበባ ከተማረ በግልና በመንግስት 2ተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ አገር አቀፍ ፈተና ውጤቶች ንፅፅር።" ለኤም. ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)።

ዮሃሁን ንጉሴ (1989)። "ሐረር ከተማ በሚገኙ ሁለት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ 1987 እና በ 1988 ዓ.ም የተሰጡ የአማረኛ ፈተና ጥያቄዎች ይዘትና አቀራረብ ግምገማ።" የቢኤ. ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩነቨርስቲ (ያልታተመ)።

Alderson, J. C. 1988. *Testing English for Specific Purposes How Specific Can we Get.* in A Hugher (ed.), PP. 16-28.

Alderson, J. C., Clapham, C. and Wall, D. (1995). *Language Test construction and Evaluation.* Cambridge: Cambridge University press.

Atkins, J., Hailom Bante Yerga and Nuru Mohammed (1996). *Skill Development Methodology part-2.* Addis Ababa University, Department of Foreign Language and Literature.

Bachman, L. (1990). *Fundamental Consideration in Language Testing.* Oxford: Oxford University press.

Baker, D. (1989). *Language Testing*: A critical survey and Practical Guide London: Edward Arnold.

Brown, J.D. (1996). *Testing in language Programs*, New Jersy: Prentice Hall Regents.

_____(1994).*Principles of Language Learning and Teaching*. New Jersy Prentice Hall Regents.

Carroll, B. J. (1980). *Testing Communicative Performance: An Interim Study*. Oxford: Pergamon press ltd.

Clark, L and Star, I (1996). *Secondary and Middle School Teaching Methods*. Upper Saddle: prentice Hall Inc.

Cohen, A (1991). *Second Language Testing*: In Murcia Teaching English as a Second or Foreign Language: Second Edition. Boston: Heinle and Heinle Publishers.

Cronbach, L.J.(1970*): Essential & psychological testing.* Harper international Edition, New York.

Cunning worth, A. (1995). *Choosing your course Book*, London, The Bath Press.

Davis, A. (1988). *Communicative Language Testing*. In A. Hughes (ed.) PP 5-14. Oxford. Oxford University press.

Desalegn and Girma (2009) *Measurement and evaluation manual for Higher Education Institutions;* The National pedagogical Resource Center, Addis Ababa university. Addis Ababa .

Dubin, F and E. Olshtain (1986). *Course Design: developing Programs and Material for Language Learning.* Cambridge University Press.

Finocchiaro, M and brumfit, C. (1983). *The Functional National Approach: From Theory to Practice*. Oxford. Oxford University press.

Genessee, F and Upsher, J. A. (1996). *Class room based Evaluation in Second Language Education.* Oxford: Oxford University press.

Grandman, H.L and D.J. Reed (1997) Assessment and Second Language Teaching" In M. Bardovi-harling.(Ed.) Beyond Methods; Components of second Language Teacher Education. (pp 200-205). New York ;Mc-hill.

Gronulonad E.N(1981): *Measurement and Evaluation in Teaching.* Macmillan publishing CO.INC, New York.

Harrison, A. (1983). *A language Testing Hand Book.* London: Macmillan Publishers.

Harmer, J. (1991). *The practice of English Language Teaching.* Longman, Group Limited.

Heaton, J.B. (1975). *Writing English Language Tests* : London: Longman.

———(1990). *Classroom Testing.* London. Longman.

Henning, g. (1987). *A Guide to Language Testing.* Cambridge: New Bury House Publishers.

Hughes, A. (ed.) (1988). *Testing English for University Study.* ELT. Document 127, Hong Kong: Modern English Publications with the British Council.

——— (1989). *Testing for Language Teachers.* Cambridge: Cambridge University press.

Lado, R. (1961). *Language Testing.* London: Lowe and brydon. Ltd.

Mehrens, W. A and L. Lehmann. (1974). *Standardized Tests in English* (2nd ed.) New York: Holt, Rinehart and Winston.

Nunan, D. (1988). *Syllabus Design.* Oxford: Oxford University Press.

Oller, J. W (1979). *Language Testing at School.* London: Longman group Limited.

Richards, J. C and T.S, Rodgers. (1986). *Approaches and Methods in Language Teaching.* A Description and Analysis. Cambridge: Cambridge University press.

Ur, P. (1996). *A course in Language Teaching.* Practice and Theory: Cambridge: Cambridge University press.

Weir, C. J (1990). *Communicative Language Testing.* New York: Prentice Hall.

——— (1993). *Understanding and Developing Tests.* London: Prentice Hall.

በሸሬ 2ተኛ ደረጃ ትምህርትቤት የ 2002 ዓ/ም የ 10ኛ ክፍል የአንደኛ ሰሚስተር ሚድ ፈተና::

የተሰጠዉ ግዜ 20 ደቂቃ ኮድ ሀ

1. **ከዚህ በታች ለቀረቡት ሀሳቦች ትክክል ከሆነ "እዉነት" ትክክል ካልሆነ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልስ /ሺ/**

--------- 1. ማንኛዉም ቋንቋ ሙሉ በሙሉ ራሱን የቻለ ነዉ ::

--------- 2. ሁሉም መግብያቋንቋ ነዉ::

--------- 3. ጥገኛ ምዕላድ ራሱን ችሎ መቆም የሚችል የምዕላድ ኣይነት ነዉ::

--------- 4. ምሳሌያዊ ኣነጋገር ከሌሎች የስነቃል ኣይነቶች የሚለይበት ግዜና ቦታ ተወስኖለት የሚነገር ኣለመሆኑ ነዉ::

--------- 5. ቋንወቋ በትምህርት ወይም በለመዳ ይገኛል::

2. **ከዚህ በታች ለቀረቡት ፊሊጦች በተመሳሳይ ኣዛምዷቸዉ::**

ሀ	ለ
------ 6. ክርሞ ጥጃ	ሀ/ ረጅም ሰዉ
----- 7. እምብርት ኣልባ	ለ/ ቻይ፣ ታጋሽ
----- 8. ብቅል ኣዉራጅ	ሐ/ ኣኮረፈ
----- 9. ለምቦጩን ጠላ	መ/ ተንኮለኛ
----- 10. ሆደ ሰፊ	ሠ/ የማይሻሻል
	ረ/ ሆዳም
	ሰ/ እርግጠና ሆነ
	ሸ/ ደፋር

3. ከዚህ በታች ለቀረቡት ሀሳቦች ትክክለኛዉን መልስ የያዘ ፊደል ምረጥ/ጪ/ ::

--------- 11. ከሚከተሉት ኣማራጮች መካከል ኣንዱ ቋንቋ የሰዉ ልጅ ብቻ መሆኑን የሚገልፅ ነዉ::

ሀ/ ደመነፍሳዊ ሐ/ሰብኣዊ

ለ/ ዘፈቀዳዊ መ/ ይወለዳል፣ያድጋል፣ይሞታል

--------- 12. ከሚከተሉት ኣማራጮች መካከል ኣንዱ ቃል መስራች ምዕላድ ኣይደለም::

ሀ/ -ነት ለ/-ኣማ ሐ/ -ኣኛ መ/ -ኣዊ

-------- 13. "ድንጋይ ብለን ድንንጋያማ ስንል ከ ---- ወደ ---- የቃል ክፍልነት ተቀይረዋል

ሀ/ ስም-ግስ ሐ/ ቅፅል - ስም

ለ/ስም-ቅፅል መ/ ግስ-ቅፅል

------- 14. ከሚከተሉት ምሳሌያዊ ንግግሮች ኣንድ በሚያስተላልፈዉ መልዕክት የተለየ ነዉ::

ሀ/ ዛፍ በሌለበት እምባጨ ኣድባር ነዉ

ለ/ ጋኖች ኣለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ

ሐ/ የቀና ሲታጣ ይመለመላል ጎባጣ

መ/ ሀምሌና መ·ሽራ ሳይገለጡ ነዉ

-------- 15. ከሚከተሉት ኣንዱ የተለየ ነዉ ::

ሀ/ ምሳሌያዊ ኣነጋገር ሐ/ ተረት

ለ/ እንቆቅልሽ መ/ ልቦለድ

ኣዘጋጅ

የኣማርኛ ትምህርት ክፍል



የ2003 ዓ/ም የዓዲ ዳዕሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአንደኛ ሰሚስተር ሚድ ፈተና ለ10ኛ ክፍል የቀረበ አማርኛ ፈተና

የተሰጠዉ ግዜ 30' የያዘዉ ነጥብ 25 የጥያቄ ብዛት 15

ስም _____ ክፍል ሴክሽን ቁጥር

መምርያ አንድ የሚከተሉት ጥያቄዎች እዉነት ወይም ሃሰት በማለት መልሱ

_____ 1. ቃላት የሚመስረቱት በቋንቋ ዉስጥ በሚገኝ ድምፀ ልሳናት ነዉ።

_____ 2. ቅጥያዎች ራሳቸዉ ችለዉ ትርጉም አይሰጡም።

_____ 3. መ-ሉ ስሜትን የሚሰጥ የቃላት መስተጋብር ዓረፍተ ነገር ይባላል።

_____ 4.በቋንቋ ክሂል ቀደም ተከተል ዉስጥ የመጀመርያዉን ደረጃ የሚናገኘዉ ማዳመጥን ነዉ ።

_____ 5. በክርክር ስነስርዓት ክርክሩን ጀምሮ የሚፈፅመዉ ሊቀ መንበሩ ነዉ።

መምርያ ሁለት፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች እንደየአመጣጣቸዉ ትክክለኛዉን መልስ የያዘ ፊደል ምረጡ

_____ 6. አንባብያን አንድ ልበ ወለድ አንብበዉ ስያበቁ በተለይ በአእምሯቸዉ የሚቀርፁት _____ ነዉ።

ሀ/ ጭብጡን ለ/ ግፀ ባህሪዉን ሐ/ ድርጊቱን መ/ መቸቱን

_____ 7. ከሚከተሉት ዉስጥ በያዘዉ ቅጥያ ልዩ የሆነዉ የትኛዉ ነዉ?

ሀ/ ሆዳም ለ/ ቅማላም ሐ/ ነፋጣም መ/ ኮቴ

_____ 8. እንጃራዉን በበርበሬ _____ በላ። የባዶ ቦታዉ የሚስማማዉ ቃል _____ ነዉ

ሀ/ እያጣቀስክ ለ/ እየደቆስክ ሐ/ እየራመድክ መ/ እየነካህ

_____ 9. የሴትዮዋድምፅ መረዋ ነዉ ። የቀረበበት የዘይቤ ዓይነት _____ ነዉ

ሀ/ ተለዋጭ ለ/ ተምሳሌት ሐ/ ሰወኛ መ/ ተነፃፃሪ

_____ 10. የዛሬዉ ወጥ ጣት ያስቆረጥማል የተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ

ሀ/ የጓጓል ለ/ ያምራል ሐ/ ይጣፍጣል መ/አንሰዋል

መምርያ ሶስት ከሚከተሉት ቃላት ከተሰጡት አማራጮች መካከል በትርጉም የሚስማማቸዉን ፊለጣዊ አነጋገር በመምረጥ መልስ/ሺ/

_____ 11/ ቅቤ አንጓች

ሀ/ እወደድ ባይ ለ/ አዉደልዳይ ሐ/ ዘመድ ወዳጅ መ/አሽሚጣጭ

_____ 12/ አፉን ሻረ

ሀ/እህል ዘራ ለ/እህል ጠላ ሐ/ እህል ቀመሰ መ/ሁሉም

_____ 13/ የጉም ጅብ

ሀ/ ፈሪ ለ/ አይኑ የማያይ ሐ/ ስግብግብ መ/ ጅል

_____ 14/ ዓይነ ገመድ

ሀ/ግምት ለ/እዉነተኛ ሐ/ አይነ አፋር መ/አይነ ልም

_____ 15/ ጀሮ ጠቢ

ሀ/ ሰላይ ለ/ የማይሰማ ሐ/ ባፉ የሚማታ መ/ ተለማማጭ

አዘጋጅ አ/ብ ና አ/ተ

የ2003 ዓ/ም የሸሬ እንዳስላሴ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ትምህርት
አጋማሽ ፈተና።

= ለ =

ስም_____ ክፍል_____ ቁጥር_____ ግዜ 30 ደቂቃ

መምርያ 1፦ የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ "እውነት" ስህተት ከሆነ ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ።

_____1. የእርባታ ምዕላዶች በቃል ላይ ሲጨመሩ ቃልን ወደ ሌላ የቃል ክፍልነት ይቀይራሉ።

_____2. ቋንቋ የሚያገለግለው ለሠብኣዊ ፍጡር ብቻ ነው።

_____ 3. ቋንቋ ከተናጋሪው በዘር የሚተላለፍ ደማዊ ግኑኝነት አለው።

_____4. ምሣሌያዊ አነጋገር ሃሣብን ግልፅ(ጉልህ) ለማድረግ ይረዳሉ።

_____5. ሆደ ሠፊ የሚለውን ፊሊጣዊ አነጋገር ሆዳመ የሚል ፍች ይስማማዋል።

መምርያ 2. በ"ሀ" ለተዘረዘሩት ቃላት ከ"ለ" ረድፍ ተመሣሣያቸውን ምረጡ።

ሀ	ለ
_____ 6. ሳቢያ	ሀ/ አሰፈላጊ
_____7.ማእበል	ለ/ ጭቅጭቅ
_____8. ውዝግብ	ሐ/ ረግረጋማ ቦታ
_____9. ረገድ	መ/ ነውጥ
_____10. ረብ	ሠ/ መሳብ
	ረ / ምክንያት
	ሰ/ ኣኳያ
	ሸ/ ፋይዳ

መምርያ 3፦ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘ ሆሄ ብቻ ምረጡ።

_____11. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች ትክክልኛው የትኛው ነው?

ሀ/ ጥቁር ሠዎች መጡ ሐ/ ጥቋቁር ሠዎች መጡ

ለ/ ጠቋራው ሠዎች መጡ መ/ ጥቁሮቹ ሠዎች መጡ

_____12. ከሚከተሊት ምሣሌያዊ ንግግሮች ውሥጥ በአሁኑ ሠዎች ተቀባይነት የሌለው የትኛው ነው? ሀ/ የእነ ቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሠንበሌጥ

ለ/ ሴት የሠረችው ቤት ጅብ ሲጮህ ይፈርሣል

ሐ/ ራት የሌለው ምሣ አማራት መ/ በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደሰ

____ 13. እንባ ጠባቂ ሲል

ሀ/ ተቆርቋሪ ለ/ አልቃሽ ሐ/ ሌባ መ/ አሰለቃሽ

____ 14. የምትወዱትን ሁሉ ሳተወዱ ቀራችሁ በሚለው ዐ.ነገር ባለቤት ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

ሀ/ እኛ ለ/ እናንተ ሐ/ እነሱ መ/ እሳቸው

____ 15. ከፍትፊቱ ፈቱ ለሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር በፍቺ የሚስማማው የትኛው ነው?

ሀ/ ከአፍ የወጣ ቃል ሊመለስ አይችልም።

ለ/ ጥጋብ ሲበዛ ችግር ያስከትላል

ሐ/ ችግር ከደረሠ በኋላ መሯሯጥ ትርፍ ድካም ነው

መ/ ፈገግታ ከምግብ ይበልጣል።

____16. <u>አመድ አፋሽ</u> ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር በፍች የሚስማማው_____

ሀ/ አመዳም ለ/ ንፋግ ሐ/ ሰጥቶ የማይመሰገን መ/ የሚመሰገን

____17. <u>ነጋጠባ</u> አትጨቅጭቀኝ ሲል ለተሠመረበት አባባል ተስማሚው_____

ሀ/ ፊትም ኋላም ለ/ ዛሬም ነገም ሐ/ አሁንም ድሮም መ/ አምና

____18. ከሚከተሉት ውስጥ ትክክልኛ አባባል የቱ ነው?

ሀ/ ዕድሜዬ ሃያ ስድስት አመት ነው። ለ/ ዕድሜዬ ሃያ ስድስት አመቴ ነው።

ሐ/ ዕድሜዬ ሃያ ስድስት አመቴ ነኝ። መ/ ዕድሜዬ ሃያ ስድስት ነኝ።

____19. አይኑ አዋጅ ሆነበት ሲል፦

ሀ/ መምረጥ አቃተው ለ/ ማየት ተሳነው

ሐ/ መናገር አማረው መ/መልስ አልተሰጠም

____20. ከሚከተሉት ውስጥ የልቦለድ አባባ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ/ ገፀ-ባህሪ ለ/ መቼት ሐ/ ተራኪ ድርሰት መ/ ሴራ

አዘጋጅ

የአማረኛ ት/ት ክፍል

የ2002 ዓ.ም የዓ/ዳዕሮ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የአንደኛ ሰሚስተር የአማርኛ ት/ት ለ 10ኛ ክፍል
ጊቀረበ። የጥያቄ ብዛት 35 የያዘዉ ነጥብ 50% የተሰጠዉ ግዜ 50

ስም----------ክፍል ----------ሴክሽን--------ቁጥር--------
መመርያ አንድ፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ፡ እንደየ አመጣጣቸዉ ትክክለኛ መልስ በመምረጥ ከተሰጡት
አማራጮች መካከል መልስ/ሺ።
-------1.ታማኝነታቸዉን ጠንቂቄ አዉቃለሁ። በሚለዉ የተሰመረበት ቃል በምዕላድ ሲተነተኑ
ሀ/ታማኝነት-አቸዉን ለ/ታማኝ-ነት-አቸዉ-ን
ሐ/ታማኝ-ነት-አቸዉን መ/ታማ-ኝነታ-አቸዉን
-------2.አበባ ከመጣ እመጣለሁ ለሚለዉ አንድ ትክክል ነዉ።
ሀ/የአበበ መምጣት ካወቅሁ እመጣለሁ፣ አለበለዚያ አልመጣም።
ለ/አበበ ካልመጣ እመጣለሁ።
ሐ/አበበ ቢመጣም ባይመጣም እመጣለሁ።
መ/እኔ ከመጣሁ አበበ አይመጣም፡፡
-------3.ከሚከተሉት ዉስጥ አንድ ከልበለድ ቴክኒክ የማይካተት የትኛዉ ነዉ?
ሀ/አንባር ለ/ገለባ ሐ/ ንግር መ/ምልልስ ሠ/ቋንቋ
-------4.የአንድ ልቦለድ ፅሑፍ ታሪክ የማን ታሪክ ነዉ?
ሀ/ የገፀባህርያት ለ/የግጭት ሐ/የመቼት መ/የጭብጥ
-------5.አወይ በመምህር ላይ ያለበት አባዜ፣
አስተዋይ ተማሪ በጠየቀዉ ጊዜ። በሚለዉ ባለ ሁለት ስንኝ ግጥሙ ከምን የግጥም ዓይነት ይመደባል?
ሀ/ከሰንጎ መገን ቤት ለ/ ከቡሄበሉ ቤት ሐ/ከወልቤት መ/ከድብልቅ
-------ር.ከሚከተሉት ዉስጥ ትክክል ያልሆነዉ የትኛዉ ነዉ?
ሀ/ ቋንቋ ማህበራዊ ክስተት ነዉ።
ለ/አንድ ቋንቋ ከሌላዉ አይበልጥም፣ አያንስም።
ሐ/የአንድ ሕ/ሰብ ቋንቋ፣ ሕብረተሰብ የማያዉቀዉን አደስ ፅንሰ ሓሳብ መግለፅ ይችላል።
መ/በቋንቋ አማከኛነት አነድን ጉዳይ ቦታና ጊዜ ሳይወሰነዉ መናገር ይችላል።
-------7.በፍርድ ቤት ሌላን ግለ ሰብ ወይም ድርጅት ወክሎ የሚከራከር ግለ ሰብ በአንድ ቃል
ሲገለፅ የትኛዉ ነዉ? ሀ/ ዳኛ ለ/ ምስክር ሐ/አፈ ጎባኤ መ/ጠበቃ
-------8.ጨቅጫቃዉ አባወራ ከሚስቱ ጋራ ተጣላች። የሚታየዉ ስህተት
ሀ/የሀረግ አለመስማማት ለ/የቁጥር አለመስማማት
ሐ/የባለቤትና የተሳቢ አለመስማማት መ/ የፃታ አለመስማማት
-------9. ከሚከተሉት ዉስጥ ትክክለኛ ያልሆነ የቃል ጥምረትን የያዘዉ /ፊደል የትኛዉ ነዉ?
ሀ/ ተዉኔት---ታዳሚ ለ/ልቦለድ---አንባቢ ሐ/ ተዉኔት---- ምዕራፍ
መ/ልቦለድ---ገፀባህሪ ሠ/ተዉኔት---ገፀባህሪ
-------10. ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ዉስጥ ተሳቢዉ ባለቤት የሆነበት/ተገብሮ/ ዓ/ነገር የሆነዉ የትኛዉ ነዉ?
ሀ/መላኪ ዛፍን ቆረጠዉ። ሐ/ብርጭቆዉ ተሰበረ።
ለ/ስራአሰኪያጅ ሰብስባዉን በንግግር ከፈቱ። መ/ወታደሩ ጠላቱን ማረከዉ።
-------11.ባእንቀፅ ዉስጥ የኃይለ ቃል መገኛ ስፍራ የት ነዉ?
ሀ/ መጀመርያ ለ/ መጨረሻ ሐ/ መካከል መ/በሁሉም ሊገኝ ይችላሉ
-------12.በልቦለድ ዉስጥ መቼት--------ነዉ፡፡
ሀ/የልበለድ ታሪክ የተፈፀመበት በታና ጊዜ።
ለ/የልቦለድ ታሪክ የሚያጠነጥንበት ቁም ነገር
ሐ/በልቦለድ ዉስጥ የገፀባህርያቱ ምልልስ
መ/በገፀባህርያቱ መካከል የሚፈጠር አለመስማማት
-------13.ሓኪሙ ለባሽተኛዉ መከረዉ። በሚለዉ ዐ.ነገር ዉስጥ የሚታየዉ ስዋስዊ ስህተት መንድን ነዉ?
ሀ/ የቀጥተኛ ተሳቢዉ በትክክለኛ ቅርፁ አለመቀመጥ
ለ/የባለቤት የግስ በቁጥር አለመስማማት
ሐ/የተሳቢና ግስ በቁጥር አለመስማማት
መ/የባለቤቱ በትክክለኛዉ ቦታዉ ላይ አለመቀመጥ
-------14.ጀምበር መጥለቅ ጀምራለች፣ ከብቶቹ------እስከአሁን ወደበረት አልገቡም።
በባዶ በታዉላይ መቀመጥ የሚገባዉ አያያዥ የትኛዉ ነዉ?
ሀ/ እንካ ለ/ ግን ሐ/-ም መ/-ስ
-------15. ከሚከተሉት ዉስጥ ሰማዊ ሓረግ የሆነዉን ይትኛዉ ነዉ?
ሀ/የልክ አዋቂ ለ/የወጣት ስነፍ ሐ/ ብርቱ ስራ መ/የዘረበት ስካራም

------16. በረሀብተኞች ዓለም ዐቀፍ ዉስጥ በቀደም ተከተል የተቀመጠዉ የትኛዉ ነዉ?
ሀ/ ማነገር፡ ማዳመጥ፡ መፃፍ ማንበብ
ለ/ ማ፡ዳመጥ፡ መናገር፡ መፃፍ፡ ማነበብ
ሐ/ማዳመጥ፡ መናገር፡ ማንበብ፡መፃፍ
መ/ማንበብ፡መፃፍ፡ መናገር፡ማዳመጥ
-------17. አንድን ክንዉን ወይም ሂደት በሚመለከት ሪፓርት የሚቀርብበት የፅሑፍ ዓይነት የትኛዉ ነዉ?
ሀ/ ዘገባ ለ/ቃለጉባኤ ሐ/ ክርክር መ/ቃለ መጠይቅ
------18. ስልጣን ተሰጥቶታል። በሚለዉ ዓረፍተነገር ዉስጥ የቀረበዉ ሓሳብ በአንድ ቃል ቢገለፅ የትኛዉትክክል ነዉ
ሀ/ተሸማል ለ/ ተረክባል ሐ/ አድጎዋል መ/በልፅጋል
---------19.ከሚከተሉት ዉስጥ አንድ ከስነ-ግጥም ባህርያት ዉስጥ ሊጠቀስ አይችልም።
ሀ/ በሓረጋትና በስንኞች የተከፈፈለ መሆኑ። ሐ/ሞት የሚጠብቅ መሆኑ
ለ/ ረዥም ዕድሜ ያለዉ መሆኑ መ/ሲነባብ ሙዚቃዊ ቃኖ ያለዉ መሆኑ
---------20.ራስህን ዳህና አድርጎ ማወቅ ብልህነት ነዉ። በሚለዉ ዐ.ነገር ዉስጥ ስማዊ ሓረጉ የሚያመለክት፡
ሀ/ ራስህን ደህና አድርጎ። ሐ/ራስህን ደህናአድርጎ ማወቅ ብልህነት ነዉ፡፡
ለ/ ራስህን ዳህና አድርጎ ማወቅ መ/ አድርጎ ማወቅ ብልህነት ነዉ።
መመሪያ ሁለት፡ ለሚከተሉት ቃላት ወይም ሓረጋት ለተሰመረባቸዉ ተመሳሳይ ፍቺ ሊሆኒ የሚችሉ ከተሰጡአማራጮች
---------21.የወይዘሮ ወርቅነሽ ንግግር ዉስጠ ወይራ ነዉ።የተሰመረበት ቃል የወ/ሮ ወርቅነሽ
ንግግር----------መሆኑን ያስገነዝባል።
ሀ/ለጀሮ የሚከብድ ለ/ምስጢር አዘል ሐ/ ግልፅ ያልሆነ መ/ስሜት የሚጎዳ
--------22. አልማዝና ወርቅነሽ ልብሳቸዉን አጠቡ። የተሰመረበት ቃል የትኛዉን ይገልፃል።
ሀ/ሥስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አንስታይ ያታን
ለ/ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባእታይ ያታን
ሐ/ ሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥር አንስታይ ያታን
መ/ሥስተኛ መደብ ብዙ ቁጥር አነስታይ ያታን
--------23ብዙ ካህናት በሠርጉላይ አልተገኙም። የተሰመረበትን ቃል በቅርፅ የማይመሳሰለዉ የትኛዉ ነዉ?
ሀ/አደባራት ለ/ዓመታት ሐ/ገዳማት መ/ሊቃዉንት ሠ/ምሁራት
--------24.የፊፀመዉ ስህተት በገሃድ እየታየ ለምን እንደማያምን አልገባኝም።
ሀ/ በእዉነት ለ/ በግልፅ ሐ/በፍፁም መ/ በጥራት
--------25.ወንድሙ ዐይን አዉጣ ነዉ።
ሀ/ የአይን ሀኪም ለ/ ይሉኝታ ቢስ ነዉ ሐ/አይን አፍር መ/አይን ያጠፍል
--------26.በስፈር ዉስጥ ያስቸግሩ የነበሩ ሌቦች በፖሊሶች ታፈሱ።
ሀ/ ተሰበሰቡ ለ/ ተገኙ ሐ/ ተያዙ መ/ ታጎሩ
--------27.አይኔ ዉስጥ ጉድፍ ገባ።
ሀ/ የማልወደዉን ሰዉ አየሁ ለ/ትንኝ ገባ ሐ/አባራ ገባ መ/ቆሻሻ ገባ
መመርያ ሥስት፡ ለሚከተሉት ጥያቄ በምን የዘይቤ ዓይነት እንደቀረቡት ከተሰጡት አማራጮች
ትክክለኛ መልስ በመምረጥ መልስ/ሺ።
--------28.የፊንጣዋች ጭርጭርታ ከወንዙ እንቁራሪቶች ቁርርታና እልልታ ጋር በመቀባበል
የተወሳሰበ ህብረ ሙዚቃ ይፈጥራል።
ሀ/ ሰዉኛ ለ/ አያዎ ሐ/ ተምሳሌት መ/ተለዋጭ ሠ/ አነፃፃሪ
--------29.መቅደላሲ ሉት አድዋላይ መጣ።
የክረምት ብራቅ የሰማይ ቁጣ።
ሀ/ ተለዋጭ ለ/ ሰዉኛ ሐ/ ተነፃፃሪ መ/ አያዎ
--------30.የቴሌቪዥን ማሰራጫዉ ስማዩን ቀድዶ የገባ ይመስላል።
ሀ/ ተነፃፃሪ ለ/ ሰዉኛ ሐ/ ተምሳሌት መ/ እንቶኔ
መመሪያ አራት፡ ከሚከተሉት ቃላት ከተሰጡት አማራጮች መካከል በትርጉም የሚስማማቸዉን
ፊሊጣዊ አነጋገር በመምረጥ መልስ/ሺ።
--------31. ቅቤ አንጋች ሀ/እወደድባይ ለ/አዉደልዳይ ሐ/ዘመድ ወዳጅ መ/አሽማጣም
--------32. ብቅል አዉራጅ ሀ/ሽቃጭ ለ/መላሎ ሐ/ሰካራም መ/ጠንሳሽ
--------33. እንካበእንካ ሀ/አገም ጠቀም ለ/እከክልኝ ልከክልህ ሐ/ፊትለፊት መ/ወሰድ መላስ
--------34. አይኑ-ገመድ ሀ/ እዉነተኛ ለ/ግምት ሐ/ አይን አፍር መ/አይነልም
--------35. አይኑንበዓይኑ አየ፡ ሀ/ነመስተዋት ተመለከተ ሐ/ዓይኑን አየሁት
ለ/ልጅ ወለደ መ/ዓይኑ ንበራለት

መልካም ፈተና፡ ኤድስን በጋራ እንግታ! ቃላችንን
አዘጋጅ ፡ አ.ብ/ አ. ተ

20, 5, 35
14 11 13 38
31 13 44

Subject code 01

ሽሬ ኣጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ 2002 10ኛ ክፍል የኣማርኛ ሞዴል ፈተና

የተሰጠዉ ግዜ 40 ደቂቃ

ኮድ A

ከዚህ በታች በቀረበዉ ግጥም ላይ ተመርኩዛችሁ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ።

እስከ ግዜዉ ድረስ እስኪሞላልኩ
የጀግና ፈረስ ነዉ የሰዉ ሁሉ መልኩ

1. የመጨረሻዉ ስንኝ መነኛ ሀረግ ማነዉ?
   A/ እስከ ጊዜዉ ድረስ C/የጀግና ፈረስ ነዉ
   B/ለ የሰዉ ሁሉ መልኩ D/ እስኪ ሞላ ልኩ
2. ግጥሙ ምን ያህል ሀረጎች ኣሉት?
   A/ 6 B/ 4 C/ 2 D/ 8
3. የግጥሙ ቤት ማነዉ?
   A/ኩ B/ለ መልኩ C/ሐ እስኪ ሞላልኩ D/ መ.የለም

ከዚህ በታች ኣንድ ኣንቀፅ ቀርቧል። በኣንቀፅ ዉስጥ ሊገቡ የሚችሉ ስርዓተ ነጥቦችን ከተሰጡት ኣማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘዉን ፊደል ምረጡ።

ወዳጄ ስለቤተሰቡ ሲናገር እንዲህ ካሎኝ እንደነበር ኣስታዉሳለሁ። 1 የተወደዳችሁ ወዳጄ ሆይ 2 ቤተሰቤ የጣለኝ እንዳይመስላችሁ 3 የኔቤተሰብ በኢ/ያ የተከበረ ነዉ። ቅዱስ ጳዉሎስ ደቀ መዛሙርቱን 4 እግዚያ ብሄርን ለምኑልኝ 5 እንዳላቸዉ ሁሉ ቤተሰቦቹም እግዚያብሄርን ስለ እኔ ይለምኑታል። 6

4. በቁጥር "1" ና "6" ሊገባ የሚችለዉ ስርዓነ -ነጥብ የቱ ነዉ?
   A/ ' ' B/ " " C/ ..... D/ መ.የለም



11. በሀረግ ዉስጥ የሚገቡ ተዋቃሪዎች ተግባራቸዉ _____ ነዉ?
A/ መሙያ B/ ኣጎላማሽ C/ መስተኣምር D/ ሁሉም

12. ከሚከተሉት ኣገላለፃች ኣንዱ ሰማዊ ሀረግ ነዉ?
A/ የሰዉ ልጅ C/ ተዘበድ ጠያቂ
B/ የልጅ ኣስተዋይ D/ AናC

13. ድርጊቶችና ሁነቶች በጊዜና ቦታ ቅደም ተከተል የሚያቀርብ ድርሰት ___ ይባላል።
A/ ገላጭ B/ ተራኪ C/ ስዕላዊ D/ ኣመዛዛኝ

14. ስዋስዋዊ ስህተት የሚታይበት መዋቅር የትኛዉ ነዉ?
A/ ያንን ቀበቶ ስጠኝ C/ ቀበቶየን ስጠኝ
B/ የኔን ቀበቶ ስጠኝ D/ B ናC

15. እንደ ኣንበሳ ያገሳል።የተሰመረበት ቃል የሚመደበዉ በየትኛዉ የቃል ክፍል ነዉ?
A/ ስም B/ ቅፅል C/ መስተዋድድ D/ ተ/ግስ

16. መታችሁት በሚለዉ ግስ ዉስጥ ያለዉ ባለቤት ኣመልካቹ ጥገኛ ምዕላድ ------ ነዉ?
A/ ታችሁ B/ መት C/ ኣችሁ D/ሁት

17. ከሚከተሉት ኣንዱ የተለየ ነዉ?
A/ ቋንቋ ሰብዓዊ ነዉ C/ ቋንቋ ይወለዳል፣ያድጋል፣ይሞታል
B/ሐ ቋንቋ በት/ት ይገኛል D/ ቋንቋ ደመነፍሳዊ ነዉ

18. ቋንቋ ይዋዋሳሉ፣ይወራረሳሉ ሲል
A/ ቋንቋ ስርዓታዊ ነዉ
B/ ቋንቋ ሰብዓዊ ነዉ
C/ ቋንቋ የሰዉ ብቻ ነዉ
D/ ማንኛዉም ቋንቋ ሙሉ በሙሉ ራሱን የቻለ ኣይደለም

19. ከሚከተሉት ኣንዱ የዘገባ ባህሪ ኣይደለም
A/ ወቅታዊነት B/ ግልፅነት C/ ፈጠራዊነት D/ ተነባቢነት

Booklet code 62
Subject code 01

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንበብ የተጠቀመዉን የዘይቤ አይነት ከአማራጮች መካከል ትክክለኛዉን መስል የያዘዉን ፊደል ምረጡ።

30. ህይወት ያለዉ በድን ሆንክብኝ
    A/ እንቶኔ B/ ኣያዋ C/ ተምሳሌት D/ ሰወኛ
31. ምድሪቱ ተራበች
    A/ ግነት B/ ሰወኛ C/ ተምሳሌት D/ ተለዋጭ
32. በኢ/ያ ጥቁር ልብስ ለህዘን ይለበሳል
    A/ ተነፃፃሪ B/ ተምሳሌት C/ ምፀት D/ ግነት
33. መልኩ ልክ ኣያቱን ነዉ
    A/ ተለዋዋጭ B/ ተነፃፃሪ C/ ግነት D/ ኣያዋ
34. መሃመድ በግ ነዉ
    A/ ተለዋጭ B/ ግነት C/ ምፀት D/ ተነፃፃሪ

ከዚህ በታች የቀረቡትን ቅጥያዎች በጥሞና በማንበብ ከአማራጮች መካከል ትክክለኛዉን መልስ የያዘዉን ፊደል ምረጡ

35. ሁልግዜ ቤት መስራት በልቤ እመኛለሁ።
    ኣንድም ማዘን የለኝ ወዴት እገኛለሁ። የዚህ ቅኔ ህብረቃል ____ ነዉ
    A/ ወዴት እገኛለሁ C/ ኣንድም ማዘን የለኝ
    B/ ኣንድም ማዘን D/ BናC
36. ለህይለኛ ሴት ለምትቆጣ
    ምነዉ መካሪ ባልታጣ። የዚህ ቅኔ ሰሙ ---- ነዉ ።
    A/ ባልታጣ C/ ህይለኛ ሴት የሚገስፅ ባልጠፍታል
    B/የሚመክር ባልጠፍ D/ AናC
37. ቀፎ ኣለ ኣሉ ባገርህ
    ኧረ ተዉ ማር እባክህ። የዚህ ቅኔ ወርቅ ----- ነዉ
    A/ እባክህ ማር ስጠኝ C/ እባክህ ምህረት ኣዉርድ
    B/ ይቅርታ ኣድርግ D/ BናC

Booklet Code 02
Subject Code 01

38. ሰዉ ሁሉ ሲማር ሲያወቅ
እኔስ ተምሬም አላዉቅ#የዚህ ቅኔ ህብረ ቃል ------ ነዉ
A/ ተምሬም አላዉቅ C/ ተምሬም
B/ ት/ት ተምሬም አላዉቅም D/ ምህረት ተደርጎልኝ አያዉቅም

39. ስራም አልሰራም ምናምን
እያትማ ጣቴን# የዚህ ቅኔ ወርቅ ----- ነዉ#
A/ ጣቴን ተመልከታት C/ ድህነቴን እየዉ
B/ እጦቴን ተመልክተዉ D/ BናC

40. ሁል ጊዜ በስጋት በዱር ከመኖር
ቆቅስ ብትመረቅ ይሻላት ነበር# የዚህ ቅኔ ህብረቃል ----- ነዉ #
A/ ብትመረቅ C/ ይሻላት ነበር
B/ ቆቅ ለማዳ ሆና ከሰዉ ጋር ብትኖር ጥሩ ነበር D/ ቆቅስ ብትመረቅ

አዘጋጅ አማርኛ ት/ት ክፍል

1. ሐ	11. ጋ	21. ለ	31. ለ
2. ለ	12. ለ	22. ጋ	32. ለ
3. ለ	13. ለ	23. ጋ	33. ለ
4. ለ	14. ለ	24. ጋ	34. ለ
5. ለ	15. ሐ	25. ለ	35. ለ
6. ሐ	16. ሐ	26. ለ	36. ለ
7. ጋ	17. ጋ	27. ለ	37. ጋ
8. ሐ	18. ጋ	28. ሐ	38. ለ
9. ለ	19. ሐ	29. ሐ	39. ጋ
10. ለ	20. ለ	30. ለ	40. ለ

Code A (02)

1 ክፍለ ጊዜ ፈተና ትምህርት ዓይነት የ2002ዓ.ም ሁለተኛ መንፈቅ ዓመት 15 ክፍል ለሠራተኞች

I የሚያገለግሉትን ቃላት ከአንደኛው ከተሰጡት ውስጥ ተመሳሳይ ትርጉም ያለውን ጥንድ ፊደል ብቻ ይምረጡ። 10X1

ሀ	ለ
1, ጀነሬተር	ሀ, ሰርክዩት
2, ሀዋጅ	ለ, ሽቦ
3, የወረዳ ቁጥጥር	ሐ, መጠገኛ
4 የሙከራ ውጤት	መ, ትክክለኛ ያልሆነ
5 የጉዳት ሁኔታ	ሠ, ጉዳት ያደረሰ
6, ጎጂ ተግባር	ረ, የጉዳት ዝርዝር
7 ተገቢ ያልሆነ	ሰ, ቁሳቁስ የማቀነባበሪያ ማሽን
8 መከላከያመሳሪያ	ሸ, ማንኛውም የሚያስቀጣ ተግባር
9, ጨለማ	ቀ, ቁጥጥርንና ጥገናውን
10, ጥንቃቄ	በ, ጨለማ ቦታውን ለማብራት የሚያገለግል መሳሪያ
	ተ, ተገቢነት
	ቸ ጎጂ

II ከሚከተሉት ጥያቄዎች ሀሳብ የሚሰጠውን ትክክለኛ መልስ ብቻ በመምረጥ ፃፉ። 2X5

1, _____ ለመሥራት ከሚያስችሉን ጥንቃቄዎች አንዱ ነው።
ሀ, ጉዳይ ለ, ጉጉት ሐ, ቁጠባ መ, ሀ እና ሐ

2, ለመሥራት _____ ጊዜውን ለተሳሳተው ስዎች መስጠት ነው ብለን ስናስብ ለማለት የፈለግነው ነገር ምንድን ነው?
ሀ, የሥራ ፍጥነት ለ, የሥራ ጫና ሐ, መረጋጋት መ, መረጋጋት

3, "ወዳጄን ጉዳት ከማየት ዝናዬ ጉዳት ይሻላል" የሚለው አገላለፅ ከሚከተሉት ውስጥ የትኛውን የሚገልፅ ነው? ሀ, ለሌሎች ለ, ጉጉት ሐ, ሥርቆት መ, ሥነ ምግባር

4, ከንግግሩ ውስጥ ጉዳት ያደረሰው ሰው ስለመሆኑ የሚያመለክተው ቃል የትኛው ነው?
ሀ, ጉዳት ለ, ሥራ ሐ, ይሰማል መ, ይሉኝ ነው

5, ያለው ሰው ለሚያጠፋው ሥራ ተጠያቂ ስለመሆኑ የሚረዳው ለ — ነው።
ሀ, ለ ይጠቀም ለ, ለ ነው ሐ, ለ ነው መ, ለ ሥራ ነው

III ከቃላት አጠቃቀም አንፃር ትክክለኛ ትርጉም ያለውን ቃል ብቻ በመምረጥ ፃፉ። 1X6

1,
1. ሀ, ጉዳት ለ, ጉዳይ ሐ, መጠገኛ መ, መጀመሪያ
2 ሀ, ጉጉት ለ, መጠበቅ ሐ, ትክክል መ, ጉጉ
3, ሀ, ቁርስ ለ, ጉጉት ሐ, ጉዳት መ, ትክክል
4, ሀ, ዘለፋ ለ, ጎጂ ሐ, ጉዳት መ, ማጥፋት
5, ሀ, ቁጠባ ለ, ጨ ሐ, መጠበቅ መ, ትክክል

ለመለስ ለመረጥ የፈለጉትን

I. ትክክለኛ	II ምላሽ	III. ትክክለኛ ትርጉም ያለው የሚለው ለመለሱት
1.	1.	1.
2.	2.	2.
3.	3.	3.
4.	4.	4.
5.	5.	5.
6.		
7.		
8.		
9.		
10.		

ተሳትፎ ያደረጉ ሰልጣኞች ፊርማ



870

አባሪ ሁለት

በአስረኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ይዘቶች

ምዕራፍ	ርዕስ	በምዕራፉ የተካተቱ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች	በእያንዳንዱ ይዘት የቀረቡ ማስታወሻዎችና መመሪያዎች ብዛት
1	የቋንቋዎች እኩልነት	ንባብ ዕህፈት ንግግር ማዳመጥ ሥነ- ልሳን	3 3 3 3 1
2	ትኩረት ያለገኘው ሀብታችን	ንባብ ዕህፈት ንግግር ሥነ- ልሳን	2 3 3 2
3	ዝምታ	ንባብ ዕህፈት ንግግር ሥነ- ልሳን ሥነ- ዕሁፍ	4 5 1 2 4
4	ተበቺሳ	ንባብ ዕህፈት ንግግር ማዳመጥ ሥነ- ልሳን ሥነ- ዕሁፍ	3 2 3 2 2 4
5	የብርሃን ምዕዋት	ንባብ ዕህፈት ንግግር ሥነ- ልሳን	2 2 2 2
6	ሚንጊነኝ	ንባብ ዕህፈት ንግግር ማዳመጥ ሥነ- ልሳን ሥነ- ዕሁፍ	5 5 2 1 1 3
7	ተባበር	ንባብ ዕህፈት ማዳመጥ ሥነ- ዕሁፍ	2 3 1 2
8	የድርሰት መሰረታዊ ነገሮች	ንባብ ዕህፈት ንግግር ማዳመጥ ሥነ- ዕሁፍ	3 5 2 1 2

	የገንዘብ አጠቃቀም	ንባብ ፅህፈት ሥነ- ፅሁፍ	3 4 2
0	ሥራ ፍለጋ	ንባብ ንግግር ሥነ- ልሳን	5 4 3
1	አበዳሪና ተበዳሪ	ንባብ ንግግር ማዳመጥ ሥነ- ልሳን ሥነ- ፅሁፍ	3 3 1 3 2
2	የአበላል ስርዓት	ንባብ ፅህፈት ንግግር ሥነ- ልሳን ሥነ- ፅሁፍ	2 2 1 1 1
3	ቤተ መጻህፍት አፍራሽ ግብረ ሓይላት	ንባብ ፅህፈት ንግግር ሥነ- ልሳን ሥነ- ፅሁፍ	3 3 1 3 1
4	ኮሚፒውተር	ንባብ ፅህፈት ንግግር ሥነ- ልሳን	3 2 3 2
5	ስለ ኤድስ እንመካከር	ንባብ ፅህፈት ንግግር ሥነ- ፅሁፍ	3 3 2 2
6	የማይታክተው አገልጋይ	ንባብ ፅህፈት ንግግር ሥነ- ልሳን ሥነ- ፅሁፍ	2 2 3 1 1
17	ሀሮ	ንባብ ፅህፈት ንግግር ሥነ- ፅሁፍ	2 1 1 2
18	የማይደክመው መልዕክተኛ	ንባብ ፅህፈት ንግግር ማዳመጥ ሥነ- ልሳን ሥነ-ጽሁፍ	3 3 1 1 2 3

አባሪ ሦስት

በትግራይ ክልል ሰ/ምዕራብ ዞን በተመረጡ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቃለ መጠይቅ

ውድ መምህር/ት በመጀመሪያ ጊዜዎትን መስዋዕት በማድረግ ቃለ መጠይቅ ፍቃደኛ በመሆንዎ ከልብ አመሰግንዎታለሁ።

የዚህ ቃለ-መጠይቅ ዋና አላማ በትምህርት ቤት ደረጃ ለ10ኛ ክፍል የሚዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች በመማሪያ መፅሐፍ ካሉት የትምህርት ይዘቶች ጋር ያላቸው የተገቢነት ደረጃን ለማወቅ ለሚደረገው ጥናትና ምርምር አጋዥ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ ነው።

ጥናቱ የታለመለትን አላማ ከግብ ማድረስ የሚችለው ደግሞ ትክክለኛ መረጃ መሰብሰብ ሲቻል መሆኑ ግልፅ ነው። በመሆኑም የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና ተረድተው ተገቢና ትክክለኛ መልስ በመስጠት እንዲተባበሩኝ በትህትና እጠይቃለሁ።

ማሳሰቢያ

- የሚሰበሰበው መረጃ ለታሰበው ዓላማ ብቻ የሚውል ነው።

ጥያቄ ቁጥር አንድ፡-

እርስዎ በሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት የችሎታ መለክያ ተብለው በሚታወቁ፤ በትምህርት ቤት ደረጃ በሚዘጋጁ የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መደበኛ (የሰሚስተር አጋማሽ፣ ማጠቃለያ እና ሞዴል) ፈተናዎች ዝግጅት ላይ ይሳተፋሉ?

ጥያቄ ቁጥር ሁለት፡-

ለአስረኛ ክፍል የሚቀርበው እንደነዚህ አይነት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎቹ በዚሁ ትምህርት ቤት እንዴት እንደሚዘጋጁ ቢገልፁልኝ?

ጥያቄ ቁጥር ሦስት፡-

በፈተናዎቹ ዝግጅት ተሳታፊ እንደመሆንዎ መጠን የፈተናዎቹ ጥያቄዎች ሲመርጡ በምንጭነት የሚጠቀሙት ምንድን ነው? ማለቴ የፈተና ጥያቄዎች የሚወጡት ወይም የሚመረጡት ከየት ነው?

ጥያቄ ቁጥር አራት፡-

ፈተናዎቹን ከሚያዘጋጁት መካከል እርስዎም አሉበትና በግልዎ የፈተና ጥያቄዎቹን ሲመርጡ በብዛት ትኩረት የሚያደርጉበት የተለየ የቋንቋ ትምህርት ይዘት አለ? ካለ የትኛውን ይዘት ነው? ለምን?

ጥያቄ ቁጥር አምስት፡-

በአማርኛ ቋንቋ የአስረኛ ክፍል ፈተና ዝግጅት ወቅት የፈተና ይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ (Table of Specification) ስለመጠቀም ያለዎት ልምድ ምን ይመስላል?

ጥያቄ ቁጥር ስድስት

በአጠቃላይ የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተናዎች የይዘት ተገቢነት ወይም የፈተናዎቹ ይዘቶች ከመማሪያ መፅሐፉ ይዘቶች አንጻር ያላቸውን ተመጣጣኝ ውክልና በተመለከተ ምን የሚነግሩኝ ነገር አለ?

አባሪ አራት

የአስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ፈተና አዘጋጅ ከሆኑና በናሙናነት ከተመረጡ መምህን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ (ምላሽ)

መረጃ ሰጪ አንድ

አጠቃላይ መረጃ

- የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት - ሸሬ ሁ/ደ/ት/ቤት
- የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ - 9ኛ እና 10ኛ
- የሰለጠኑበት ትምህርት አብይ- አማርኛ ንኡስ እንግሊዘኛ
- አማርኛን በማስተማር ላይ የቆዩበት ዓመት - 4
- የትምህርት ደረጃ - ዲግሪ

የዝርዝር ጥያቄዎች መልስ

1. አዎ ፣ ለአስረኛም ሆነ ለዘጠነኛ ክፍል በሚዘጋጁ የሰሚስተር አጋማሽ፣ የሰሚስተር ማጠቃለያና ሞዴል ፈተና በሚባሉ መደበኛ የትምህርት ቤቱ ፈተናዎች ዝግጅት ላይ እሳተፋለሁ።

2. በመጀመሪያ ደረጃ እያንዳንዱ መምህር ለሚያስተምራቸው ተማሪዎች ተከታታይ ምዘና ሰለሚያካሂድ ፈተና ማዘጋጀቱ አዲስ ነገር አይደለም። የሰሚስተር አጋማሽ ማጠቃለያና ሞዴል የመሳሰሉት ፈተናዎች ሲዘጋጁ የትምህርት ክፍሉ አባላት ይሰባሰብና የተወሰኑ አባላት እንዲያዘጋጁ ይደረጋል። እነሱ አዘጋጅተው ያመጡት ፈተና የትምህርት ክፍሉ አባል ይነጋገርበታል። የተስማማባቸው ጥያቄዎች ይኖራሉ፣ ያልተስማማንባቸው ጥያቄዎች ደግሞ በሌላ ጥያቄ እንዲቀየሩ ይደረጋል።

(ተጨማሪ ጥያቄ) ከጥያቄዎቹ መካል እንዲካተቱ ወይም እንዳይካተቱ የምታደርጉት ከምን አንጻር ነው?

2.1 አብዛኛውን ጊዜ እያንዳንዱ መምህር ምን ምን ይዘቶች ማስተማር እንዳለበት በትምህርት ክፍል ደረጃ ስምምነት የደረስበታል። የፈተናዎቹ ይዘት ከነዚህ ውጭ ከሆኑ ወይም ሁሉም መምህር ካልደረሰበት ይዘት አካባቢ የወጡ ከሆኑ በሌላ እንዲቀየሩ ይደረጋል።

3. የፈተና ጥያቄዎች በበኩሌ የምወስዳቸው በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተለያዩ ማስታወሻዎች አሉ። ለምሳሌ ስለ ቋንቋ ባህርያት፣ ስለ ልብወለድ፣ ስለ ደብዳቤ፣ ዘገባ ወዘተ. የተመለከቱ ማብራሪያዎች አሉ። ከነዚህ እወስዳለሁ፣ በተጨማሪም በመፅሐፉ መጨረሻ ላይ መዳየ ቃላትና ፈሊጣዊ ንግግሮች የሚል አለ ከዚያም እወስዳለሁ።

4. አብዛኛውን ጊዜ የማዘጋጃቸው ጥያቄዎች በምዕላድ፣ የሀረግ አይነቶች፣ በሐረግ ውስጥ ያሉት ተዋቃሪዎችና ተግባሮቻቸው፣ ዘይቤና ቅኔ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው።እነዚህ የምመርጥበት ምክንያት ደግሞ የማስተምረውና በትምህርት ክፍል ደረጃም እንድናስተምረው የተስማማንበት በነዚህና መሰል ይዘቶች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ነው።

5. አሁን ስላልከው ነገር የማውቀው ነገር የለኝም።

(ተጨማሪ ጥያቄ) የይዘት መወሰኛ ሰንጠረዥ ማለት- እያንዳንዱ የትምህርት ይዘት በመማሪያ መፅሐፍ ያለውን ሽፋን በማስቀመጥ ከእያንዳንዱ ይዘት ምን ያህል ጥያቄ

በፈተና ላይ መካተት እንዳለበት ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ አስልቶ የሚያስቀምጥ ሰንጠረዥ ነው። በናንተ በኩል እንዲህ አይነት አካሄድ ያለ እንደሆነ ማለቴ ነው።

5.1እንዲህ አይነቱ አካሄድ በበኩሌ አላውቀውም።

6. የፈተና ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ ከመማሪያ መፅሐፍ ብቻ ማውጣት ማለት የማይታሰብ ጉዳይ ነው። ተማሪዎቻችንም ይህን አይወዱትም፣ አይጠብቁትምም። ተማሪ ከመፅሐፍ ወጣ ያለና በተለይ በ Grammar ላይ ያተኮረ ጥያቄ ብታመጣለት ደስ ይለዋል፤ ትምህርቱም ጠበቅ አድርጎ ይይዘዋል። ከዚህ አንጻር የትምህርት ቤታችን የአማርኛ ፈተናዎች በተለይ ደግሞ ሞዴል ፈተና በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ካሉት ይዘቶች ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ውክልና አላቸው ብዬ አላምንም።

መረጃ ሰጪ ሁለት

አጠቃላይ መረጃ

- የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ሸሪፊ ሁ/ደ/ ት/ቤት
- የሚያስተምሩት የክፍል ደረጃ 10ኛ
- የሰለጠነበት ትምህርት አብይ አማርኛ ንኡስ ትግርኛ
- አማርኛን በማስተማር የቆዩበት ዓመት 10
- የትምህርት ደረጃ ዲግሪ

የዝርዝር ጥያቄዎች መልስ

1. በመደበኛ ፈተናዎች ማለትም በሰሚስቴር አጋማሽ፣ በማጠቃለያና በሞዴል ፈተናዎች ዝግጅት ላይ እሳተፋለሁ።

2. አብዛኛውን ጊዜ ፈተናዎች የሚዘጋጁት በዲፓርትመንት ውስጥ ካሉት አባላት መካከል የተወሰኑትን በጋራ ወይም በግል እንዲያዘጋጁ በመነጋገር ነው። እነሱ አዘጋጅተው ያመጡት ፈተና በዲፓርትመንት አባላት ይታያል፤ ይህ ጥያቄ ተማሪዎቹ አልተማሩትም ወይም አልደረሰኩብትም ይሰረዝ፣ እንዲህ አይነት ጥያዌ ቢጨመርም ጥሩ ነው ወዘተ. በማለት የተወሰነ ማስተካከያ ተደርጎበት ይፀድቃል።

3. ጥያቄዎቹን ከየት ይመረጣሉ የሚለው ጥያቄ እንደ ግለሰብ ይለያል። ለምሳሌ እኔ ከተለያዩ መጻሕፍት ማለትም ለሽያጭ የሚውሉ ልዩ ልዩ ደጋፊ መጻህፍት በምንጭነት

ቀማለሁ። አልፎ አልፎም በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ
ግሮች እንዲሁም ተመሳሳይና ተቃራኒ ቃላት በቀጥታ የምወስድበት አጋጣሚ አለ።
ከቋንቋ ትምህርት ይዘቶች መካከል የበለጠ ትኩረት አለ ማለት እችላለሁ ለምሳሌ፦
ን- ጽሁፍ እውቀት ውስጥ የሚካተቱ ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮች፣ ስነ- ግጥምን፣
ገለድ፣ ዘይቤና ቅኔ ጥያቄዎችን ሳዘጋጅ በይበልጥ ትኩረት የማደርግባቸው ይዘቶች
ው። ሌሎች የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ለምሳሌ እንደማዳመጥና ንግግር የመሳሰሉ
ን አይነት ጥያቄ ልታዘጋጅላቸው ትችላለህ? በቋንቋ ላባሪቶሪ ካልሆነ በስተቀር።
ዚህ ቅድም የጠቀስኳቸው ይዘቶች ጥያቄ ለማዘጋጀት የሚመቹ በመሆናቸው ነው
ርጥኳቸው።
ምን ለማለት እንደተፈለገ ይብራራልኝ።
ጨማሪ ማብራሪያ) የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ካላቸው
ን አንጻር በማየት በአይነትና በመጠን ወስኖ በፈተናዎች ላይ በተመጣጣኝ መልኩ
ዲካተቱ የማድረግ ልምድ ማለቱ ነው።
ይህ ጉዳይ ተግባራዊ ባላደርገውም በሐሳብ ደረጃ የማውቀውና የማምንበት ጉዳይ
። ይሁን እንጂ እዚህ ካለው የስራ ጫና አንጻር ስታየው ለመስራት የሚታሰብ
ይደለም። ከዚህ በተጨማሪም በአብዛኞቹ መምህራን የሚታወቅ ጉዳይ ባለመሆኑ
ሮህ የሚሰራ አታገኝም።
ቀደም ሲል እንደገለጽኩልህ እኔ በበኩሌ ጥያቄዎችን የምመርጣቸው ሙሉ በሙሉ
መማሪያ መጽሐፍ አይደለም። በተጨማሪም ጥያቄዎቹን በተወሰኑ ይዘቶች ብቻ
ኩረት ያደረጉ ናቸው። ከዚህ አንጻር ትምህርት ቤታችን ፈተናዎች በመማሪያ
ጽሐፉ ካሉት ይዘቶች ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ውክልና ያላቸው ይዘቶች ይኖራቸዋል
ሚል ግምት የለኝም።

ንደባጉና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅና የሰጡት ምላሽ

ረጃ ሰጪ- ሦስት

ክቃላይ መረጃ

- የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ዓዲ ዳ/ሁ/ደ/ት/ቤት
- የሚያስተምሩት ክፍል 9ኛ ና 10ኛ

- የሰለጠኑበት ትምህርት አብይ አማርኛ ንኡስ እንግሊዝኛ
- ያስተማሩት ዓመት 8 ዓመት
- የትምህርት ደረጃ ዲግሪ

የዝርዝር ጥያቄዎች መልስ

1. በትምህርት ቤታችን በሚዘጋጁ የሰሚስቴር አጋማሽ፣ የማጠቃለያ እና ሞዴል አስረኛ ክፍል ፈተና ዝግጅት ላይ እሳተፋለሁ።

2. የፈተና ዝግጅት በተመለከተ በዲፓርትመንታችን አንድ የተለመደ ነገር አለ። እሱም እያንዳንዱ መምህር በመደበኛነት በሚታወቁ የሰሚስቴር አጋማሽና የመጠቃለያ ፈተና በሁለቱም ሰሚስቴር እንዲሁም ሞዴል የአስረኛ ክፍ ፈተናዎች ተራ ተደልድሏል። በተራው መሰረት የፈተናዎች ጥያቄ አዘጋጅቶ ይመጣል። ከዚህ በኋላ ዲፓርትመንቱ ተጠሪ አይቶ ፈርሞ ለፅሕፈት ቤት ገቢ ያደርጋል። በዚህ መሰረት ፈተናዎች እየተዘጋጁ ይቀርባሉ።

(ተጨማሪ ጥያቄ) አንዱ ፈተና አዘጋጅቶ ሲመጣ ሌሎች በፈተና ጥያቄዎች ዙሪያ የሚያነሱት ጥያቄ የለም?

2.1 በመጀመሪያ ደረጃ የዲፓርትመንቱ አባላት በሙሉ በምን ዙሪያ ማስተማር እንዳለብን የተስማማንበት ጉዳይ አለ። ለምሳሌ፦ በአንደኛ ሰሚስቴር ስለ ምዕላድ እና የቃል ክፍል (በመማሪያ መፅሐፉ ካለው በተጨማሪ የሚሰጥ ትምህርት ነው) እናስተምር ከተባለ ፈተናውም በዚያ ዙሪያ የሚያውጣነጥኑ ጥያቄዎች ያካትታል። ይህም ከመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ ወይም ከዚያ ውጭ ካሉት ሌሎች መጻህፍት (ለምሳሌ - የአማርኛ ቋንቋ አጠቃላይ መማሪያ ከ 9-12ኛ ክፍል የሚል) ሊሆን ይችላል።

3. በግሌ የተለየ ትኩረት የምሰጥበት ይዘት የምለው የለኝም። ዲፓርትመንቱ ቀደም ብሎ ካስቀመጣቸው የትምህርት ይዘቶች መካከል ነው ጥያቄዎችን የማዘጋጀው።

(ተጨማሪ ጥያቄ) ዲፓርትመንቱ የሚያስቀምጣቸው ያሉኝ የትምህርት ይዘቶች የተወሰኑ ቢጠቅሱልኝ።

3.1 ስነ- ቃል፣ ስነ- ግጥም፣ ዘይቤ፣ ስነ- ሐረግ፣ ፊሊጣዊና ምሳሌያዊ አነጋገር፣ ልብወለድ፣ ተውኔት፣ ቅኔ ወዘተ ናቸው።

4. በብዛት ትኩረት የማደርግበት ይዘት በተለይ ለአስረኛ ክፍል ከሆነ ማትሪክ ላይ ሊያጋጥሙ በሚችሉት ለምሳሌ- እንደ ቅኔ፣ ዘይቤ፣ ልብወለድ፣የዓረፍተ-ነገር አይነቶች፣

ተቃራኒና ተመሳሳይ የቃላት ፍቺ እና ሰዋሰዋዊ ስህተት የሚታይባቸው ዓረፍተ-ነገሮች ባለቤትና ተሳቢ በሚል ዙሪ ላይ ነው ::

5.ሰንጠረዥ የሚባል ተጠቅሜ አላውቅም::

6.በመማሪያ መጽሐፉ ያሉት ይዘቶችና በፈተና ላይ ያሉት የጥያቄዎች ይዘቶች ሙሉ በሙሉ የሚመሳሰሉ ናቸው ለማለት ከብደኛል::

(ተጨማሪ ጥያቄ) ስለዚህ ተመጣጣኝ የሆነ ውክልና አይኖራቸውም የሚሉኝ?

6.1 አዎ::

መረጃ ሰጪ 4

አጠቃላይ መረጃ

- የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት እ/ጉና ሁ/ደ/ት/ቤት
- የሚያስተምሩት ክፍል 9ኛ እና 10ኛ
- የሰለጠኑበት ትምህርት አብይ አማርኛ ንኡስ ትግርኛ
- ያስተማሩት ዓመት 3 ዓመት
- የትምህርት ደረጃ ዲግሪ

የዝርዝር ጥያቄዎች መልስ

1.አዎ፤በሁሉም ፈተናዎች ዝግጅት እሳተፋለሁ::

2.መደበኛ ፈተናዎቹ የሚዘጋጁበት በዲፓርትመንት በተወከሉ መምህራን አማካኝነት ነው:: አብዛኛው ጊዜ ተረኛ መምህራን አዘጋጅተው ያመጡና ትምህርት ክፍሉ ተጠሪ ፈርሞለት ለፀሐፊ ይሰጣል:: አንዳንድ ጊዜ ግን በፈተናው ስለተካተቱ ጥያቄዎች ውይይት ይደረጋል:: በዚህ ወቅት ተማሪዎች ያልተማሩት ከሆነ እንዲቀየር ይደረጋል::

(ተጨማሪ ጥያቄ) ተማሪዎች ያልተማሩ ሲሉ ምን ማለትዎ ነው? ሁሉም መምህር በመማሪያ መጽሐፉ ያለውን አይደል የሚያስተምረው?

2.1 አይደለም! ሁሉም መምህር በመጽሐፉ አይሄድም:: አንዳንዱ ደስ ያለውን ርእስ ከሌላ አምጥቶ ያስተምራል፤ሌላውም እንደዚሁ ነው:: በዚህ ጊዜ ፈተና ሲወጣ ሁሉን ያስተማረውን ትምህርት መሰረት ያደረገ እንዲሆን ይነገራል::

(ተጨማሪ ጥያቄ) ከመማሪያ መጽሐፍ ውጭ በትምህርትነት የሚቀርቡ ይዘቶች ምን ላይ የሚያተኩሩ ናቸው?

2.2አብዛኞቹ መምህራን በልቦለድ፣ በዘይቤና ሰዋስው ይዘቶች ላይ ያተኩራል::

3.የፈተና ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ ካስተማርነው ትምህርት ነው የምንመርጣቸው

ለምሳሌ - ስለ የሀረግ አይነቶች ወይም የልቦለድ አላባዊያን እናስተምራን ከዚያ ደግሞ ጥያቄዎች እናወጣለን::

4.እኔ ፈተናዎችን ሳዘጋጅ ከሁሉንም ለማካተት ጥረት አደርጋለሁ:: ነገር ግን በብዛት ሰዋሰውንና ስነ- ጽሁፋዊ ይዘቶችን ስለማስተምር ብዙ ጥያቄዎችም ከነዚህ ይዘቶች ነው የማወጣው::

5.የፈተና ጥያቄዎች ስናዘጋጅ ከየትኛው ይዘት ምን ያህል ይሁን ብሎ በመወሰን ማዘጋጅት የሚቻል ይመስለኛል:: እስካሁን ድረስ ግን እንደዚህ አድርጌ አላውቅም::

6.በፈተና ውስጥ የሚካተቱ ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ባላቸው ብዛት መጠን የሚመረጡ አይመስለኝም:: በመሆኑም ፈተናዎቹ ሙሉ በሙሉ የመማሪያ መጽሐፉን ነጸብራቅ ናቸው ብሎ መናገር አይቻልም::

የዓዲዳዕሮ ትምህርት ቤት መምህራን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ(ምላሽ)

መረጃ ሰጪ 5

አጠቃላይ መረጃ

- የሚያስመትሩበት ት/ ቤት ዓዲ ዳ/ሁ/ደ/ት/ቤት
- የሚያስተምሩት የክፍ ደረጃ - 9ኛ እና 10ኛ
- የሰለጠኑበት ትምህርት አብይ ትግርኛ ንኡስ አማርኛ
- አማርኛን በማስተማረ የቆዩበት አመት 4

የዝርዝር ጥያቄዎች መልስ

1.አዎ! በሁሉም ፈተናዎች ዝግጅት እሳተፋለሁ

2.ፈተናዎች ስናዘጋጅ ሁላችን ወጥ ሆነ አካሄድ የለንም:: አንዳንድ ጊዜ ሁለት ወይም ሶስት የዲፓርትመንቱ አባላት በጋራ ሁነው እየተወያዩ ጥያቄዎችን የሚያዘጋጁበት አጋጣሚ አለ:: ሌላ ጊዜ ደግሞ አንድ የዲፓርትመንቱ አባል በፍቃደኝነት አልያም ተራው ደርሶ አዘጋጅቶ ይመጣና ለዲፓርትመንት ተጠሪው ያስረክባል::

(ተጨማሪ ጥያቄ) ተዘጋጅተው የሚመጡ ጥያቄዎች በተመለከተ አስተያት እንዲሰጥ የሚደረግበት አጋጣሚ አለ?

2.1ብዙውን ጊዜ ይህ የሚሆነው ከፈተና በኋላ ነው። አንዱ በሌላው አስተያየት ለመስጠትም ብዙውን ጊዜ ድፍረት አይኖረውም። ምክንያቱ ደግሞ ማን ከማን በልጦ ነው የሚል መንፈስ ስለሚጭር ነው።

3.እኔ ጥያቄዎችን ሳወጣ ያስተማርኩበት ደብተርን ነው በምንችነት የምጠቀመው። የማስተማርበት ደብተር የተለያዩ ማስታወሻዎችና ጥያቄዎች የያዘ በመሆኑ የፈተና ጥያቄዎችን በቀላሉ ለመምረጥ ይጠቅመኛል።

(ተጨማሪ ጥያቄ) በደብተርዎ የሚገኙ ማስታወሻዎች ከየት የተወሰዱ ናቸው? ምሳሌዎች በሚቅሱልኝ ?

3.1ከመማሪ መጽሐፍ ውጭ ካሉት የተለያዩ መጻህፍት የተወሰዱ ናቸው። ለምሳሌ- የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፣ የስነ- ጸሁፍ መሰረታዊያን አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የመሳሰሉት ናቸው።

4.በብዛት ትኩረት የሚርግበት ይዘት በተለይ ለአስረኛ ክፍል ከሆነ ማትሪክ ላይ ሊጋጥሙ በሚችሉት ለምሳሌ- እንደ ቅኔ፣ ዘይቤ፣ የሀረግ አይነቶች፣ ተቃራኒና ተመሳሳይ የቃላት ፍቺ እና ሰዋሰዋዊ ስህተት የሚይባቸው ዓ/ነገሮች ባለቤትና ተሳቢ በሚል ዙሪ ላይ ነው ።

5.የፈተና ይዘት ሰንጠረዥ የሚባል ነገር በበኩሌ አላውቀውም አልጠቀምም።

6.በርግጥ የፈተና ይዘቶች ተማሪዎች እንዲማሩበት ከተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ መዘጋጀት አለበት። ነገር ግን በብዛት ተማሪዎች የሚማሩት ከመማሪያ መጽሐፍ ያሉት ይዘቶችን ነው። ለምሳ በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ‹‹ንግግር››ለማስተማር የሚቀርቡ ነገሮች አሉ። ተማሪዎች ግን እሱን ከምታቀርብላቸው ስለ Grammar ብታስተምራቸው ይበልጥ ይከታተሉሃል። ከዚህ አንጻር ፈተናዎች የሚዘጋጁት ተማሪዎች ከተማሩት እንጂ ከመማሪያ መጽሐፉ ባለመሆናቸው ተመጣጣኝ የሆነ ውክልና አላቸው አልልም።

መረጃ ሰጪ -6

አጠቃላይ መረጃ

- የሚያስተምሩበት ት/ቤት <u>ዓዲ ዳ/ሁ/ደ/ ትምህርት ቤት</u>
- የሚያስተምሩት ክፍል <u>9ኛ እና 10ኛ</u>
- የሰለጠኑበት ትምህርት አብይ <u>አማርኛ እና ትግርኛ</u>
- አማርኛን በማስተማር የቆዩበት ዓመት <u>4</u>
- የትምህርት ደረጃ <u>ዲግሪ</u>

የዝርዝር ጥያቄዎች መልስ

1. በቡድንም ሆነ በግል ደረጃ ፈተናዎችን አዘጋጃለሁ።
2. በኛ ትምህርት ቤት ፈተናዎችን የምናዘጋጀው በቡድን ወይም በግል ነው። ሰፊ ይዘት ያላቸው እንደ ሞዴል እና የማጠቃለያ ፈተናዎች የመሳሰሉት በዲፓርትመንት ውስጥ ያሉት መምህራን የክፍል ደረጃዎቹን በመከፋፈል በቡድን ሆነው ያዘጋጃሉ። የሰሚስተር አጋማሽ ፈተና ደግሞ በግል ደረጃ የሚዘጋጅ ነው። በቡድንም ሆነ በግል ደረጃ የሚዘጋጁት ፈተናዎች አብዛኛውን ጊዜ ለውይይት ቀርበው ነው የሚጸድቁት።
3. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ድርሰት፣ ዘገባ፣ ሐረግ የቋንቋ ባህሪያትን፣ ግጥም፣ ልቦወለድ ወዘተ. በተመለከተ የተሰጡ ማስታወሻዎች አሉ። ከዚህ በተጨማሪ ስለነዚህና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች በተመለከተ የራሴ የማስታወሻ ደብተር አለኝ። እነዚህንና በመማሪያ መጽሐፉ የመጨረሻ ክፍል አካባቢ ያሉት ሙዳየ ቃላት በመጠቀም ጥያቄዎችን አዘጋጃለሁኝ።
4. የፈተና ጥያቄዎችን ስመርጥ ያስተማርኳቸውን ይዘቶች በሙሉ እኩል ትኩረት ለመስጠት ጥረት አደርጋለሁ።

   (ተጨማሪ ጥያቄ) የሚያስተምሯቸው ይዘቶች አራቱን የቋንቋ ክሂሎችና ሁለቱን የእውቀት ዘርፎች ያካተቱ ናቸው ይላሉ?

4.1እነዚህ ሁሉን ያካተተ አይደለም። አብዛኛው ጊዜ በኛ የሚሰጠው ትምህርት በሁለቱም የእውቀት ዘርፎች ላይ ያተኮረ ነው። ክሂሎችን የተመለከተ የንባብና ፅሕፈት ክሂል በመማሪያ መጽሐፉ ባሉት ይዘቶች አማካኝነት ትምህርቱ ይቀርባል፤ ፈተናም ከዚህ ይዘጋጃል። ነገር ግን የሚዳመጥና የንግግር ክሂሎች ብዙ ግዜ በትምህርት ላይ ሽፋን ስለማይሰጣቸው በፈተና ላይም ትኩረት አይሰጣቸውም።

5. በፈተና ዝግጅት ወቅት ሰንጠረዥ የሚባል ነገር ተጠቅሜ አላውቅም።

6.የምናዘጋጃቸው ፈተናዎች ይዘት እኛ ከምናስተምረው ትምህርት አንጻር ተገቢነት ያላቸው ናቸው። ነገር ግን በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ካሉት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች አንጻር ሲታይ ተመጣጣኝነት ላይኖራቸው ይችላል የሚል እምነት አለኝ።

ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስምና ፊርማዬ የሚታየው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ አማርኛ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ተማሪ ስሆን ይህ የሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያ ጥናት የራሴ ስራና የተጠቀምኩባቸውን ምንጮችም በሙሉ የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ሥም ፊርማ

_____ _____

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

አማርኛ ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

አዲስ አበባ

የማስረከቢያ ጊዜ መጋቢት 2003